# የክቡር ዶክተር ሀዲስ ዓለማየሁ የሕይወት ታሪክና የስነፅሑፍ ስራዎቻቸው

1997

ETHIOPIA
FOREIGN LANGUAGES

በ

ፈለቀች እሸቴ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ግንቦት 1992 ዓ.ም

928.928
ፈለቀ

# የክቡር ዶክተር ሀዲስ ዓለማየሁ የሕይወት ታሪክና የስነጽሑፍ ስራዎቻቸው

INSTITUTE OF ETHIOPIA STUDIES
FOREIGN LANGUAGES

በ

ፈለቀች እሸቴ

የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉ ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ

አማካሪ

ዘሪሁን አስፋው

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

ግንቦት 1992 ዓ.ም



ክቡር ዶክተር ሀዲስ ዓለማየሁ

# ምስጋና


- የጥናት ጽሑፌን አስጀምሮ ላስጨረሰኝ ለልዑል እግዚአብሔር ምስጋና ይሁን፡፡
- ይህን ርዕስ ለመረጡልኝና የጥናት ጽሑፌን ያለመሰልቸት ላረሙልኝ ለአማካሪዬ ዘሪሁን አስፋው ታላቅ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡
- ለጥናት ጽሑፌ መሠረት የሆኑኝን ክቡር ዶክተር ሀዲስ ዓለማየሁን አመሰግናለሁ፡፡ ድካምና ሕመም ተጭኗቸው ሳለ ቃለ መጠይቅ እንዳደርግላቸው ተባብረውኛልና!
- ክቡር ዶክተር ሀዲስ ዓለማየሁ ዘንድ እንድቀርብ ለረዱችኝ ወይዘሮ ባንቺ አምላክም ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡
- ከምንም ነገር በላይ የልጄን መማር በማስበለጥ እዚህ ደረጃ እንድደርስ ለረዳኝ ለአባቴ አቶ እሸቴ ወንድምአገኘሁ እና በሃሳብ ላልተለየችኝ ለእናቴ ወ/ሮ ፀሐይ መኮንን ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡
- እህቴ አስቴር እሸቴም በሃሳብና በሞራል ለትምህርት የሚያስፈልጉኝን በማሟላት ትብብሯ ስላልተለየኝ አመሰግናታለሁ፡፡
- በህትመት ስራ ለረዱኝ ለአቶ ጌታቸው ወልዩ፣ ወ/ሪ ወይንሸት አበበ፣ ወ/ሪ አልማዝ አጥላው ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

# ማውጫ

ጽርጽክት ገፅ

መግቢያ ........................................................................ ሀ

ሀ. የጥናቱ ዓላማ ........................................................ ሀ

ለ. የጥናቱ አስፈላጊነት ................................................. ለ

ሐ. የመረጃ አሰባሰብ ስልት ........................................... ለ

መ. ያጋጠሙ ችግሮች ................................................. ለ

1. የሕይወት ታሪክ ምንነትና የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ..................... 1

1.1 የሕይወት ታሪክ ምንነት ........................................................ 1

1.2 የደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁን የሕይወት ታሪክ የዳሰሱ ጽሑፎች ቅኝት...4

1.3 በደራስያን የሕይወት ታሪክና የስነ ጽሑፍ ስራዎቻቸው ላይ የተሰሩ ጥናታዊ ጽሑፎች ቅኝት........................................................ 8

1.4 በደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁ የስነ-ጽሑፍ ስራዎች ላይ የተሰሩ ጥናታዊ ጽሑፎች ቅኝት ....................................................... 15

2. የደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁ የሕይወት ታሪክ ................................ 21

2.1 ልደትና አስተዳደግ ...................................................... 21

2.2 ትምህርት ........................................................................ 22

2.2.1 ባህላዊ ትምህርት ........................................................ 22

2.2.2 ዘመናዊ ትምርት ........................................................ 24

2.3 የሥራ ዓለም .......... ........................................... 28

2.3.1 በመምህርነት ........................................................ 28

2.3.2 በአርበኝነት ........................................................ 29

2.3.3 በሚኒስትርነት ........................................................ 31

2.3.4 በአምባሳደርነት ........................................................ 33

2.4 ትዳር ........................................................................ 37

2.5 የደራሲው ዋና ዋና ባሕርያት .......... ........................................ 39

3 ደራሲ ሀዲስ ከረገኸኘም ልቦለዶቻቸው አራት ዋና ገጸባህርያት ጋር ያላቸው ጥቂት ተመሳስሎ ........................................ 44

3.1 ሀዲስ በፍቅር እስከ መቃብር ........................................ 44

3.1.1 የፍቅር እስከ መቃብር ታሪክ ባጭሩ ........................................ 44

3.1.2 ሀዲስና በዛብህ ........................................ 47

3.1.3 ሀዲስና ጉዱ ካሳ ........................................ 48

3.2 ሀዲስ በወንጀለኛው ዳኛ ........................................ .. 49

3.2.1 የወንጀለኛው ዳኛ ታሪክ ባጭሩ ........................................ 49

3.2.2 ሀዲስና ጥላሁን ........................................ 52

3.3 ሀዲስ በ የልምዣት........................................ 53

3.3.1 የየልምዣት አጭር ታሪክ ........................................ 53

3.3.2 ሀዲስና በሻህ ........................................ 55

ማጠቃለያ ........................................ ........................................ 59

ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው........................................ 60

ዋቢ መጻሕፍት........................................ ........................................ 61

አባሪዎች

# መግቢያ

ይህ የጥናት ጽሑፍ በሦስት ምዕራፎች ተከፍሏል፡፡ የመጀመሪያው ምዕራፍ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ተዛማጅ ጥናቶች የቀረቡበት ሲሆን፤ በውስጡም የሕይወት ታሪክን ምንነት፣ የደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁን የሕይወት ታሪክ የዳሰሱ ጽሑፎችን፣ በደራስያን የሕይወት ታሪክና የስነ ጽሑፍ ስራዎቻቸው ላይ የተሰሩ እና በሀዲስ የስነጽሑፍ ስራዎች ላይ የተሰሩ የጥናት ጽሑፎችን ቅኝት ይዟል፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ የደራሲ ሀዲስ የሕይወት ታሪክ ከልደታቸው አሁን እስካሉበት ድረስ ተዘግቦበታል፡፡

በሦስተኛው ምዕራፍ ደግሞ ከደራሲው ሰባት መጽሐፎች ሦስቱን ረገኘሮም ልቦለዶች /ፍቅር እስከ መቃብር፣ ወንጀለኛው ዳኛና የልምዣት/ በመምረጥ በየመጽሐፎቹ ከተቀረጹት ዓበይት ገጸባህርያት ከአራቱ /በዛብህ፣ ጉዱ ካሳ፣ ጥላሁንና በሻህ / ጋር ያላቸውን ጥቂት ተመሳስሎ ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡ በመጨረሻም የጥናት ጽሑፉ ማጠቃለያ ቀርቧል፡፡ አባሪዎችና ዋቢ መጽሐፎችም የዚህ ጽሑፍ አካል ናቸው፡፡

## ሀ. የጥናቱ ዓላማ

የስነ - ጽሑፍ ሰዎችን ትኩረት አድርገው የሚነሱ ጥናቶች የተለያዩ አላማዎች አሏቸው፡፡ የደራሲውን የሕይወት ታሪክ መመዝገብ፣ ደራሲውን ከስነልቦና ቲዎሪዎች አንፃር ማጥናት፣ ደራሲውን ከነበረበት /ካለበት/ ኅብረተሰብ፣ ባህልና ወግ አንፃር ማጥናት ወዘተ ከአላማዎቻቸው ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ በደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁ ላይ አተኩሮ የሚሰራው ይህ ጥናትም ሁለት አላማዎች አሉት፡-

1. የደራሲውን የሕይወት ታሪክ ከራሳቸው አንደበት፣ በቅርብ ከሚያውቋቸው ሰዎችና ከሌሎች የጽሑፍ መረጃዎች በማሰባሰብ በዝርዝር መጻፍ
2. የደራሲው የሕይወት ታሪክ ከስነ ጽሑፍ ስራዎቻቸው ጋር ምን ያህል ተዛምዶ እንዳለው መፈተሽ፡፡

ለ. የጥናቱ አስፈላጊነት

ደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁ ከታላላቅ ሰዎች አንዱ በመሆናቸው የሕይወት ታሪካቸውን መዝግቦ ለተተኪው ትውልድ ማቆየት ተገቢ ነው። ምንም እንኳን በተለያየ መገናኛ ብዙሐንና በግለሰቦች ስለ ሕይወት ታሪካቸው አንዳንድ ጉዳዮች ቢወሱም በቂ አይደሉም፤ ከልደታቸው አሁን እስካሉበት ጊዜ ድረስ ያሳለፉትን ሕይወት በዝርዝር አላቀረቡም። በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍልም የደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁን የሕይወት ታሪክና የስነ - ጽሑፍ ስራዎቻቸውን በጥምረት የያዘ የጥናት ጽሑፍ የለም። በመሆኑም የእኒዚህን ታላቅ ደራሲ የሕይወት ታሪክ መዝግቦ ለማቆየትና ሌሎች አጥኚዎችም መነሻ ይሆናቸው ዘንድ ይህ ጥናት መዘጋጀቱ አስፈለገ።

ሐ. የመረጃ አሰባሰብ ስልት

በደራሲው የሕይወት ታሪክና ስነጽሑፍ ስራ ላይ ጥናት ለማድረግ መረጃ መሰብሰብ የጀመርኩት ደራሲውን መነሻ በማድረግ ነው። ደራሲውን በዋና መረጃነት በመያዝ ቃለመጠይቅ አድርጌላቸው ድምጻቸውን በቴፕ /ለመቅረፀ - ድምጽ/ ቀድቻለሁ። ለደራሲው ቅርብ የሆኑትን ሰዎች በማፈላለግም ጓደኞቻቸውንና ዘመዶቻቸውን አነጋግሪያለሁ። ። ስለደራሲው የተፃፉ አንዳንድ መፅሐፍና መፅሔቶችንም በመመልከት ጠቃሚ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ።

መ. ያጋጠሙ ችግሮች

ደራሲውን ለማግኘት ብዙ ውጣ ውረድ ገጥሞኛል። ከተገኙ በኋላም የጤና መታወክ ስለገጠማቸው ጤንነት እስኪሰማቸው ድረስ መጠበቅና በቃለ መጠይቁ ወቅት የደራሲው አንዳንድ ሁኔታዎችን በተለይ ዓመተ ምህረትን በተመለከተ መርሳታቸው ሌሎች ችግሮች ነበሩ። ስለደራሲው የሕይወት ታሪክ መረጃ ይሰጣሉ ተብለው የታሰቡት አንዳንድ ግለሰቦች ፈቃደኛ አለመሆናቸው፤ እነሱን ለማግባባት መሞከርም ሌላው ከባድ ፈተና ነበር።

# ምዕራፍ አንድ

# 1. የሕይወት ታሪክ ምንነትና የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት

## 1.1 የህይወት ታሪክ ምንነት

የህይወት ታሪክ ምንነትን በተመለከተ በተለያዩ መጽሀፎች ተቀራራቢ ብያኔዎች ተሰጥተዋል፡፡ ስለ አጀማመሩ "ካምብሪጅ ኢንሳይክሎፒዲያ" እንዲህ በማለት ይገልጻል፡-

> የሕይወት ታሪክ የግለሰብ ሕይወት ትረካ ነው፡፡ እንደምናውቀው ቅርጽ የተስተካከለው በዘመናዊው ክፍለ ዘመን /ከ17ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ/ ነው፡፡ በጥንት (Classical) እና በመካከለኛው ዘመን የሕይወት ታሪክ የሚዳፈው ጥቅልና ምሳሌያዊ በሆኑ በነገሥታት በጀግኖችና በቅዱሳን ታሪክ ላይ ሆኖ፤ በጥቂቱ ግለሰባዊ ጉዳይንም ያካተተ ነበር፡፡ ነገር ግን ፕሮቴስታንቶችና ዲሞክራቶች ለእያንዳንዱ ሰው ታላቅ ዋጋ በመስጠት አከበሯቸው፤ እናም የቦስዋል ታላቁ የሕይወት ታሪክ በ1791 ዶክተር ጆንሰን በፃፈው የማንኛውም ሰው የሕይወት ታሪክ ዋጋ ያለው ንባብ መሆኑን ጠቀሰ፡፡ ... በሃያኛው ክፍለ ዘመን ደግሞ በቴፕ፣ ሬዲዮ፣ ፊልምና ቴሌቪዥን የተቀረጸ የሕይወት ታሪክ ማግኘት ተቻለ፡፡[1] ...
> *(Cambridge Encyclopedia .             1994:147)*

ከዚህ ጥቅስ ቀድሞ የሕይወት ታሪክ አፃፃፍ ምን ይመስል እንደነበርና አሁን በዘመናችን ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ መረዳት እንችላለን፡፡ የህይወት ታሪክ አንድ ሰው በሕይወት እያለ ባሳለፋቸው ጊዜያት እንዴት እንደኖረ፣ ምን እንደሰራ፣ ምን እንዳጋጠመው፣... ወዘተ የሚመዘገብበት ታሪክ ነው፡፡ ሰው በዕድሜው ደግም ሰራ ክፉ በሕይወቱ ያሳለፈው፣ የፈጸመው ታሪክ ይኖረዋል፡፡ «... ሁሉም የሕይወት ታሪኮች የሚጋሩት አንድ ነገር አለ፡፡ ይኸውም ትኩረታቸው በእውነተኛ ታሪክ እና ገጠመኝ ላይ የተመሰረተ መሆኑ ነው፡፡»[2] (Leon Edel, 1959: 2)

የሕይወት ታሪክ የግለሰብ ሕይወት በጽሑፍ ወይም በንግግር የሚቀርብበት የታሪክ ቅርንጫፍ ሲሆን በስነፅሑፍ መልኩ ታዋቂነቱ የጎላውም ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ ነው፡፡ (Harry shaw, 1997)

ሀሪ ሾው አጻጻፉን አስመልክቶ ሲገልጽ ለሕይወት ታሪክ ጸሐፊው ማንኛውም አይነት መረጃዎች ከሥራው ጋር ግንኙነት እንደሚኖራቸው ጠቅሶ መረጃዎቹም የባለታሪኩ የራሱ ጽሑፎች በተለይ የእለት ውሎውን የሚመዘግብበት ማስታወሻዎች

(diaries) እና ደብዳቤዎች፣ ልብሱን ያሳጠበበት ደረሰኝ (Laundary bills)፣ ቀድሞ ሰብስቦ ያስቀመጣቸው ታሪካዊ ጽሑፎች፣ ወቅታዊ የሆኑ ማስታወሻዎች፣ ፎቶዎችና ቅቦች፣ በሕይወት ያሉ ሰዎች (ምስክሮች)፣ ትዝታ፣ ታሪካዊ ጽሑፎች የግለሰቡ እውቀት እና የግለሰቡ ሌሎች መጽሐፎች መሆናቸውን ያትታል።

A new Encyclopedia Britanica: (Chicago, 1993, Vol.2, 222) ከላይ የተጠቀሱት መፅሐፎች ከሰጡት ብያኔ በተጨማሪ የቀደሙት የሕይወት ታሪክ መረጃዎች የቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ የሚደረጉ ንግግሮች ወይም ጽሁፎች ሊሆኑ የሚችሉ፣ ብዙውን ጊዜ ሕይወት የሚመሰገንባቸው እና የሟች ምሳሌነት የሚጠቀስባቸው እንደ ነበሩ ገልጿል።

ከላይ ስለ ሕይወት ታሪክ ከተሰጡት ብያኔዎች ተነስተን የሕይወት ታሪክ ምን ያህል የሚያጓጓ ታሪክ እንደሆነ እንገምታለን። ግለሰቡ /ባለታሪኩ/ ለሌሎች ሰዎች የጻፋቸውን፣ ሌሎች ሰዎች ለግለሰቡ የጻፉለትን ደብዳቤ፣ የእለት ውሎውን የሚመዘግብባቸውን ማስታወሻዎች እና አንዳንድ እሱነቱን የሚነግሩን ጹሁፎችን ማንበብ ከማስደሰትና ከማሳዘን አልፈው የሚያጋሩን የሕይወት ገጠመኝ ከፍተኛ ነው። «ሊተን ስትራች የተባለው ሰው አንድ ጊዜ የሕይወት ታሪክን 'ከሁሉም የኪነ ጥበብ ዘርፎች በተለየ በረቂቅነት የሚሰራና ሰዋዊ ነው።»[3] በላቀ በጣም አስደሳችና ነፍስ ያለው ሰዋዊ ነው። በማለት ገልጿል (Leon Edel,1959, 1)

የሕይወት ታሪክ በሁለት መንገድ ሊጻፍ ይችላል። አንደኛው ግለሰቡ በሕይወት እያለ ስለራሱ የሚጽፈው ሲሆን ይህ በእንግሊዝኛው «Autobiography» በአማርኛ /ግለ ሕይወት/ ታሪክ የሚባለው ነው። ሁለተኛው ደግሞ የሕይወት ታሪክ «Biography» የሚባለው የአንድ ግለሰብን የሕይወት ታሪክ ሌላ ሰው ሲፅፈው ነው።

በባለ ታሪኩ በራሱ የሚጻፈው የሕይወት ታሪክ ሌሎች ስለ እሱ ሕይወት የሚሉት ላይቀርብበት ይችላል። በሌላ ሰው በሚጻፈው የሕይወት ታሪክ ግን የሌሎች ሰዎች አስተያየት ታክሎ በሁለት መንገድ ሊዘጋጅ ይችላል። ይኸውም አንድም ግለሰቡ በህይወት እያለ ስለቤተሰቡ፣ ስለ አስተዳደጉ፣ ስለ ትምህርት ደረጃው፣ በሥራ ዓለም ስለ አሳለፈው ጊዜ ራሱ ሲናገር እሱን እንደ ቀዳሚ መረጃ ወስዶ ለእሱ ቅርብ ከሆኑና ቤተሰብ፣ ዘመድና ጓደኞቹን እንደካልዐይ መረጃ /ሁለተኛ ምንጭ/ በመውሰድ ይጻፋል። የሕይወት ታሪክ የሚጻፍለት ባለታሪክ በሕይወት ከሌለ ደግሞ ለእሱ ቅርብ የሆኑትን፣ ትክክለኛ መረጃ ይሰጣሉ ከሚባሉት ሰዎች በመነሳት፣ አንዳንድ የግለሰቡን ሰነድ፣ ግለ ማሕደር በማገላበጥ፣ ስለ ግለሰቡ የተጻፉ ጹሑፎች ካሉም በመሰብሰብ መጻፍ ይቻላል።

እንግዲህ ከእነዚህ በአንዱ መንገድ የሚጻፈው የሕይወት ታሪክ ሳይጋነን፣ ፈጠራ ሳይታከልበት፣ የነበረውንና ያለውን ብቻ በቃላት ከሽኖ ማቅረቡ የሕይወት ታሪክ ጸሐፊው ድርሻ ነው፡፡

> የሕይወት ታሪክ አዘጋጁ የተነጣጠሉ እውነታዎችን ሲሰበስብ ያልቀሰጠውን ብረት በመውሰድ ወደ ወርቅ ስብእና (Personality) ይስውጠዋል፤ ስውጡ ግን ምንም አይነት ኬሚካሳዊ ሂደት ሳይታከልበት በአመርቂ ሁነታ የሚከናወን ነው፡፡[4] (Leon Edel, 1959: 8)

የታዋቂ ሰዎችን የሕይወት ታሪክ መጻፍ ጠቀሜታው ጉልህ ነው፡፡ ታዋቂዎቹ በሕይወት ዘመናቸው ያሳለፉት ውጣ ውረድ ለሥራቸው ምን ያህል አስተዋጽኦ እንዳለው ይታይበታል፡፡ እንደየሙያ መስካቸው ልምድ ያስቀስሙናል፡፡ እነሱን ለመከተል ለሚሻም ከምን እንደተነሱ፣ ምን ምን ነገሮች ለታዋቂነታቸው መነሻ እንደሆናቸው ይገልጽልናል፡፡

የሕይወት ታሪክ እውነተኛ ታሪክ ይዞ ሲቀርብ ግለሰቡ /ባለታሪኩ/ ከሌሎች ሰዎች ጋር ማለትም ከባለቤቱ /ከትዳር ጓደኛው/፣ ከቤተሰቡ፣ ከጓደኞቹና ከዘመዶቹ በአጠቃላይ ለእሱ ከሚቀርቡት ሰዎች ጋር የነበረው /ያለው/ ግንኙነት ተያይዞ ይቀርባል፡፡ በልቦለድም በዋናነት የተጻፈለት ባለታሪክ ይኖራል፡፡ ሌሎች ገጸባህርያት ከእሱ ጋር ባላቸው ግንኙነት የሚገለጹ ናቸው፡፡ ልቦለድና የሕይወት ታሪክ በዚህ ቢመሳሰሉም በሕይወት ታሪክ ግን ፈጠራ አለመታከሉ፣ ጸሐፊው ታሪኩን እንደሻው ለመምራት አለመቻሉ ይለያቸዋል፡፡ ከሚጠቀሙበት መረጃ አኳያም፡-

> ረዥም ልቦለድ /ኖቨል/ ስመጻፍ ጸሐፊውም ምናቡ የደረሰበትን ምንጭ ሁሉ ስመጠቀም ነፃ ነው፤ የሕይወት ታሪክ ስመጻፍ ግን መረጃው ቀድሞ የተወሰነ /የተገደበ/ ነው፡፡ ጸሐፊው ያሰበውን የሚጠቀመው በሰበሰባቸው መረጃዎች እና ጽሑፉን በመቅረጽ ሂደት ብቻ ነው፡፡[5] *(Leon Edel, 1959: 5)*

በአብዛኛው እንደተለመደው የሕይወት ታሪክ የሚጻፈው የታሪኩን ባለቤት መልካም ጎን በማጉላት ነው፡፡ በሕይወት ዘመኑ የፈጸመው ስህተት፣ ወንጀል፣ ኃጢያት በአጠቃላይ ክፉ ስራው አይገለጽም፡፡ የሕይወት ታሪክ ሲጻፍ ባለታሪኩ ካለ እሱን በዋና መረጃነት፤ ቤተሰብ፣ ጓደኞችና ዘመዶቹን በሁለተኛ መረጃነት በመውሰድ ስለሚዘጋጅ ደካማ ጎኑን ለማውጣት አስቸጋሪ ይሆናል፡፡ በመሠረቱ ግን የሕይወት ታሪክ ግለሰቡን መግለጽ እስከ ሆነ ድረስ ባህሪውን በጥልቀት ለማሳየት ደካማ ጎኑም ሊንጸባረቅ ይገባ ነበር፡፡

ሮበርት ካልደር The Life of W. Semerest Maugham (London,1989) በተሰኘው መጽሐፉ የዊልያም ሲመርስትን የሕይወት ታሪክ ሲጽፍ ስቃይ ከተሞላበት ከሕፃንነት ሕይወቱ እስከ እለተ ሞቱ ድረስ ያሳለፈውን ጊዜ፣ የፃፋቸውን መጻሕፍት ዓመተ ምህረት በመጥቀስ በዝርዝር አስፍሯል:: በማስረጃነት የቀረቡ 46 ፎቶዎችም በሦስት ምድብ ተከፍለው ለጽሑፉ ረዳት ሆነው ይታያሉ:: ፎቶዎቹ የማውጋም፣ የቤተሰቡ፣ የጓደኞቹና ከእሱ ጋር ቅርበት ያላቸው የዘመዶቹን ምስል ያመለክታሉ::

ጸሐፊው በመቅድሙ የዊልያምን የሕይወት ታሪክ ለመጻፍ አስራ አራት ዓመት እንደ ፈጀበት ገልጿል:: ሌሎች የዊልያምን የሕይወት ታሪክ በጥቂቱ ጠቃቅሰው የጻፉ ቢኖሩም ጠቅላላ ሕይወቱን ግን ከእሱ በፊት የመዘገበ እንደሌለ ጠቁሟል::

ዊልያም ሰመርስት በዘመኑ ተጓዥ ጸሐፊ፤ የተዋጣለት የቲያትርና የረዥም ልቦለድ ደራሲ እንደ ነበር በመጽሐፉ ተገልጿል:: የባለታሪኩን መጽሐፎች ርዕስም ከተጻፉበት ዘመን ጋር ተጠቅሰዋል::

ዊልያም ፍሪማን ደግሞ የአስራ ስምንት ዝነኛ ሳይንቲስቶችና የፈጠራ ሰዎችን የሕይወት ታሪክ ይዞ በወጣው መጽሐፉ Biographies: Scientists and Inventors (London,1954) ግለሰቦቹ በሕይወት ሳሉ ታዋቂ ያደረጋቸውን ስራና የተወለዱበትና የሞቱበትን ዘመን በመጥቀስ ጽፏል:: ከግለሰቦቹ አንዳንዶቹ የስነጽሁፍ ስራን በተደራቢ ይሰሩ እንደ ነበር ታሪካቸው ያስረዳል::

ጸሐፊው እንደገለጸው ታሪካቸው የተጻፈላቸው ሰዎች በሕይወት ዘመናቸው በዓለም ሳይንስ ውስጥ ታላቅ የፈጠራ ሰዎችና ተመራማሪዎች ነበሩ:: የሕይወት ታሪካቸው በመጽሐፍ የተመዘገቡላቸው ሰዎች የሚጋሩት ሁለት ነገር እንዳለ ዊልያም ገልጿል:: ይኸውም በመጀመሪያ በሕይወት ዘመናቸው የሰሩት ያለፈ ታሪክ እና ሁሉም መጽሐፉ በተዘጋጀበት ዘመን በሕይወት ያልነበሩ ቢሆንም የእነሱ ምርምርና ግኝት ግን የሁሉንም ሰው ሕይወት የሚነካ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ በቦታው በመወለድም ይሁን በመጤነት ሁሉም እንግሊዛዊ ናቸው በማለት አመልክቷል::

## 1.2 የደራሲ ሐዲስ ዓለማየሁን የሕይወት ታሪክ የዳሰሱ ጽሁፎች ቅኝት

የደራሲ ሀዲስን የሕይወት ታሪክ በሙሉ ሳይሆን በጥቂቱ የዳሰሱ መጽሐፎች፣ መጽሔቶች፣ የመመረቂያ ጽሑፉ እና ጋዜጦች አሉ:: እነዚህ ጽሑፎች የደራሲውን

የሕይወት ታሪክ በዝርዝር ያሳዩ አይደሉም። በእኔ ጥናት የተካተቱትን አንዳንድ መረጃዎች ግን ይዘዋል። ጽሑፎቹ ምን ጉዳዮችን እንዳነሱ በሚቀጥሉት አንቀጾች በጭሩ እገልጻለሁ።

Black Lions: The Creative Lives of Modern Ethiopia's Literary Giants and Pioneers. (Dulf K. Molvear, 1997) ይህ መጽሐፍ የ31 ኢትዮጵያውያን ደራስያን የሕይወት ታሪክ የያዘና ስራቸውን ያስተዋወቀ ሲሆን ከእነዚህ ደራስያን አንዱ ሀዲስ ዓለማየሁ ናቸው። ሞልቬር ሀዲስን ለመጀመሪያ ጊዜ ያያቸው እ.ኤ.አ በ1970 ናዝሬት ሶደሬ ሲዝናኑ እንደነበር ገልጾ የሕይወት ታሪካቸውን ከገዛ አንደበታቸው ያገኘው መሆኑን ጠቁሟል። ጸሐፊው ሀዲስን በጥንካሬና በጤንነታቸው ወቅት ስላገኛቸው ዓመተ ምህረት ሳይረሱ ነግረውታል። የሕይወት ታሪካቸውን ከልጅነት እስከ 1966 ዓ.ም ደርግ ለጠቅላይ ሚኒስትርነት እስከጠየቃቸው ጊዜ ያሳለፉት በአጭሩ ቢጽፍም ከደራሲው ሌላ የሚቀርቧቸውን ሰዎች አስተያየት አላካለበትም።

ሞልቬር መፅሐፎቻቸውን ሲያስተዋውቅ በፍቅር እስከ መቃብር ልቦለድ ውስጥ ግለ ሕይወት ታሪክ እንዳለም ጠቁሟል። ይኸውም ቦታዎቹ ደብረወርቅ እና ዲማ ቅኔ የተማሩባቸው አካባቢዎች መሆናቸውን አዲስ አበባ እስኪመጡ ያጋጠማቸው አንዳንድ ነገርም ከዋናው ገፀባህሪ ጋር እንደሚመሳሰል ገልጿል። ከሁለቱ ገጸባህርያት ከበዛብህና ከጉዱ ካሳ ጋር ጥቂት መመሳሰል እንዳላቸው ሲያመለክት ከበዛብህ ጋር፣ ሁለቱም አዲስ አበባ ከመምጣታቸው በፊት የቤተክህነት ትምህርት መማራቸውና ብቸኛ ልጅ መሆናቸውን፣ ከጉዱ ካሳ ጋር ደግሞ በራስ አስተሳሰብ የመመራትና የወቅቱን ስርዓተ ማኅበር በግልጽ መቃወምን በመጥቀስ ጽፏል።

ትዝታ፣ በ1985 ዓ.ም የታተመ የሀዲስ ዓለማየሁ ድርሰት ነው። በዚህ መጽሀፍ ደራሲው በጣሊያን ጦርነት ወቅት የነበረውን ሁኔታና ገጠመኛቸውን አስፍረዋል። ምንም እንኳን ጣሊያን ከኢትዮጵያ ጋር ጦርነት በነበራት ወቅት ያሳለፉትን ውሎ በመጻፋቸው ከሕይወት ታሪካቸው ጥቂቱን ቢገልጹም የአቶ ሀዲስ የሕይወት ታሪክ በዚህ መጽሐፍ ብቻ የተጠቀሰው አይደለም፣ ከጣሊያን ጦርነት በፊትና በኋላ ያሳለፉት ሕይወትም አለና።

'ፍካሬ' መጽሔት 1ኛ ዓመት ቅጽ1፣ ቁ1 የካቲት 1985 ባወጣው እትም «ሐዲስ ዓለማየሁ ከቆሎ ተማሪነት እስከ አርበኝነት» በሚል ርዕስ የተወለዱበትን ዘመንና ቦታ አስተዋውቋል። ሀዲስ የቆሎ ተማሪነታቸውን ጊዜ፣ የጣሊያንን ወረራን ትውስታና

በጣሊያን አገር የእስር ቤት ቆይታቸውን ለመጽሔቱ በሰጡት ቃለ መጠይቅ ባጭሩ ገልጸዋል፡፡ በዚህ መጽሔትም የተጠቀሰው የደራሲው የሕይወት ታሪክ እጅግ ጥቂቱ ነው፡፡ በሥራው ዓለም ያሳለፉትና የትዳር ሕይወታቸውን እንዲሁም ለአገሪቱ ያበረከቱት አስተዋጽኦ በሙሉ አልተጻፈም፡፡

የህዲስን የሕይወት ታሪክ እጅግ ባጭሩ ከሌሎች ጉዳዮች ጋር በማያያዝ የጻፈው ሁለተኛው መጽሔት መስከረም 1992 ዓ.ም የወጣው 'ፈርጥ' መጽሔት ቅጽ 4 ቁጥር 2 ነው፡፡ ይህ መጽሔት «ህዲስ እንደ አዲስ» በሚል ርዕስ ሥር ባሰፈረው ጽሑፍ ጳጉሜ 5/1991 ዓ.ም ሜጋ ኪነጥበባትና ማስታወቂያ ድርጅት እና ሜጋ አሳታሚ ድርጅት በጋራ «ዝክረ ሥንክን» በሚል ስያሜ በደራሲ ህዲስ ዓለማየሁና ሥነጽሑፋዊ ሥራዎቻቸው ላይ ያተኮረ ዐውደ ጥናት አዘጋጅተው እንደ ነበር ገልጿል፡፡ ነሐሴ 26/1999 ዓ.ም በመኖሪያ ቤታቸው በመገኘት የፈርጥ መጽሔት ዝግጅት ክፍልም ዐውደ ጥናቱን በተመለከተ የተሰማቸውን ጠይቆ ምላሹን በመጽሔቱ አስፍሯል፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሐምሌ 2/1991 ወስኖ ነሐሴ 27/1991 ዓ.ም በመኖሪያ ቤታቸው ተገኝቶ የክብር ዶክትሬት እንደሰጣቸውም ጠቅሶ ስለ ፍቅር እስከ መቃብር ያላቸውን አስተያየትም ገልጿል፡፡ ከትዝታ መጽሐፋቸው ውጭ ስለራሳቸው ታሪክ የጻፉት እንደሌለ ጠቁሞ የተወለዱበትን ቦታና ዘመንም አመልክቷል፡፡

'አዲስ ዘመን ጋዜጣ' በሦስት ተከታታይ ሳምንታዊ እትሞች ህዲስ ዓለማየሁን በተመለከተ ዘግቧል፡፡ ጋዜጣው መስከረም 8 ቀን 1992 ዓ.ም ለንባብ ባበቃው ኪነጥብብና ባህል አምድ ሥር 'አገራቸውን በሁለንተናዊ መልኩ ያገለገሉ ታላቅ ሰው' በሚል ርዕስ የህዲስን የሕይወት ታሪክ በመጠኑ ገልጿል፡፡ ደራሲው ለንጉሥ ኃይለ ስላሴ በ1953 ዓ.ም ከጻፉላቸው ልዩ ማስታወሻ ላይም በጥቂቱ ጠቅሷል፡፡

መስከረም 15 ቀን 1992 ዓ.ም በወጣው እትም ደግሞ ትዝታ ከተባለው መጽሐፋቸው የጣሊያንን ወረራ አስመልክተው የጻፉትን በቀጥታ ገልብጦ በጋዜጣው ላይ አስፍሯል፡፡ በማጠቃለያው የህዲስ ብዕር መሠረታዊ እና ዘላቂነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ የሚያነጣጥር የእውነተኛ ዜጋ ብዕር መሆኑን ገልጾ የጣሊያን ወረራ ከአሁኑ የኢትዮጵያና ኤርትራ ግጭት ጋር የሚያመሳስለው ነገር እንዳለም ጠቁሟል፡፡

መስከረም 22 ቀን 1992 ዓ.ም ይኸው 'አዲስ ዘመን' ጋዜጣ 'አርአያነታቸው የሚመረጥ የተከበሩ ዜጋ ሐዲስ ዓለማየሁ' በሚል ርዕስ ካለፈው ሳምንት የቀጠለ ሦስተኛ ክፍል ይዟ ወጥቷል፡፡ በዚህ ጋዜጣ ላይ የደራሲው ስራ የፍቅር እስከ መቃብርን

የሕትመት ሂደት ገልጸ ልቦለዱ በገጸባህርያቶቹ ወጥ ጠባይና በታሪክ አካሄዱ ሲታይ ከግል ታሪካቸው ጋር እንደሚመሳሰል ግምት መኖሩን ይጠቅሳል። ደራሲው ስራዎቻቸውን በተመለከተ ሰዎች የሚሰጧቸው አድናቆት የሚበዛባቸው መሆኑን፣ በተሰጣቸው የኃላፊነት ሥራዎችም ሆነ በድርሰቶቻቸው ግን ለአገራቸው ትንሽ አስተዋጽኦ ማበርከታቸውን በተደረገላቸው ቃለ መጠይቅ መግለጻቸውን ጋዜጣው አመልክቷል።

አደፍርስ አድማሱ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ክፍል ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ በ1980 ዓ.ም ያቀረበው የጥናት ጹሑፍ «የኢትዮጵያ ልቦለድ ዐበይት ደራስያን አጭር ዜና ሕይወት» የሚል ርዕስ ይዟል። አደፍርስ በጥናቱ አስራ አንዱን ዋና ዋና የልቦለድ ደራስያን በሁለት ዘመን መድቧቸዋል። አንደኛው ከ1900-1933 ዓ.ም ሲሆን፤ በዚህ ዘመን አፈወርቅ ገብረየሱስንና ኅሩይ ወልደስላሴን ሲጠቅስ፤ በሁለተኛው ምድብ የስማቸው ዝርዝር የተጻፈው ደግሞ ከ1933-1966 ዓ.ም ግርማቸው ተክለሃዋርያት፣ መኮንን እንዳልካቸው፣ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ፣ መኮንን ዘውዴ፣ መንግስቱ ገዳሙ፣ ብርሃኑ ዘርይሁን፣ አቤ ጎበኛ፣ ሀዲስ ዓለማየሁና በዓሉ ግርማ ናቸው።

አጥኚው የአስራ አንዱን ደራስያን የሕይወት ታሪክ በመጠኑ ሲጠቃቅስ የደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁን የሕይወት ታሪክም የተወለዱበትን ዓመተ ምህረት 1906 በማለት የት እንደተማሩ፣ የት የት እንደሰሩ ከጠቀሰ በኋላ መጽሐፎቻቸውን አስተዋውቋል። በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ አቶ ሀዲስ ዳንግላ የራሳቸውን ትምህርት ቤት ከፍተው እንደነበር ተገልጿል። ይህ ግን ባለታሪኩን ጠይቄ እንደተረዳሁት ትምህርት ቤቱ የራሳቸው ሳይሆን በአስተዳዳሪነትና በመምህርነት ያገለገሉበት ነበር።

ከላይ የዘረዘርኳቸው መጽሐፎች፣ መጽሔቶች፣ የጥናት ጽሑፍና ጋዜጦች ያሰፈሯቸውን፣ በስፋት ያልገለጿቸውንና ፈጽሞ ያላነሷቸውን የደራሲውን ሕይወት የሚመለከቱ ቁም ነገሮች በዚህ ጥናት የሕይወት ታሪክ ክፍል ተካትተዋል። እነዚህ ጽሑፎች የደራሲው የሕይወት ታሪክ ከስነ ጽሑፍ ስራዎቻቸው ጋር ያለውን ዝምድና ትኩረት ሰጥተው አላሳዩም። የእኔ ጥናት ዋና ዓላማ በተለያዩ ጽሑፎች አልፎ አልፎ የተነካካውን የደራሲውን የሕይወት ታሪክ በወጥነት ባለታሪኩን በዋና መረጃነት በመውሰድ እያመሳከሩ መጻፍና ከሕይወት ታሪካቸው ጋር ያለውን ቁርኝት ማመልከት ነው።

## 1.3 በደራስያን የሕይወት ታሪክና የስነጽሑፍ ስራዎቻቸው ላይ የተሰሩ ጥናታዊ ጽሑፎች ቅኝት

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ከቀረቡት ጥናቶች በደራስያን የሕይወት ታሪክና ስነጽሑፍ ስራዎች ላይ የተሰሩት ከሌሎች ጥናቶች ጋር ሲወዳደሩ ቁጥራቸው አናሳ ነው:: የቁጥራቸው ማነስ እንዲህ አይነት ስራ አለመለመዱን ይጠቁማል:: እስከ 1991 ዓ.ም ድረስ በዚህ ርዕስ ዙሪያ በቤተመጻሕፍት ውስጥ የተገኙ ሃያ ሰባት ናቸው:: የጥናት ጽሑፎች በረዥም ልቦለድ፣ ግጥም እና አጭር ልቦለድ ደራስያን የሕይወት ታሪክና ሥራዎቻቸው ላይ የተሰሩ ናቸው:: በተውኔት ደራሲያን የሕይወት ታሪክና ስራዎቻቸው ላይ የተሰሩት ሲታከሉ ቁጥራቸው ወደ ሰላሳ ሦስት ከፍ ይላል::

በ1960ዎቹ መጀመሪያ በሕይወት ታሪክ ላይ ብቻ የተሰሩት የጥናት ጽሑፎች ርዕሳቸው የደራሲያን የሕይወት ታሪክ ይሁን እንጂ የባለታሪኮቹን የስነጽሁፍ ስራም የዳሰሱ ናቸው:: እነሱን ለማስቃኘት ርዕሴ ባይፈቅድም ከእኔ ጥናት ጋር ጥቂት መቀራረብ አላቸውና በምሳሌነት አንዱን እጠቅሳለሁ:: በ1962 ዓ.ም «የነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ አጭር የሕይወት ታሪክ» በሚል ርዕስ በጥጋቤ አስረስ የቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ የነጋድራስ ገብረሕይወትን የሕይወት ታሪክ ከማስነበብ በተጨማሪ ደራሲው የጻፏቸውን <u>አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ</u> እና <u>የመንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር</u> የተባሉት መጽሐፎች ያነሱትን ጉዳይ አጥኚው አመልክቷል:: ከሞላ ጎደል በይዘት ከመለያየታቸው በቀር በአቀራረባቸው በደራሲያን የህይወት ታሪክ ላይ ብቻ የተሰሩት ሌሎች ጥናቶችም ተመሳሳይ ናቸው:: ጥናቱ የተካሄደባቸው ባለታሪኮች ጽሁፉ በተዘጋጀበት ወቅት በሕይወት አልነበሩምና ከልደት እስከ ሞት ያሳለፉት ኑሮ ተጽፎላቸዋል::

በደራሲያን የሕይወት ታሪክና የስነጽሑፍ ስራዎች ላይ ወደ ተሰሩት የመመረቂያ ጽሑፎች ስናመራ፤ በ1970ዎቹ በዚህ ርዕስ ዙሪያ በርካታ ጥናታዊ ጽሑፎች የቀረቡ ሲሆን በ1979ዓ.ም ብቻ ዘጠኝ ተሰርተዋል:: በላይ ሰይድ «ደራሲ ገበየሁ አየለና የስነ ጽሑፍ ስራዎቹ» በሚል ርዕስ በ1987 ዓ.ም ባቀረበችው የጥናት ጽሁፍ ክለሳድርሳን በእሷ ጥናት ርዕስ ዙሪያ ከተሰሩት የመመረቂያ ጽሑፎች ሰባቱን አስተዋውቃለች:: አጥኚዎቹ ከጥናት ፅሁፋቸው ርዕስ ጋር የሚከተሉት ናቸው:: አያና ካሣሁን «ብርሃኔ ጉቻለወርቅና የስነጽሑፍ ስራዎቹ» በ1979፣ ሰይፉ ስማ «ደራሲ ስብሐት ገብረ እግዚአብሔርና የስነጽሑፍ ስራዎቹ በ1979፣ ዳንኤል ፋንታ አተሮ «ደራሲ አበራ ለማና

የስነ ጽሑፍ ስራዎቹ» በ1979፣ ሀይሉ ተሰማ «የደራሲ ሙላቱ ገብሩ የስነጽሑፍ ስራዎች» በ1979፣ ዘሪሁን ግርማ «ደራሲ መኮንን ዘውዴና የልቦለድ ስራዎቻቸው» በ1979፣ ደመላሽ ዓለሙ «ኃይለስላሴ ደስታና የድርሰት ስራዎቹ» በ1979 እና በላቸው ወርቁ «ደራሲ ማሞ ውድነህና የስነጽሑፍ ስራዎቹ» በ1980

በ1976 የስንዱ ገብሩ፣ በ1979 የብላታ ወልደጊዮርጊስ ወልደዮሐንስ፣ በ1979 የጳውሎስ ኞኞ፣ በ1981 የመንግስቱ ለማ፣ በ1984 የዓለማየሁ ሞገስ እና በ1987 የገበየሁ አየለን የሕይወት ታሪክና የስነጽሑፍ ስራዎች እንደ ደራሲዎቹ የስም ቅድም ተከተልና ጥናቱ የተዘጋጀበት ዘመን በፍሬህይወት አሰፋ፣ ፈቃደ አደራ፣ ጌታቸው ታፈሰ፣ ወንድወሰን በየነ እና በላይ ሰይድ የተሰሩ ናቸው:: እነዚህ ከላይ ጥናቱ የተካሄደባቸውን ደራሲዎችና የአጥኚዎቹን ስም በመጥቀስ የዘረዘርኳቸውን ስድስቱን የጥናት ጽሑፎች ደምስ አላምረው በ1988 ዓ.ም የደራሲ አውግቸው ተረፈን የሕይወት ታሪክና የስነጽሑፍ ስራዎች ባቀረበበት የመመረቂያ ጽሑፍ ክለሳ ድርሳን አመልክቷል::

ዓለማየሁ ግርማ« አስፋው ዳምጤና የስነጽሑፍ አበርክቶዎቹ» በሚል ርዕስ በ1988 ዓ.ም ባቀረበው የጥናት ጽሑፍ ደግሞ የክንፈ ኃይሉ 1963 «የነጋድራስ ተሰማ እሸቴ አጭር የሕይወት ታሪክና ግጥሞቻቸው»፣ የደመላሽ ዓለሙ 1984 «አቶ ዓለማየሁ ሞገስና የስነጽሑፍ ስራቸው» እና የወርቁ መንገሻ 1980 «የያሬድ የሕይወት ታሪክና ስራዎቹን በክለሳ ድርሳን ምዕራፍ አስተዋውቋል::

በዚህ ጽሁፍ ከላይ የጠቀስኳቸው ቀደምት አጥኚዎች በተዛማጅ ጽሑፋቸው ያልጠቀሷቸውን አምስቱን የጥናት ጽሑፎች ለማስቃኘት ተሞክሯል:: ከአምስቱ ጥናቶች ሁለቱ በገጣምያን ሦስቱ ደግሞ በዝርው ጸሐፍያን የሕይወት ታሪክና ስራዎቻቸው ላይ የተሰሩ ናቸው:: በእነዚህ ጥናታዊ ጸሑፎችና በእኔ ጥናት መካከል ያለውን ተመሳስሎና ልዩነት እንዲሁም ድካምና ጥንካሬ ከማመልከቴ በፊት እያንዳንዳቸው ያነሱትን እንደሚከተለው እገልጻለሁ::

በ1975 ዓ.ም በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ከቀረቡት የጥናት ጽሑፎች አንዱ በተድላ ወልደስላሴ «የበእምነት ገብረአምላክ የሕይወት ታሪክና ልጅነት ተመልሶ አይመጣም» በሚል ርዕስ የተዘጋጀው ነው:: ይህ ጥናት ሦስት ምዕራፎችን ይዟል:: የመጀመሪያው ምዕራፍ የበእምነት ገብረአምላክ የጊዜ ዳራ በሚል በሁለት ክፍል የቀረበ ሲሆን ፤ አንደኛው ደራሲው የነበሩበትን የወቅቱን የስነፅሑፍ አዝማሚያ ሲጠቁም፣

ሁለተኛው ደግሞ ልጅነት ተመልሶ አይመጣም የተጻፈበትን ዘመን፣ በእምነት ገብረአምላክ የነበሩበትን የጊዜውን፣ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታዎች ያመለክታል።

በሁለተኛው ምዕራፍ የበእምነት ገብረ አምላክን አጭር የሕይወት ታሪክ፣ የተወለዱበት፣ አካባቢ፣ ወደ ደራሲነት ያመሩበት ዓብይ ምክንያት እና በእምነት በጓደኞቻቸው አይን በሚል ሦስት ንኡሳን ክፍሎች ቀርቦበታል። ሦስተኛው ምዕራፍ የደራሲው መጽሐፍ የሆነው የልጅነት ተመልሶ አይመጣምን አብይ ጭብጥ በመወዋቅሩ (በሴራው) ውስጥ የተቀነባበሩት ታሪኮች ያላቸው የርስ በርስ መያያዝ ፣ የገጸባህርያት እውቂያና አሳሳል፣ ደራሲው የተጠቀሙባቸው ዘይቤአዊ አነጋገሮች በልቦለዱ ውስጥ የታዩ ድክመቶች እና በመጨረሻም በመጽሐፉ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉ የዘይቤአዊ አነጋገሮችን ስብስብ የያዘ ነው።

ተድላ፣ ልጅነት ተመልሶ አይመጣም የተባለውን የደራሲውን መጽሐፍ ከተቸ በኋላ «ለዛሬው ትውልድ የምትሰጠው አገልግሎት ቢኖር በዚያን ወቅት የስነጽሑፍ የእድገት ደረጃና አጠቃላይ ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለሚሻ ልታገለግል የምትችልበት ሁኔታ ይኖራል» በማለት ስለ መጽሐፉ ያለውን አስተያየቱን አስፍሯል። ደራሲው ሌሎች ትርጉምና ያልታተሙ ጽሑፎች እንዳላቸው ቢጠቁምም ርዕሳቸውን ግን አልጠቀሰም።

አዳነ ታዳገ «ሻምበል ክፍሌ አቦቸርና የግጥም ሥራዎቹ» በሚል ርዕስ በ1979 ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ባቀረበው ጥናት የመጀመሪያ ምዕራፍ የሻምበል ክፍሌ አቦቸርን የህይወት ታሪክ በሦስት ክፍል ገልጾታል። አንደኛው ክፍል ክፍሌን ለገጣሚነት የኮተኮተው የሕይወት ዳራ፣ ወደ ውትድርና ከመግባቱ በፊትና ከእዛ በኃላ ያሳለፈውን ሕይወት ያስነብባል። በመግቢያውም እንዳመለከተው የገጣሚውን ሙሉ የሕይወት ታሪክ በመዘገብ ሳይሆን ለገጣሚነት ብቃት ያደረሰውን የኑሮ ገጠመኝ ብቻ ጽፏል። የመጀመሪያው ምዕራፍ ሁለተኛ ክፍል የገጣሚው የፈጠራ ሥራ እንቅስቃሴ መነሻ አጋጣሚዎችና የትና እንዴት እንደሚጽፍ የሚገልጽ ነው። በዚህ ክፍል ክፍሌ ለታዋቂ ዘፋኞች ለጥላሁን ገሠሠ፣ ለሂሩት በቀለ፣ ለጌታቸው አስፋውና ለታምራት ሞላ አብዮታዊ የሆኑና አብዮታዊ ያልሆኑ ዜማና ግጥሞች ሰጥቶ እንደነበር ጠቅሷል።

ክፍሌ የገጣሚነት ሙያው በሚል በሦስተኛው ክፍል ጸሐፊው ለሥነግጥም ያለውን አመለካከት፣ በገጣሚነት ያበረከተውን አስተዋጽኦ እና በገጣሚነት ሙያው ያሳየውን ቅጽበታዊ እድገት አመልክቷል። አዳነ ታደገ «ክፍሌ በማርክሳዊ ሌኒናዊ ንድፈ ሃሳብ

ራሱን በማስታጠቅ የሥነ ግጥም ሙያውንም በዚያው መሠረት ገንብቶ በማነጽ የሶሻሊስት እሙናዊነትን ፈለግ ለመከተል የሚጥር ወገናዊ ገጣሚ ነው» ይላል:: ስለገጣሚው አስተያየት እንዲሰጡት የጠየቃቸው ብዙ ምሑራን በቅርብ የተነሳ ገጣሚ በመሆኑ አስተያየት ለመስጠት እንደተቆጠቡ ገልጾ ፈቃደኛ የሆኑትን የአሰፋ ገብረ ማርያም፣ ማሞ ውድነህና አማረ ማሞን አስተያየት በጥናቱ አስፍሯል::

በሁለተኛው ምዕራፍ የክፍሌ የግጥም ሥራዎች ከይዘታቸውና ከቅርጻቸው አኳያ ተተንትነዋል:: የግጥሞቹ ይዘት የሶሻሊስት እሙናዊነትን ፈለግ የተከተሉ እንደሆኑ ጠ ቁሞ ቅርጻቸውንም የሐሳብ ግጥም ግጥምነት፣ የቃላት አጠቃቀም፣ የዘይቤ አጠቃቀምና አስነኘነት በሚል አመልክቷል:: አዳነ የክፍሌን አብዮተኛነት በጥናቱ መግቢያ፣ በዋናው ክፍልና በማጠቃለያው ደጋግሞ ሲገልጽ፤ በመግቢያው ተጠቅሶ በዋናው ጽሑፍ ግን ያልተገለጸ አንድ ጉዳይ አለ:: ይኸውም የገጣሚው የሕይወት ታሪክና ግጥሞቹ ያላቸው ቁርኝት አለመታየት ነው:: የገጣሚው የሕይወት ታሪክና ግጥሞቹ ግን በተናጠል ተገልጸዋል::

«የሠዓሊ ገብረክርስቶስ ደስታ የሕይወት ታሪክና አንዳንድ ግጥሞቹ» በብርሃነ መስቀል ደጀኔ በ1982 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል የቀረበ ጥናት ነው:: ይህ የጥናት ጽሑፍ ሦስት ምዕራፎችን የያዘ ሲሆን፤ በመጀመሪያው ምዕራፍ በሠዓሊ ገብረ ክርስቶስ ደስታ የሕይወት ታሪክ እና በግጥሞቻቸው ላይ የተሰሩ ቀደምት ጥናቶችን ጠቅሶ ድክመትና ጥንካሬያቸውን አሳይቷል:: በቀጣዩ ምዕራፍ የገብረ ክርስቶስን የሕይወት ታሪክ ገልጿል:: የጥናት ጽሑፉ በተዘጋጀበት ወቅት ባለታሪኩ በሕይወት ባለመኖሩ አጥኚው የሕይወት ታሪኩን ለመስራት መሠረት ያደረገው ሠዓሊውን የሚያውቁ ሰዎችን በማነጋገርና ያልታተሙ የጽሑፍ መረጃዎችን በማሰባሰብ መሆኑን በመግቢያው ላይ ጠቅሷል:: የሕይወት ታሪኩ በተጻፈበት ምዕራፍ የገጣሚው የቤተሰብ ታሪክ፣ የልጅነት አስተዳደግ፣ የትምህርት ዘመን፣ የሠዓሊነት፣ የመምህርነትና የገጣሚነት ሕይወቱ እንዴት እንደ ነበር በሰፊው ተገልጿል:: በዚህ ክፍል ሠዓሊና ገጣሚው ገብረ ክርስቶስ በሕይወቱ ወስጥ ላጋጠሙት አንዳንድ ሁነቶች ለምሳሌ አባቱ ሲሞቱና በውጭ ሳለ የገጠማቸው አንዳንድ ግጥሞች ስፍረዋል::

በሦስተኛው ምዕራፍ የገብረክርስቶስ የገጣሚነት ሰብእናና የግጥሞቹ ይዘትና ቅርጽ ትንተና ቀርቧል:: የግጥሞቹን ይዘት የነፃነት ስሜት፣ ጥበብ፣ ሕይወትና ሞት፣ የሴት ፍቅርና ብሔራዊ ስሜት በሚል ከፋፍሎ የግጥሞቹን ቅርጽ ደግሞ ከቃላት አመራረጥ፣ ምስል አፈጣጠርና አሰነኛኘት አንጻር አመልክቷል:: የገብረ ክርስቶስ ሠዓሊነት

በግጥሞች እንደተንጸባረቁና የሕይወት ታሪኩንም እንደገለጹም ከግጥሞቹ ይዘት ትንተና በኋላ ጠቅሷል።

የጥናታዊ ጽሁፉ ማጠቃለያ የሆነው ክፍል ገብረክርስቶስ ደስታ በግጥምም ሆነ ስዕል የተዋጣለት እንደሆነና ሕይወቱን ለጥበብ ሙያ ያዋለ ጠቢብ መሆኑን አስረድቷል። በመጨረሻ ገጾቹም የገጣሚው ጥቂት ግጥሞችና ስዕሎቹ እንዲሁም በሌሎች ሰዎች የተገጠሙለት አንዳንድ ግጥሞች ቀርበዋል።

በቅርብ ጊዜ በደራሲያን የሕይወት ታሪክና ስነጽሑፍ ከተሰሩት ጥናታዊ ጽሑፎች አንዱ በ1988 ዓ.ም የደምስ አላምረው «ደራሲ አውግቸው ተረፈና የስነጽሑፍ ሥራዎች» የሚል ርዕስ የያዘው ነው። ጥናቱ በሦስት ምዕራፎች ተከፍሏል። የመጀመሪያው ምዕራፍ የሕይወት ታሪክ ነቢባዊ ክለሳ፣ የሕይወት ታሪክ ዓይነቶች እና የቀደምት ጥናቶች ቅኝት የቀረበበት ክለሳ ድርሳን ነው። በቀጣዩ ምዕራፍ የደራሲ አውግቸው የሕይወት ታሪክ ከልጅነት ጥናቱ እስከተካሄደበት ያሳለፈው ኑሮ ተገልጾበታል። አውግቸው ደራሲ ብቻ ሳይሆን ተርጓሚም እንደ ነበር ለዚህም ያነሳሳው ምክንያትና የስነጽሑፍ አመለካከቱ ምን እንደሆነ ተጠቅሷል።

ደምስ አላምረው በጥናቱ መጨረሻ ምዕራፍ የአውግቸው ተረፈ የህይወት ታሪክና የስነ ጽሑፍ ሥራዎቹን ዝምድና ገልጿል። የአውግቸው አጭር ልቦለድ የሆነው የወይ አዲስ አበባ ታሪክ የራሱ የደራሲው የሕይወት ታሪክ መሆኑን በማዛመድ አሳይቷል። ሌሎች የደራሲው አጭር ልቦለዶች ከሕይወት ታሪኩ ጋር ያላቸውን ግጥምጥምነትም አመልክቷል። በማጠቃለያው አውግቸው በመጽሐፉ ከቀረቡት አጭር ልቦለዶቹ በተጨማሪ በመጽሔትና በጋዜጣ ላይም የጻፋቸው ልቦለዶች እንዳሉ ጠቁሞ፤ በደራሲነት ብቻ ሳይሆን በተርጓሚነትም ታዋቂ መሆኑን ጠቅሷል።

በ1988 ዓ.ም ከተሰሩት ጥናታዊ ጽሑፎች ሁለት ተመሳሳይ ርዕሶች አንዱ ከላይ ለማሳየት የሞከርኩት የደምስ አላምረው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የዓለማሁ ግርማ የአቶ አሰፋው ዳምጤን የሕይወት ታሪክና የስነ ጽሑፍ አበርክቷቸውን የሚገልጸው ጥናት ነው። የዓለማየሁ ጥናት በአራት ምዕራፎች ቀርቧል። በመጀመሪያው ምዕራፍ በክለሳ ድርሳን የህይወት ታሪክን ምንነትና የደራሲን ማንነት ገልጾ ጥቂት ቀደምት የጥናት ጽሁፎችንም አስቃኝቷል። በሁለተኛው ምዕራፍ የደራሲው ታሪክ በግል ትውስታ በሚል ርዕስ የደራሲው የልጅነት ጊዜ፣ በጥቁር አንበሳ፣ ኮከበጽበህ እና በኃላም በዩኒቨርስቲ ኮሌጅ ያሳለፉትን የትምህርት ዘመናት እና የስራ ዓለም ቆይታቸውን በስፋት ገልጿል።

ዓለማየሁ በጥናቱ ሦስተኛ ምዕራፍ አቶ አስፋው አንድ ለአምስት የተባለ ረዥም ልቦለድ ከመጻፋቸው በተጨማሪ እነሆ የሚል ርዕስ የያዘ የአጫጭር ልቦለዶች መድበል ማሳተማቸውን ጠቅሷል:: በየመጽሔትና ጋዜጦች ላይ በተለያዩ ጊዜያት የጻፏቸውን የጽሁፍ አይነቶች በየርዕሳቸው ከፋፍሎ ስለ እያንዳንዳቸው ያነሷቸውን ሃሳቦች አቅርቧል:: በሃያሲነታቸው የታወቁ እንደመሆናቸው ይህንኑ አስመልክቶ የጻፉትንም በጥናቱ አስፍሯል:: በመጽሔት ለንባብ ካበቋቸው ሰባት አጫጭር ልቦለዶች በደራሲው አጠራር «እንጎቻ ወጎች» ሁለቱን «ዘጠነኛው ዶሴ»ና «ቦዩ» የተሰኙትን ለአብነት በመውሰድ ታሪካቸውን በአጭሩ አስተዋወቆ ከልቦለድ አላባውያን አንጻር ገምግሟቸዋል::

በመጨረሻው ምዕራፍ የአቶ አስፋው የህይወት ታሪክ ከአንድ ለአምስት መጽሐፋቸው ጋር ያለውን ዝምድና ከመጽሐፉ ጭብጥ፣ ከገጸባህርያት አካላዊ መመሳሰል፣ በታሪክ መገጣጠምና ከአምልኮ ስርዓት አንጻር አሳይቷል:: አጥኚው የአምልኮ ስርዓት የሚላቸው ደራሲው በመጽሐፋቸው የገለጿቸው ባህላዊ አምልኮዎች ናቸው:: እነዚህ ባህላዊ አምልኮዎች ገጸባህሪያት ወደፊት ይደርሳሉ ብለው የተነበይዋቸው በእውን ሲፈጸሙላቸው በመጽሐፉ ተገልጿል:: በደራሲው ህይወትም የተተነበዩት ሲደርሱ እንደታዩ ዓለማየሁ ጠቅሷል:: አቶ አስፋው አንድ ረዥም ልቦለድ ሰባት ያህል አጫጭር ልቦለዶችን በርካታ የጥናት ጽሁፎችን በማቅረብ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ሲል ጥናቱን አጠቃሏል::

ከዚህ በላይ የገለጽኳቸው የጥናት ጽሁፎችን ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው አብይ ጉዳይ ሁሉም በደራሲያን የህይወት ታሪክና ስራዎቻቸው ላይ መስራታቸው ነው:: ብርሃነ መስቀል ደጀኔና አዳነ ታደገ ባቀረቡት የጥናት ጽሁፍ ባለታሪኮቹ ገጣምያን ሲሆኑ የቀሩት ሦስቱ ባለታሪኮች ግን የረዥም ልቦለድና የአጭር ልቦለድ ደራሲያን ናቸው:: ዝርው ጸሀፊያን ናቸው:: አዳነ ታደገ የሻምበል ክፍሌን የሕይወት ታሪክና የግጥም ስራዎቹን በተናጠል ሲያሳይ ጥምረታቸውን ግን አልገለጸም:: ተድላ ወልደ ስላሴ አብርሃም «የበእምነት ገብረ አምላክ የሕይወት ታሪክና ልጅነት ተመልሶ አይመጣም» በሚል ርዕስ ባቀረበው ጥናት የደራሲውን የሕይወት ታሪክ የነበሩበትን ዘመን የስነ ጽሁፍ አመለካከትና መጽሀፋቸውን ከመተቸት በቀር የሕይወታቸውን በድርሰቶቻቸው መገለጽ፣ አለመገለጽ አልጠቆመም::

የደምስ አላምረውና የዓለማየሁ ግርማ ጥናታዊ ጽሁፎች በዘመን ብዙ ያልራቁ በስራቸውም የደራሲያኑን የሕይወት ታሪክ ከድርሰቶቻቸው ጋር በማዛመድ ከእኔ ጥናት

ጋር የሚመሳሰሉ ናቸው። በተለያዩ ደራሲዎች ላይ እንደመስራታችን በይዘት ስንለያይ በአጻጻፍ ስልታችን ግን እንቀራረባለን። ሁለቱም የደራሲያኑን የሕይወት ታሪክ ከልደት ጥናቱ እስከቀረበበት ዓመት ያሳለፉትን ህይወት አስነብበው፣ ስራዎቻቸውንም አስተዋውቀው በመጨረሻ የደራሲያኑ የሕይወት ታሪክ በድርስቶቻቸው መንጸባረቃቸውን አመልክተዋል። የእኔን ስራ ከዓለማየሁ የሚለየው የደራሲውን ስራዎች በዝርዝር አለማየቴ ነው። የአለማየሁ ጥናት የአቶ አሰፋውን ዕሁፎች በሙሉ ካስተዋወቀ በኃላ ደራሲውን ከአንድ ለአምስት መጽሀፋቸው ጭብጥ፣ ከገጸባህሪያት አካላዊ መመሳሰል፣ ከታሪክ መገጣጠምና ከአምልኮ ስርዓት ጋር ያላቸውን ዝምድና ሲያትት የእኔ ጥናት ግን ከደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁ ሰባት መጽሀፎች ሦስቱን ረዥም ልቦለዶች በመምረጥ ከአራቱ ዋና ገጸ ባህርያት /ከበዛብህ፣ ጉድካሳ፣ በሻህና ጥላሁን ጋር ያላቸውን ተመሳስሎ ለማመልከት ይሞክራል።

ከላይ በቅኝት መልክ የቀረቡት አምስቱ የመመረቂያ ጽሁፎች ርዕሳቸው እንደሚያመለክተው የደራስያንን የህይወት ታሪክ ከስራዎቻቸው ጋር የያዙ ናቸው። የህይወት ታሪክ አጻጻፋቸውን ስንመረምር ግን ከፊሎቹ ለአጻጻፉ ትኩረት የሰጡት አይመስሉም። የብርሃነ መስቀል ደጀኔ «የሠዐሊ ገብረክርስቶስ ደስታ የህይወት ታሪክና አንዳንድ ግጥሞቹ»፣ የዓለማየሁ ግርማ «አስፋው ዳምጤና የስነ ጽሁፍ አበርክቶዎቹ» እና የደምስ አላምረው «ደራሲ አውግቸው ተረፈና የስነጽሑፍ ስራዎቹ» የጥናት ጽሁፎች የየደራሲዎቹን የሕይወት ታሪክ በማስረጃ ደግፈው ያቀረቡ ናቸው። ደራሲዎቹ ከውልደት ጥናቱ እስከተዘጋጀበት ወይም እስከሞቱበት ድረስ ያሳለፉትን ሕይወት በቅደም ተከተል በማቅረብ ማንነታቸውን በበቂ አስተዋውቀዋል።

የሠዐሊና ገጣሚ ገብረክርስቶስ የሕይወት ታሪክና ስራዎቹ በቀረበበት የብርሃነ መስቀል የመመሪቂያ ጽሑፍ ጥናቱ ሲዘጋጅ ገጣሚው በሕይወት አልነበሩም ስለሆነም አጥኚው የሕይወት ታሪክ ለመጻፍ መሰረት ያደረገው በቅርቡ የሚያውቋቸውን ዘመዶቻቸውንና ጓደኞቻቸውን ነው። በተለያዩ ጊዜያት ስለ ደራሲው የተጻፉት መጽሔቶች፣ ጋዜጦች፣ መጽሀፍና በሰዓሊው የተዘጋጁ የስዕል ኤግዚብሽኖችም በመረጃነት አገልግለዋል። በተጨማሪም የባለታሪኩ ግጥሞች የሕይወት ታሪኩ በተጻፈበት ምዕራፍ የተገጠሙበት ጊዜ ተገልጿል። ብርሃነ መስቀል እነዚህን ማስረጃዎች በመጠቀሙ ደራሲውን በማስተዋወቅ የተጨበጠ ሃሳብ ሰጥቷል።

የደምስ አላምረውና የዓለማየሁ ግርማ ጥናቶችም ከባለታሪኩ ተነስተው ሌሎች በቅርብ የሚያውቋቸው ሰዎችንም በመጠየቅ የየደራሲዎቹን የህይወት ታሪክ ዘግበዋል።

ምንም እንኳን የጥናት ጽሁፋቸውን ባዘጋጁበት ወቅት ደራስያኑ በሕይወት ቢኖሩም የሕይወት ታሪካቸውን ለመጻፍ የደራሲያኑ ቃል ብቻ በቂ ባለመሆኑ ስለደራሲዎቹ ያውቃሉ የተባሉትን ዘመዶችና ጓደኞቻቸውን ቃልም በጽሁፍ ማስፈራቸው ግድ ነው:: የደራሲዎቹ የሕይወት ታሪክ ከስራዎቻቸው ጋር ያለውን ጥምረት ለማሳየትም ድጋፍ ሆኗቸው::

በአንጻሩ ደግሞ ተድላ ወልደ ስላሴ «የበእምነት ገብረ አምላክ የሕይወት ታሪክና ልጅነት ተመልሶ አይመጣም» በሚል ርዕስ ያዘጋጀው የጥናት ጽሁፍ በርዕሱ እንደጠቆመው የደራሲውን የሕይወት ታሪክ አልገለጸም:: ይህን ለማለት ያስደፈረኝ አጥኚው የደራሲውን የሕይወት ታሪክ በተመለከተ የተለያዩ ሰዎችን አነጋግሮ ሳለ የጻፈው ግን እጅግ በጣም ባጭሩ፣ በሦስት ገጽ ብቻ ነው:: የሕይወት ታሪክ አጻጻፉ ቃለ መጠይቅ ያደረገላቸውን ሰዎች ስም በዝርዝር ቢጠቅስም የደራሲውን ማንነት በግልጽ አያስተዋውቅም:: አዳነ ታደገ በክፍሌ አቦቸር የሕይወት ታሪክና ግጥሞቹ ላይ ባዘጋጀው የጥናት ጽሁፍም ቢሆን ለገጣሚነቱ መነሻ የሆነውን የህይወት ታሪክ ብቻ ከሚጽፍ ደራሲውን በተመለከተ የተለያዩ ሰዎች አነጋግሯልና በቁንጽል ባይጽፈው የደራሲው ማንነት በበለጠ ይገለጽ ነበር::

አምስቱን የጥናት ጽሁፎች በአጠቃላይ ስንመለከት ሁሉም የባለታሪኮቹን ድርሰቶች ጠቅሰዋል:: ይህ ደግሞ ከህይወት ታሪክ አጻጻፍ አንጻር ተገቢ ነው፤ የደራሲዎቹ ጽሁፎች በሕይወት ሳሉ ከሰሯቸው ስራዎች ዋነኞቹ ናቸውና:: በደራስያን የሕይወት ታሪክና ስራዎቻቸው ላይ በተሰሩት ሌሎች የጥናት ጽሁፎች ላይ እንደሚታየው ሁሉ በእነዚህ የጥናት ጽሁፎችም የባለታሪኩ መልካምነት እንጂ መጥፎ ጎኑ አልተገለጸም:: ይህ ደግሞ ከተገኙት የመረጃ ምንጮች አድሏዊነት የሚመነጭ በመሆኑ የሁሉም አጥኚዎች ችግር ነው::

## 1.4 በደራሲ ህዲስ ዓለማየሁ የስነ ጽሁፍ ስራዎች ላይ የተሰሩ ጥናታዊ ጽሁፎች ቅኝት

በደራሲ ህዲስ የስነ ጽሁፍ ስራዎች ላይ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል የቀረቡ የጥናት ጽሁፎች አስራ ዘጠኝ ደርሰዋል:: ሁሉም ለመጀመሪያ ዲግሪ ሟሟያ የተሰሩ ናቸው:: ከእነዚህም ውስጥ አስራ አንዱ የጥናት ጽሁፎች የደራሲ ህዲስ ዓለማየሁ ስራዎች ከሌሎች ደራሲያን ስራዎች ጋር በጥምረት የተጠኑባቸው ሲሆኑ ስምንቱ ደግሞ በደራሲው ረዥምም ልቦለድ መጻሕፍት ላይ የተሰሩ ናቸው::

በዚህ የጥናት ክፍል የደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁን መጻሕፍት ከሌሎች ደራስያን ሥራዎች ጋር ያጠኑትን ለመዳሰስ አልተሞከረም፤ ይልቁንም የሀዲስን ስራዎች ለብቻ የሰሩትን ስምንቱን የጥናት ጽሁፎች በዓመተ ምህረት ቅደም ተከተላቸው መሠረት አንድ ባንድ ለማሳየት ተሞክሯል:: ምንም እንኳን የጥናቴ ዓላማ የደራሲው የስነ ጽሁፍ ስራዎች ላይ ማተኮር ባይሆንም ከሕይወታቸው ጋር ያለውን ጥምረት ለመፈተሽ ማየቴ አይቀርምና ምን ተሰርቷል የሚለውን በሚቀጥሉት ምዕራፎች አስተዋውቃለሁ::

አስፋው ሺበሺ በ1964 ዓ.ም በቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዩኒቨርስቲ ለኢዱኬሽን ፋኩሊት «በአቶ ሀዲስ ዓለማየሁ መጻሕፍት ውስጥ ያሉ ምሳሌያዊ አነጋገሮች» በሚል ርዕስ የጥናት ጽሁፍ አቅርቧል::

የአስፋው ጥናታዊ ፅሁፍ ምዕራፎች ሳይሰጠው በስድስት ነጥቦች በርዕስ ተዘርዝሯል:: የመጀመሪያው ርዕስ መቅድም ሲሆን በውስጡ የያዘው ሃሳብም ከላይ የገለጽኩት የስያሜን ችግር የተመለከተ ነው:: የምሳሌያዊ አነጋገርን ውሳኔና አገልግሎት የሚገልጸው ሁለተኛው ርዕስ ደግሞ ስለ ምሳሊያዊ አነጋገር ምንነት አራት ደራሲያን የሰጡትን ውሳኔዎች አስፍሯል:: አጥኚው ከአራቱ ደራስያን ውሳኔዎች ተነስቶ «ምሳሌያዊ አነጋገር አብዛኛውን ጊዜ ያልተመሳሰሉ ነገሮችን በማመሳሰል ተራው አነጋገር የማይገልጽልንን ስሜት ለመግለጽ የምንችልበት ዘዴ ነው» ይላል:: ምሳሌያዊ አነጋገሮች ስሜትን ብሩህ አድርገው የሚያሳዩ መሆናቸውንም ያስረዳል:: በመቀጠልም የምሳሌያዊ አነጋገር መሠረት ሊሆኑ የሚችሉ ፍንጮች ያላቸውን በአራት ነጥብ አስፍሯል::

ሌላው የጥናቱ ክፍል ምሳሌያዊ አነጋገርን አካላዊና አካባቢያዊ በማለት በሁለት ምድብ ያመለከተበት ሲሆን በመጨረሻም በፊደል ተራ ቅደም ተከተል የተደረደሩ የሦስት መቶ ስድሳ ሦስት ምሳሌያዊ አነጋገር ስብስቦችና ትርጉማቸውን አመልክቷል:: ምሳሌያዊ አነጋገሮች የተሰበሰቡት ከሀዲስ ዓለማየሁ መጻሕፍት መሆኑን አጥኚው ቢገልጽም ከየትኞቹ መጻሕፍት እንደሆነ ግን አልጠቆመም:: አስፋው የጥናት ጽሁፉን እስካቀረበበት ዓመት ድረስ ደራሲ ሀዲስ ያሳተሟቸው መጻሕፍት ሦስት ናቸውና ከእነዚህ በየትኞቹ ላይ እንደሰራ መግለጽ ነበረበት::

አበበ ሐረገ ወይን «ፊታውራሪ መሸሻ» በሚል ርዕስ ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል በ1970 ዓ.ም ጥናታዊ ጽሁፍ አቅርቧል:: የአበበ ጥናት መግቢያውን ጨምሮ በስድስት ምዕራፍ ተከፍሏል

በመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱን መነሻ ችግር ከጠቀሰ በኋላ ርዕሱን የመረጠበት ምክንያትም ገጸባህሪ የልብወለድ አካል መሆኑን ለማሳየት እንደሆነ ይገልጻል፤ በመጨረሻም የጥናቱን ምንጭ አሰባሰብ ያትታል።

በምዕራፍ ሁለት ገጸ ባህሪ ሲባል ምን ማለት ነው? የሚለውን ጥያቄ ከተለያዩ አቅጣጫ ይመልሳል። በምዕራፍ ሦስት ደግሞ ፊታውራሪ መሸሻ የአካባቢው ሰው ናቸው መጥነታቸው የታየ በሚል የገጸባህሪውን የጊዜና የቦታ ይዘት ጠቁሞ፤ ገጸባህሪውን በእምነታቸው፣ በአለባበሳቸው፣ በአነጋገራቸውና በጉልተኛ ጸባያቸው ከፋፍሎ ከመጽሐፉ እየጠቀሰ ማንነታቸውን ይገልጻል።

በምዕራፍ አራት ፊታውራሪ መሸሻ ከቤተ ክህነት ሰዎች (ከአባ ሞገሴና ከአባተክለሃይማኖት) ጋር፣ ከባሮቻቸው ጋር፣ ከጉዱ ካሳ ጋር፣ ከሰብለ ጋር እና ከመደብ ጓደኞቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ታይቶበታል። በምዕራፍ አምስት ገጸባህሪው ምን ያህል ውበት ተሰጥቶበታል በማለት ፊታውራሪ መሸሻን ገልጿቸዋል። በመጨረሻው ምዕራፍ በገጸባህሪው አማካይነት ሊተላለፍ የተፈለገውን ጭብጥ ሲጠቁም በአምስት ረገድ ከፋፍሎታል። እነሱም በሃይማኖት፣ በፍቅር፣ በሥልጣን ረገድና የጭቁኖች አመድ በጉልተኛው ሥርዓተ ማህበርና ሥርዓተ ማህበሩ ለተማረው የህብረተሰብ ክፍል የሰጠው ቦታ ናቸው። አምስቱንም በዝርዝር አሳይቷል።

በማጠቃለያው የፊታውራሪ መሸሻን በገጸባህሪነት አሳሳል ሙሉ ዋጋ የሚሰጣቸው ደራሲው ሀዲስ ዓለማየሁ መሆናቸውን ጠቁሞ የገጸባህሪ አሳሳላቸው እንከን አለው የማይባል ግሩም ችሎታ ነው ሲል አድናቆቱን ይገልጻል። ቅርጽና ይዘቱን አዋሕደው በማቅረባቸውም ለአማርኛ ስነጽሁፍ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳደረጉ አንባቢ የሚመሰክረው ሀቅ ለመሆኑ በእርግጠኝነት ጽፏል።

«በፍቅር እስከ መቃብር መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የአነጋገር ዘዬዎች» በሚል ርዕስ በአለልኝ መንግስቱ በ1971 የተዘጋጀው ጥናታዊ ጽሁፍ ሌላው በዚህ ክፍል ለማስቃኘት የመረጥኩት ነው። አለልኝ በምዕራፍ አንድ የአነጋገር ዘዬን ምንነት የፍሬድሪክ ኤንግልስና የአፈናሲዬቭን መጻሕፍት መሠረት በማድረግ ሲገልጽ በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ የአነጋገር ዘዬዎችን በምሳሌ አስደግፎ፤ የቋንቋ ግንኙነት የሚፈጥረው የአነጋገር ዘዬና የሁለት ቋንቋ ተናጋሪዎች በቋንቋቸው ላይ ያላቸውን ዝንባሌም አመልክቷል። በምዕራፍ ሁለት <u>በፍቅር እስከ መቃብር</u> ውስጥ የሚገኙ የአነጋገር

የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር
INSTITUTE OF ETHIOPIA
የውጭ ቋንቋዎች
FOREIGN LANGUAGES

ዘዬዎችን፣ የመሬት ከበርቴው፣ የጭቁኑ መደብ፣ በተማሩና ባልተማሩ መካከል እና በፆታና በመደብ ልዩነት የሚፈጠሩ የአነጋገር ዘዬዎችን በመከፋፈል በጥናቱ አስፍሯል።

የመሬት ከበርቴው መደብና የጭቁኑ መደብ በጋራ የሚጠቀሙባቸው የአነጋገር ዘዬዎች፣ የገጸባህርያት አነጋገር ዘዬ ከመደበኛው አንጻር፣ የምዕላዶች ሁኔታ በቃል በስተመነሻና በስተመድረሻ መገኘትና የግለሰብ የአነጋገር ዘዬን ከፍቅር እስከ መቃብር ምሳሌ በመስጠት የሚገልጸው የጥናቱ ሁለተኛው ምዕራፍ ነው። አለልኝ በማጠቃለያው ደራሲው የአካባቢዎቹን የአነጋገር ዘዬዎች በሚገባ አልገለጹም፣ በአብዛኛው በመጽሀፉ የተጠቀሙት የአዲስ አበባን የአነጋገር ዘዬ ነው በማለት ይተቻል። ለዚህም ደራሲው በፍቅር እስከ መቃብር ውስጥ ከጠቀሷቸው አካባቢዎች የቆላ ደጋ ዳሞት አውራጃና የደብረ ማርቆስና የብቸና የአነጋገር ዘዬዎች በምን መንገድ መገለጽ ይገባቸው እንደነበር በምሳሌ አስረድቷል።

ተሾመ ይመር «የፍቅር እስከ መቃብሩ ጉዱ ካሳ» በሚል ርዕስ በ1972 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሁፍ ክፍል ለቢኤዲግሪ ማሟያ ባቀረበው ጥናታዊ ጽሁፍ በፍቅር እስከ መቃብር ዋና ገጸባህርያት ከሆኑት አንዱን ጉዱካሳን ከተለያየ አቅጣጫ በሦስት ምዕራፍ አሳይቷል።

በምዕራፍ አንድ ጉዱ ካሳ የተሳለበትን የህብረተሰብ እርከን ሲያሳይ በምዕራፍ ሁለት ደግሞ ጉዱ ካሳ ከሌሎች ገጸባህርያት ጋር ያለውን ግንኙነት ገልጾ በአራት ቡድን ከፋፍሎታል። ጉዱ ካሳና ፊታውራሪ መሸሻ በሚወክሉት የባላበት መደብ ክፍል፤ ጉዱካሳና ቀኛዝማች አካሉ የሚመሩት የባላባት መደብ ክፍል፤ ጉዱ ካሳና አበጀ በለው ከነባላገሮቹ በማለት ያላቸውን ግንኙነት በዝርዝር አመልክቷል። በመጨረሻም የጉዱ ካሳ ደቀመዛሙርት (ተባባሪዎቹ) እነማን እንደሆኑ ጠቁሟል ጉዱ ካሳ ማን ነው? ጠቅላላ ሰብእናውስ? የሚሉትን ጥያቄዎችም መልሷል።

የጉዱ ካሳ ትግል የአስከፊውን ባህል ጎጂነት ዘወርት ማጋለጥ ሲሆን የትግሉ ውጤት ግን እንደ ትግሉ ያላፈራ በኅብረተሰቡ ላይ ያጠላ መሆኑን «ጉዱ ካሳ ትግሉና የትግሉ ውጤት» ሲል በሦስተኛው ምዕራፍ ገልጾታል። ተሾመ በጥናቱ መደምደሚያ የጉዱ ካሳ በዚያ አካባቢ መቅረብ በራሱ ግላዊ ሁኔታና በእውቀት ህብረተሰቡን ቀድሞት ስለሄደ ተቀባይነት እንዳጣ ጠቅሷል። የደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁን የፈጠራ ችሎታም አድንቋል።

በ1974 ዓ.ም በዓምደማርያም ሀብተ ወልድ የተዘጋጀው ጥናታዊ ጽሁፍ ሀዲስ ዓለማየሁ በወንጀለኛው ዳኛ መጽሀፋቸው ውስጥ የተጠቀሙባቸው ዘይቤአዊ አነጋገሮችን መሠረት ያደረገ ነው:: ዓምደማርያም በምዕራፍ አንድ የዘይቤአዊ አነጋገሮችን ምንነት ገልጸ አገልግሎታቸውንና በልበወለድ ውስጥ እንዴት እንደሚታዩ አስረድቷል:: በጥናት ጽሁፉ መጀመሪያ ምዕራፍ ያስተዋወቀንን ዘይቤአዊ አነጋገሮች ከአቶ ሀዲስ ዓለማየሁ ረዥም ልቦለድ ከወንጀለኛው ዳኛ ውስጥ ለቅሞ በማውጣት በምዕራፍ ሁለት ትንታኔ ሰጥቶበታል ትንታኔው ተነፃፃሪ፣ ተለዋጭ፣ ሰውኛ፣ ተምሳሌት፣ ድምጸቀጽና ግነት የዘይቤ አይነቶችን መሠረት በማድረግ በምድባቸው የተዘረዘረበት ነው::

ሦስተኛው ምዕራፍ ከዘይቤአዊ አጠቃቀም አንፃር የወንጀለኛው ዳኛ አንዳንድ ድክመቶች ቀርቦበታል:: በዚህ ምዕራፍ የተነፃፃሪ ዘይቤ አጠቃቀም በመጽሐፉ ውስጥ በጉልህ የታየ ድክመት መሆኑን ምሳሌ በመስጠት ገልጸ በዘይቤዎቹ ላይ የገለጸ መብዛትና ግልጽነት መጉደልም ሌሎች የሚጠቀሱ ድክመቶች መሆናቸውን ጠቁሟል:: በወንጀለኛው ዳኛ ውስጥ ያሉ መቶ ሰባ ሦስት ዘይቤዎችንም በዝርዝር አቅርቧል::

ግዛቸው ሙሉጌታ «ጥላሁን ፈይሳ የወንጀለኛው ዳኛ ዋና ገጸባህሪ» በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ በ1974 ዓ.ም የጥናት ጽሁፍ አዘጋጅቷል:: ጥናቱ ሦስት ምዕራፎች አሉት የመጀመሪያው ምዕራፍ የ«ወንጀለኛው ዳኛ» ታሪክ በአጭሩ የቀረበበት ሲሆን በስሩም የመጽሀፉ ጭብጥና የአጻጻፍ ስልት በጥቂቱ ተገልጾበታል:: በምዕራፍ ሁለት ጥላሁን ፈይሳ ከሌሎች ገጸባህርያት ጋር ያለው ግንኙነት ተጠቅሶ፣ ጥላሁንና አጋሮቹ በሚል ደግሞ ጥላሁን ከሶፊያ ጋር እና ጥላሁን ከባላምባራስ ጉደታ ጋር ያላቸው ግንኙነት ተጠቁሟል:: ጥላሁን ከወንድይራድ እና ከቀኛዝማች ዳኛቸው ጋር ያለው ተቃርኖም ተገልጿል::

በሦስተኛው ምዕራፍ በገጸባህሪው አማካኝነት ሊተላለፍ የተፈለገው ጭብጥ ትምህርት፣ ፍቅር፣ ባህልና ፍትህ መሆኑን እያንዳንዱን በማብራራት አስረድቷል:: በማጠቃለያው ደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁ በወንጀለኛው ዳኛ አማካይነት ባሮጌይቱ ኢትዮጵያ የፊውዳል ስልተ ምርትን ቁልጭ አድርገው ማሳየታቸውን ጠቁሞ ጭብጦቹን የሚያሳዩት በዋናው ገጸባህሪ መሠረትነት መሆኑንም ጽፏል::

በ1976 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ ክፍል ከቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፎች አንዱ በዓለማየሁ ፀጋዬ የተሰራው «የግጭት ይዞታ በፍቅር እስከ መቃብር» ነው:: የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ምዕራፍ አንድ የግጭት ሚና በልቦለድ ውስጥ ያለውን እድገት፣ ረብና ተአማኒነት ገልጿል:: ምዕራፍ ሁለት በፍቅር እስከ መቃብር ውስጥ ያለው የግጭት

መንስኤና እድገቱን ከበዛብህ ታሪክ ጋር በዋናነት ጠቅሶ በተጨማሪ ሰብለወንጌል፣ ጉዱካሳና፣ የበዛብህ ወላጆች፣ ፍልሚያውና ዘመቻውን የሚገልጹት ታሪኮች ለዋናው ታሪክ ግጭት መጠናከርና መጓተት ያላቸውን ጉልህ ሚና አንድ በአንድ አመልክቷል።

በመጨረሻው ምዕራፍ በመጀመሪያው ምዕራፍ የገለጻቸውን የግጭት አንድነት፣ ረብና ተአማኒነት በፍቅር እስከ መቃብር እንዴት እንደተንጸባረቁ አሳይቷል። ዓለማየሁ «የፍቅር እስከ መቃብር» ደራሲ ተደራሲውን ወደዋናው ግጭት ከማስገባታቸው በፊት በንግር የትረካ ጥበብ ተጠቅመው የግጭቱን አዝማሚያ ሂደት እንደሚጠቁሙ ገልጾ የጥናት ጽሁፉን አጠቃልሏል።

በዚህ ክፍል ለቅኝት ከቀረቡት የጥናት ጽሁፎች በመጨረሻ የሚታየው «ሂዩመር በሀዲስ ዓለማየሁ ልቦለዶች ውስጥ» በሚል ርዕስ በ1984 የተጻፈው የሰሎሞን ክፍሌ ጥናት ነው። የመጀመሪያው ምዕራፍ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትና የጥናቱ ትኩረት የአቀራረብ ዘዴውን ሲገልጽ ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ የሂዩመር ምንነት ምክንያቶችና ጠቀሜታን ከሂዩመር ምንነት፣ ከተዛማጅ ቃላት ቅኝት፣ ከሂዩመር ንድፈ ሃሳቦችና ከሂዩመር ስነ ጽሁፋዊ ግልጋሎት አንጻር አብራርቷል። ሰሎሞን በመጨረሻው ምዕራፍ ሂዩመር የሚለውን ቃል በመፍታትና በሦስቱ የደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁ ረዥም ልቦለዶች በፍቅር እስከ መቃብር፣ በወንጀለኛው ዳኛ እና በየልምዣት ውስጥ የሚገኙትን ሂዩመሮች በማውጣት በምንና ለማን እንደቀረቡ አመልክቷል። ሂዩመሮቹ ለልቦለዶቹ ያላቸውን ቴክኒካዊ ጠቀሜታም ገልጿል። በማጠቃለያውም ከሦስቱ የሀዲስ ዓለማየሁ ልቦለዶች በርካታ ሂዩመሮችን የያዘና በሂዩመርነቱ ላቅ ያለ ደረጃ የሚሰጠው ፍቅር እስከ መቃብር መሆኑን ጠቅሷል። ደራሲው በልቦለዶቹ ወስጥ የተጠቀሙባቸው ሂዩመሮች ከተራኪው ቀድመው የሚሰጡት ገለጻዎች ሰፊና ዝርዝር ባይሆኑ የበለጠ የተዋጣላቸው ይሆኑ እንደነበር አጥኚው ምሳሌ በመጥቀስ አስረድቷል። ሰሎሞን በጥናት ጽሁፉ ሂዩመርን ለመበየን አስቸጋሪ መሆኑን በመጠቆም በተለያዩ ጸሐፊዎች ስለሂዩመር የተሰጡ ልዩ ልዩ ማብራሪያዎችንም አስፍሯል።

ከላይ በቅኝት መልክ ለማሳየት የሞከርኳቸው ስምንቱ የጥናት ጽሁፎች በደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁ ረዥም ልቦለዶች ላይ የተሰሩ ቢሆኑም ባነሱት ጉዳይ ግን አንዱ ከሌላው ይለያያሉ። እነዚህ ጥናቶች ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖር በአንድ ደራሲ ስራዎች ላይ መስራታችን ብቻ ነው። የእኔ ጥናት ደራሲው በሦስት ረዥም ልቦለዶቻቸው (በፍቅር እስከ መቃብር፣ ወንጀለኛው ዳኛና የልምዣት) ከፈጠሯቸው አራቱ ዋና ገጸባህርያት (በዛብህ፣ ጉዱ ካሳ፣ በሻህና ጥላሁን) ጋር ያላቸው ተመሳስሎ ላይ አትኩሯል።

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. የደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁ የሕይወት ታሪክ

### 2.1 ልደትና አስተዳደግ

ዓለማየሁ ሰለሞን ከጎጃም ክፍለ ሀገር ማቻከል ወረዳ ኤልያስ ከተባለ ከትውልድ አምባቸው ተነስተው ወደ ጎዛምን ወረዳ እንዶዳም አቀኑ። በዚያም ከወይዘሮ ደስታ ዓለሙ ጋር ተገናኙ። ወይዘሮ ደስታ በእንዶዳም ተወልደው፣ አድገው፣ በኋላም ለወግ ማዕረግ በቅተውበታል። ከአቶ ዓለማየሁ ሰለሞን ጋር ትዳር የመሰረቱት በዚሁ ቦታ ነው። በትዳራቸውም ጥቅምት 7 ቀን 1902 ዓ.ም የበኩር ልጃቸው ሀዲስ ዓለማየሁን ወለዱ።

በጊዜው የካህናት መተዳደሪያ ከደብረ መሬት የሚገኘው ምርት ነበር። በቤተክርስቲያን አገልጋይ የነበሩት ካህን ዓለማየሁም በሚያገኙት ምርት ቤተሰቡን ሲያስተዳድሩ ቆይተዋል። ይህንኑ አስመልክተው ልጃቸው ሀዲስ እንዲህ ይላሉ፡-

> እናቴ የቤት እመቤት ነበሩ። አባቴ እኔ በተወለድኩበት ጊዜ እንዲሁ ካህን ሆነው በደብረ ኤልያስ የደብተራነት ስራ ይሰሩ ነበር። ሌላ ስራ አልነበራቸውም። መሬት ይሰጣቸዋል። የደብረ መሬት እሪን ይባላል። እነሱም በሬዎች ገዝተው ያሳርሳሉ። በእዛ እየተዳደሩ ቤተክርስቲያን ያገለግላሉ። - - - የዚያን ጊዜው መሬት ርስት አይደለም እሪን ይባል ነበር። ይሸጣል፣ ይለወጣል። (ሀዲስ፣ ቃ.መ.፣ ታህሳስ 17/1992)

የሀዲስ ወላጆች በትዳራቸው ብዙም አልገፉም፤ ሁለተኛ ልጅ ሳይወልዱ ያለፍቺ ተለያዩ። አባታቸው የአንድ ደብር አለቃ ሆነው በመሾም ወደ ኢሉባቡር ሄዱ እናታቸው ግን እሳቸውን ይዘው እወላጆቻቸው ቤት ገቡ።

ወይዘሮ ደስታ ዓለሙ ከባለቤታቸው ተለያይተው ብዙ ከቆዩ በኋላ ሌላ ባል አገቡ። ሀዲስ እናታቸውን አልተከተሉም፤ እንዶዳም አያታቸው ቤት አደጉ።

ዓለማየሁና ደስታ ከተለያዩ ከብዙ ዓመታት በኋላ ልጃቸው ሀዲስ አሁን በሚኖሩበት (አዲስ አበባ ፕላዛ ሆቴል ጀርባ በሚገኘው) ቤት ተገናኝተዋል። የእናትና አባት ፍቅራቸውን በውል ያላጣጣሙ ሀዲስም ወላጆቻቸውን ሰብስበው በቤታቸው ጦረዋል። ዓለማየሁና ደስታ ሕይወታቸው ያለፈውም በዚሁ ልጃቸው ቤት ነው።

## 2.2. ትምህርት

### 2.2.1 ባህላዊ ትምህርት

ሀዲስ አለማየሁ እርቀው ሳይሄዱ በአያታቸው (በእናታቸው አባት) እገዛ ባደጉበት መንደር በእንዶዳም ከፊደል ቆጠራ እስከ ዜማ ዘለቁ። አያታቸው መምህር ዓለሙ ሥዩም ከተለያዩ አካባቢ የሚመጡ ተማሪዎችን ሰብስበው የሚያስተምሩ እውቅ ካህን ነበሩ። ሀዲስም ስለመጀመሪያ ትምህርታቸው የሚከተለውን ገልፀዋል።

> የዜማ መምህር የሚባለው ፊደል ከማስቆጠር ጀምሮ ንባብና ዜማ የሚያስተምር ነው። የእኔም አያት የዜማ መምህር ነበሩ። ፊደል አስቆጥረው ዜማ፣ ጾመድጓ እስከሚባለው ድረስ አስተምረውኛል። /ሀዲስ ቃ.መ. ጥቅምት 10/1992/

ሀዲስ ትምህርቱን አያታቸው ዘንድ እየተከታተሉ በእረኛነትም ያገለግሉ ነበር። ያን ጊዜ ያሳለፉትን አስታውሰው 'ፍካሬ' መጽሔት በአንድ ወቅት ባደረገላቸው ቃለ መጠይቅ እንዲህ ብለዋል፡-

> ትምህርት ከሕይወት የተገነጠለ አይደለም። ከዕድሜ እኩዮቼ ጋር ከትምህርት ውጭ በእረኝነት እንሰማራለን። የእረኝነት ስራ ራሱን የቻለ ትክለ - ሰብዕና ገንቢ ነው። ከጓደኛ ጋር መፋቀር አለ፣ አንዳንዴም ደግሞ መጣላት አለ። ለሁል ጊዜ መኳረፍ በቂም ለዘለዓለሙ መፈላለግ የለም። - - - የእርፍ አያያዙን የጠመንጃ አነጣጠሩን፣ የዳኛ ወንበር አቀማመጡን ፣ የዲያቆን አቋቋምና የድምጽ አጣጣሉን በአጠቃላይ የማኅበራዊ ተሳትፎን በየገፁ እንደቲያትር ሚና ይዘን እየሠራን መጪውን ሕይወት ሆነን የምንገኘው። (ፍካሬ፣ ቅ.1፣ቁ1፣ የካቲት፣ 1985)

ከዜማ ትምህርታቸው በኋላ ወደ ቅኔ ትምህርት ተዛወሩ። ከሦስት ዓመት ቆይታ በኋላ ቅኔ መቀኘት ጀመሩ። የቅኔ ትምህርቱን በአባታቸው አገር ኤልያስ ጀምረው በዲማ ፈፀሙ። የኤልያስ ቅኔ አስተማሪያቸው መምህር ገብረ ስላሴ ሲሆኑ የዲማው ደግሞ መምህር በላይ እንደነበሩ አሁንም ያስታውሳሉ።

ሀዲስ የቅኔ ትምህርታቸውን እስከመቀኘት አድርሰዋል። የቤተ ክህነት ትምህርታቸውን ለማሳደግ የቅኔ መምህራቸውን ተከትለው በአስራ ስድስት ዓመታቸው አዲስ አበባ መጡ።

ከጎጃም ተነስተው አዲስ አበባ የገቡበትን ዘመን እንዲነግሩኝ ደራሲ ሀዲስን ስጠይቃቸው እንደማያስታውሱ ገልፀውልኛል:: ይህ ብቻ ሳይሆን የሕይወት ታሪካቸውን በተመለከተ በአብዛኛው ዓመተ ምህረቱን ዘንግተዋል:: ሆኖም ግን ወቅቱ ንግስት ዘውዲቱ በሕይወት እያሉ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ንጉሠ ነገስት ተብለው አልጋ ወራሽ የነበሩበት ዘመን እንደ ነበር አውግተውኛል:: ወደ አዲስ አበባ አመጣጣቸውን አስመልክተው እንዲህ ብለዋል:-

> - - - አዲስ አበባ ስመጣ ብቻዬን አልነበርኩም:: ዲማ ቅኔ ያስተምሩን ከነበሩት ከመምህር በላይ ጋር ብዙ ተማሪዎች ነበርን:: መምህር በላይ ዲማ ቢያስተምሩም ተወላጅነታቸው ግን ሸዋ ነው:: ዲማ ትልቅ ደብር በመሆኑ ከብዙ አገር እየመጡ ይማሩበታል:: የእዛ መምህር መሆን ደግሞ ከፍ ያለ ደረጃ ነው:: ታዲያ እሳቸው ዲማ መምህር ሆነው ከቆዩ በኋላ ከአገሩ ካህናት ተጣሉ:: - - - የእሳቸው ተማሪ የሆንን ተከትለናቸው መጣን::/ ሀዲስ፣ ኅዳር 1/1992 ፣ ቃ.መ/

ሀዲስ አዲስ አበባ ከመድረሳቸው በፊት ከጎጃም ወደ አዲስ አበባ በሚወስደው መንገድ ላይ በሰላሌ አውራጃ አለተማርያም በተሰኘችው ቤተክርስቲያን ከጓደኞቻቸው ጋር ለሦስት ወራት ተቀምጠው ነበር:: መምህራቸው ግን አዲስ አበባ ካሉት ዘመዶቻቸው ጋር ይፃፃፉ ነበር:: ዘመዶቻቸው ለዋናዎቹ የቤተክርስቲያን ሹማምንት ነግረውላቸው የደብረ ብርሃን አለቃ ሆነው ስለተሾሙ አዲስ አበባ ሳይደርሱ በቀጥታ ወደዛው እንዲሄዱ አበሰሯቸው:: ተማሪዎቻቸውን ሰላሌ ትተው ወደ ደብረብርሃን አቀኑ::

የመምህራቸው መለየት ያላስደነገጣቸው ሀዲስና ጓደኞቻቸው እዛው ሰላሌ አለተማርያም የጀመሩትን ትምህርት እያጠኑ የአዲስ አበባን መንገድ ተያያዙት:: ሀዲስ እንደተናገሩት ሃሳባቸው ከቅኔ በኋላ የሚቀጥለውን የውዳሴ ማርያም ትርጉም መንገድ ለመንገድ እያጠኑ አዲስ አበባ እስኪደርሱ ለመጨረስ ነበር:: በኋላም አዲስ አበባ ሲደርሱ ከነጋዴዎች ጋር ለመመለስ::

ከጎጃም የተነሱት ተማሪዎች መምህራቸው ሰላሌ ትተዋቸው ከሄዱ በኋላ አዲስ አበባ እንዴት እንደደረሱ ሀዲስ እንዲህ ሲሉ ይገልጹታል:-

> ሁላችን እዛ አለተማርያም እንዳለን መምህራችን ትተውን ደብረ ብርሃን ተሹመው ሄዱ:: ከአለተማርያም በእግራችን ወደ አዲስ አበባ መጣን:: ከጎጃም የመጣነው ከነጋዴ ጋር እንመለሳለን በማለት ነበር:: ያን ጊዜ የጎጃም ነጋዴ ከጎጃም ማሩንም፣ ቆዳውንም በአጋሰስ ጭኖ ይመጣና አዲስ አበባ ይሸጣል:: ከአዲስ አበባ ደግሞ ጎጃም የሚፈለገውን ጨርቃ ጨርቅና ሌሎች እቃዎችን ገዝቶ ይመለሳል:: ሲመጣም ሆነ ሲመለስ በእግሩ ነበር:: ታዲያ

> እኛ ከጎጃም እንደመጣን እዚህ በቆየንበት ጊዜ ነጋዴ ስንፈልግ አስራ አምስት ቀን ያህል ሰነበትን:: / ሀዲስ፣ ቃ.መ. ኅዳር 1/1992

«ለአገሩ እንግዳ ለሰው ባዳ» የሆኑት ሀዲስና ጓደኞቻቸው በአስራ አምስት ቀን ቆይታቸው ቀኑን ከተማ ውስጥ ሲዞሩና ቁራሽ ሲለምኑ ይውላሉ:: ሌሊቱን ደግሞ የጳጳሱ ግቢ ከነበረው ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ዙሪያ ቅስናና ድቁና ከሚቀበሉት ጋር ያሳልፉት ነበር:: የቤተ ክህነት ትምህርት ግን አይማሩም ነበር::

## 2.2.2 ዘመናዊ ትምህርት

ሀዲስና ጓደኞቻቸው እንደወትሯቸው አዲስ አበባ ውስጥ አራዳ አካባቢ በየሱቁ የሚሸጠውን በመስኮት እያዩ ይዞራሉ:: አንድ ቤት ውስጥ ዳቦ ከመስታወቱ ባሻገር በማየታቸው ቆሙ:: የአምስቱን ልጆች ተሰብስቦ መቆም የተመለከተ አንድ የጎጃም ሰው ነበር:: የአገሩ ልጆች መሆናቸውን እንዴት እንደጠረጠረ ባይታወቅም ጠጋ ብሎ ጎጃሜነታቸውን ሲነግራቸው ተገረሙ:: የሚመለከቱትን ተረድቶ ሊጋብዛቸው ወደ ውስጥ ይዟቸው ዘለቀ:: እንግዳው ሰው ዳቦ ብቻ ሳይሆን፤ አቶ ሀዲስ «እንኳን ቀምሰነው ስሙን እንኳን ሰምተነው የማናውቀው ነገር» ያሉትን ሻይም ጋብዟቸው ጨዋታ ቀጠሉ::

ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ አበባ ዳቦና ሻይ የተጋበዙበት እለት ለሀዲስና ጓደኞቻቸው የሕይወታቸው አዲስ ፈር ቀዳጅ ሆነ:: ጋባዡ ልጆቹን በምን ስራ ላይ እንደሚገኙ ጠየቃቸው፤ ምንም ስራ እንደሌላቸው ወደ አገራቸው ለመመለስ ነጋዴ እየፈለጉ እንደሆነ ገለፁለት:: ሃሳባቸውን ካዳመጠ በኋላ አዲስ አበባ ቀርተው ዘመናዊ ትምህርት ቢማሩ መልካም መሆኑን ነገራቸው::

ሀዲስ ዘመናዊ ትምህርት የመማር ምኞት አልነበራቸውም:: ወደ አዲስ አበባ የመጡትም ካላይ እንደተገለፀው መምህራቸውን ተከትለው ትምህርታቸውን ለማጠናቀቅ ነበር:: ጋባዡ እንግዳ የፈረንጅ ትምህርት እንዲማሩ ሃሳብ ሲያቀርብላቸው ሀዲስ ብቻ ሲቃወሙ ሌሎቹ ግን ተቀብለውታል::

> እነዛ ጓደኞቼ ሁሉ ወሬውን ሰምተዋል፣ የሲዊዲን ሚስዮን ተማሪዎች ፍልውሃ ስመታጠብ ተሰልፈው ጠባቂያቸው እየመራቸው ሲሄዱ አይተዋል:: እኔ ግን አላየሁም ጓደኞቼ እዛ በገባን እያሉ ይመኙ ነበር:: ይህን ምኞታቸውን እዛ ማታ ማታ ስንሰበሰብ ይናገራሉ:: እዛው ሚስዮን

> አስተማሪ የነበረው ሰው ሲጠይቃቸው በደስታ እንገባለን እንገባለን አሉት:: / ሀዲስ ፣ ቃ.መ. ኅዳር 1/1992/

'የፈረንጅ ትምህርት ሃይማኖት ያስለውጣል' የሚለውን ወሬ የሰሙ ሀዲስ ዘመናዊ ትምህርት አልሻም በማለት አሻፈረኝ አሉ:: ጓደኞቻቸው ትምህርት ቤት ሲገቡ ለማየት ግን ተከትለው ሄዱ:: ትምህርቱን ለማስጀመር ፈቃድ የሚሰጡትን ሰው ያገናኛቸው እንግዳው የጎጃም ሰው ነበር:: ፈቃድ ሰጭውም ጎጃሜ ናቸው:: የልጆቹ ጎጃሜነት ሲነገራቸው በትምህርት ቤት ውስጥ የጎጃም ተወላጅ ተማሪ እንደሌለ ተናገሩ:: እነሱን በማግኘታቸውም መደሰታቸውን ገለፁ::

ሀዲስ ግን ለመግባት አለመፈለጋቸውን አሳወቁ:: ምክንያታቸውን ሲጠየቁ ሃይማኖታቸውን ለመጠበቅ መሆኑን ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት ይዞ የመጣው ሰው ተናገረ:: ምክንያታቸውን ያዳመጡት የትምህርት ቤቱ ኃላፊ እሳቸውም በአገራቸው ቄስ እንደነበሩ፣ ሃይማኖታቸውን እንዳልለወጡ፣ አሁንም ስማቸው በቄስ የሚጠራ መሆኑን አስረዷቸው እንዳያመልጣቸውም መከሯቸው:: ወደ ትምህርት ቤት የወሰዳቸው ሰውም፣ ጓደኞቻቸውም ሲያባብሏቸው ከረሙ:: በመጨረሻም ተስማምተው ስዊዲን ሚስዮን ትምህርት ቤት ለመጀመር በቁ::

የዘጠና ስድስት አመቱ አዛውንት፣ ብላታ መሀሪ ካሳ በመጀመሪያ ጎጃም በቅኔ ትምህርት ቤት ከሀዲስ ዓለማየሁ ጋር ተዋውቀው ነበር:: በኋላም የሁለቱም የጋራ ዘመድ በሆኑ በቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ቤት መገናኘታቸውን ብላታ ነግረውኛል:: ስዊድን ትምህርት ቤት ሲገቡም አንድ ላይ ነበሩ:: ዘመናዊ ትምህርት የጀመሩበት ዘመን 1918 ዓ.ም እንደሆነም አስታውሰዋል:: ከሀዲስ ጋር ትምህርት ቤት ሳሉ ካሳለፉት የማይረሱትን ሲያጫወቱኝ:-

> ትምህርት ፈሳጊ መሆናችንን ለመፈተን ለአንድ ሳምንት ትምህርት ቤቱ ባዶ ጠፍር አልጋ እንጂ ብርድ ልብስም ፍራሽም አልሰጠንም ነበር:: አቶ ሀዲስ አንድ ቁርበት ነበረው:: እሷን አንጥፈን ለሁለት እንተኛባት ነበር:: ከእለታት አንድ ቀን ቄስ ገብረስላሴ የተባሉ አስተማሪ ለጸሎት እንድንነሳ ለመቀስቀስ ሲመጡ ሸተተኝ  በማለት አጎዛዋን ወደ ውጭ ወርውረው ጣሏት:: /-መሀሪ ካሳ፣ ቃ.መ ኅዳር 25/1992/

ብለዋል::

ከሁለት ዓመት የስዊዲን ሚስዮን ትምህርት በኋላ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ለመቀጠል ገንዘብ ያስፈልጋቸው ነበር:: ቀድሞ ወደ ዘመናዊ ትምህርት ያመጣቸውን ሰው በጊዜው የጎጃም አስተዳዳሪ የነበሩት የራስ ኃይሉን እንደራሴ

ለመነላቸው:: ፈቃደኛ ሆነውም ገንዘብ እየከፈሉ ከሦስተኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል አስተማሯቸው:: እንዳሁኑ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተብሎ ሳይከፍል ቀድሞ የመጨረሻው ትምህርት ስድስተኛ ቢበዛ ስምንተኛ ክፍል ነበር::

ትምህርት ቤት ሲዘጋ በንግሥት ዘውዲቱም ሆነ በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግሥት ንጉሡ ወይም ንግስቲቱ ባሉበት መኳንንቱና ዲፕሎማቶች ተጠርተው ትምህርት ቤት ውስጥ ቲያትር ይታይ ነበር:: የሚታየው ቲያትር ግን በአማርኛ ሳይሆን በእንግሊዝኛ ወይ በፈረንሳይኛ ቋንቋ ነው:: ሀዲስ የእንግሊዝኛ ቲያትር ሲታይ ከተዋንያኑ ጋር ሳይለዩ አልፎ አልፎ ተዋናይ በመሆን ሰርተዋል:: በኋላም በአማርኛ 'ያበሻና የወደ ኋላ ጋብቻ' በሚል ርዕስ በ1921 ዓ.ም ገደማ ቲያትር ደረሱ:: (ዘመኑን በላክ ላየንስ ከተባለው መጽሐፍ የተረዳሁት ነው)

የመጀመሪያ ድርሰታቸው ስለሆነው ቲያትር:: ሀዲስ እንዲህ ብለውኛል:-

> - - - እንደዚሁ የእንግሊዝኛ ቲያትር እንደሚታየው እኛም ይህንን እናሳይ ብዬ ለትምህርት ሚኒስትሩ አቀረብኩ:: እያና በጣም ረዥም ስለሁነ አይሆንም አሉኝ:: (ሀዲስ ፣ ቃ.መ፣ ጥቅምት 10/1992)

የደረሱት ቲያትር እንዳይታይ የተከለከሉት ደራሲ ሀዲስ ዝም አላሉም ነበረ:: በወቅቱ የአገር ግዛት ሚኒስትር የነበሩት ቢትወደድ ገብረ ጻዲቅ ፊት በመቅረብ ቲያትሩ እንዳይታይ የትምህርት ሚኒስትሩ መከልከላቸውን ነገሯቸው:: ትምህርት ቤት ውስጥ ባይሆን በውጭ እንዲያሳዩት ለጃንሆይ ያስፈቅዱላቸው ዘንድ ጠየቋቸው:: ቢትወደድም ለጃንሆይ ነግረው ካስፈቀዱ በኋላ ቲያትሩ ፒያሳ የቀድሞው አርቲስቲክ ሕንጻ ፊት ለፊት እንደ ነበረ የሚነገርለት ማጀስቲክ ሆቴል ውስጥ ታየ:: ሦስት ሰዓት የፈጀ በመሆኑ ረዥምም ቢመስልም በተመልካቾችና በመገናኛ ብዙሃን ዘንድ አድናቆትን አትርፎ ነበር:: ጃንሆይም ሰው እንዳደነቀው ሲሰሙ የልዑል አልጋ ወራሽና ወለተ እስራኤል የጋብቻ ስነስርዓት ላይ እንዲታይ ጠይቀዋቸው እንደ ነበር:: ሀዲስ አውግተውኛል::

'ያበሻና የወደኋላ ጋብቻ' ቲያትር ለቅሶም ነበረውና ለሠርግ አይሆንም በማለት ሀዲስና ሌሎች ተማሪዎች አዲስ ቲያትር ለማዘጋጀት አሰቡ:: ሠርጉ ወደፊት በመሆኑ ቲያትር ለመድረስ ጊዜ ነበራቸው:: ተማሪዎቹ እንዳሰቡትም ሰብሰብ ብለው የደረሱትን ቲያትር ጃንሆይ፣ ራስ ስዩም እና ሌሎች መኳንንትና ሰርገኞች ባሉበት በቤተ

INSTITUTE ... STUDIES
የውጭ አገር ቋንቋዎች
FOREIGN LANGUAGES

መንግሥት ውስጥ አቀረቡ:: በዚህም የንጉሱ ምስል ያለበት የኪስ ሰዓትና ሃምሳ ብር ተሸልመው እንደ ነበር ሞልቬር ብላክ ላየንስ በተሰኘ መጽሐፉ ገጽ 137 ላይ ገልፆታል::

የሀዲስ ዓለማየሁ የግል ድርሰት የሆነው 'ያበሻና የወደ ኋላ ጋብቻ' ቲያትር ጣሊያንን ለመውጋት ወደ ዘመቻ በሄዱ ጊዜ ለቅስቀሳ እንደሚመች ተዘጋጅቶ ከመታየቱ በቀር በሌላ ጊዜ አልታየም:: የመጀመሪያውን 'ያበሻና የወደኋላ ጋብቻ'ንና ለዘመቻው ቅስቀሳ ማሻሻያ ለውጦች የተደረገለትን ቲያትር ለእኔ ከነገሩኝ በስፋት ትዝታ በተሰኘው መጽሐፋቸው ገልጸውታል::

ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ሳሉ የትምህርቱ ጥራት መጓደል ከንክኗቸው እንዲስተካከል በወቅቱ ድምፅ ካሰሙት ተማሪዎች አንዱ ሀዲስ ነበሩ:: ይህንኑ በአንደበታቸው ሲገልፁ:-

> ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት የመጨረሻ ክፍል ተማሪ ሰላሁ የትምህርት አሰጣጡ፣ መምህራኑ የሚሰሩት አንዳንድ ስህተት ይታረምልን በሚል ተማሪዎች መካከል ማጉረምረም አስነስተን ነበር:: በዚያን ጊዜ የነበሩት የጠቅላላ ትምህርት ሚኒስትር ብላቴን ጌታ ፀዳሉ ይባሉ ነበር:: / ሀዲስ ፣ ቃ.መ. ኅዳር 1/1992/

ብለዋል::

ይህ ማጉረምረም ግን በትምህርታቸው መጨረሻ ዓመት ላይ ቢሆኑም ለሀዲስ ከትምህሕርታቸው መፈናቀል ምክንያት ሆነ:: ጉርምርምታው ወደ ረብሻ ተለወጠ:: ለዚህም ቆስቋሾች እላይ ክፍል ያሉት ተማሪዎች ናቸው ተባለ:: ይህንን የሚያደርጉት በትምህርት ቤት ውስጥ አዳሪ የሆኑት ተማሪዎች ማታ ማታ በየመኝታ ክፍላቸው ተሰብስበው ሴራ እያጠነጠኑ ነው:: ስለዚህ አዳሪ መሆናቸው ቀርቶ አዲስ አበባ ቤተሰብ ያላቸውም የሌላቸውም እየተመላለሱ እንዲማሩ ተፈረደባቸው::

ሀዲስ ትምህርታቸውን ለመከታተል እንዲረዳቸው የሚያስጠጋቸው ዘመድ በከተማ ውስጥ ባለመኖሩ ትምህርት ቤቱን ለመልቀቅ ተገደዱ::

> ዘመድ ያላቸው ፣ ወላጆች ያላቸው ምንችገረን አሉና ከእዛ እየተመላለሱ ይማሩ ጀመር:: እኛ ግን ቤተሰብ የሌለን እየተመላለስን የምንማርበት

> ቤት የስንምና ትምህርት ቤቱን መልቀቅ ነበረብን:: ያን ጊዜ ትምህርቴን ሳጠናቅቅ ተቃርቤ ነበርና እንግዲህ አንደኛዬን መልቀቅ ይሻለኛል ብዬ ስዊዲን ሚስዮን ትምህርት ቤት በመምህርነት ተቀጠርኩ:: / ሀዲስ፣ ቃ.መ. ፣ ኀዳር 1/1992/

እድሜያቸው ባስከተለው ድካምና ሕመም ምክንያት አቶ ሀዲስ አንዳንድ ነገር ከመዘንጋታቸው ሊሆን ይችላል፤ አጭር የመምህርነት ኮርስ መውሰዳቸውን አልገለፁኝም ነበር:: ነገር ግን ሪደልፍ ኬ ሞልቨር በ በላክ ላየንስ መፅሀፉ እንዳሰፈረው ከስድስት እስከስምንት ወር የፈጀ የመምህርነት ኮርስ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ተከታትለዋል:: አቶ አስፋው ዳምጤም የአቶ ሀዲስ ዓለማየሁን ዘጠናኛ ልደት አስመልክቶ ታህሳስ 1/1992/ ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በድኅረ ምርቃ አዳራሽ በተዘጋጀው ፕሮግራም ላይ አቶ ሀዲስ አጭር የመምህርነት ኮርስ ተከታትለው እንደ ነበር ገልጸዋል::

ከዚህ በኋላ ለመማር እድል ያገኙት በአሜሪካን አገር ነበር:: ዋሽንግተን የአምባሳደር ጸሐፊ ሆነው በሂዱበት ወቅት እዛ የቆዩበትን ያህል በትርፍ ጊዜያቸው ዓለም አቀፍ ሕግ /International Law/ በማታው ክፍለ ጊዜ በዋሽንግተን አሜሪካን ዩኒቨርሲቲ ሦስት ዓመት ገደማ ተምረዋል::

## 2.3 የሥራ ዓለም

### 2.3.1 በመምህርነት

ሀዲስ በመጀመሪያ ወደ ስራ ዓለም የተሰማሩት ዘመናዊ ትምህርትን አሀዱ ባሉበት ቀድሞ ቅድስተማርያም ቤተክስቲያን አጠገብ በነበረው በስዊዲን ሚሽን ትምህርት ቤት በመምህርነት ነው:: በዚህ ትምህርት ቤት ለጥቂት ዓመታት ሲያስተምሩ በምን ትምህረት ላይ እንደሚያስተምሩ አይመረጥም ነበር:: እያንዳንዱ አስተማሪ እንዲያስተምር አንዳንድ ክፍል ተሰጥቶታል:: በተሰጣቸው ክፍል ጂኦግራፊም፣ እንግሊዝኛም ሂሳብም ያስተምሩ እንደ ነበር ሀዲስ ነግረውኛል::

ከስዊድን ሚሽን ትምህርት ቤት መምህርነት በኋላ በዳንግላ ከተማ ጉምሩክ መስሪያ ቤት ለአጭር ጊዜ በተቆጣጣሪነት ሰርተዋል:: ለሁለተኛ ጊዜ ለአንድ ዓመት በመምህርነት በዳንግላ አገልግለዋል:: ስራውን ለመጀመር የበቁትም የእንግሊዝ ቆንስላ ሲዘጋ ወደ ትምህርት ቤት በመቀየሩ ነበር::

> የቆንስላው ዋና ፅሕፈት ቤት አዲስ አበባ ነበርና የዳንግላው ሲዘጋ እንግሊዞች ለአንድ መኮንን ተሰጥቶ የፈረስና የበቀሎ ማሰሪያ ከሚሆን በማለት የኢትዮጵያን መንግስት አስፈቅደው ትምህርት ቤት ከፈቱ:: /ሀዲስ፣ ቃ.መ፣ ታህሳስ 7/1992/

«የኢትዮጵያ የልቦለድ ዓበይት ደራሲያን አጭር ዜና ሕይወት» በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ፅሁፍ በ1980 ዓ.ም በአደፍርስ አድማሱ የተሰራ የጥናት ጽሁፍ አለ:: በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የአቶ ሀዲስን የሕይወት ታሪክ አስመልክቶ፤ «አቶ ሀዲስ ዳንግላ በሚል ስም አዲስ ትምህርት ቤት ከፈቱ» ይላል:: ይህ ግን ትክክል አለመሆኑን ለአቶ ሀዲስ ባደረግኩላቸው ቃለ መጠይቅ ተረድቻለሁ:: ዳንግላ የነበረውን ትምህርት ቤት ራሳቸው የከፈቱት ሳይሆን ትምህርት ቤቱ አዲስ በመሆኑ ሌሎች መምህራን እስኪቀጠሩ ድረስ በአስተዳዳሪነትና በመምህርነት ይመሩት የነበረ ነው::

ዳንግላ እያስተማሩ ሌሎች መምህራን ሲቀጠሩ ትምህርት ቤቱን ለእነሱ አስረከቡ:: በጊዜው ካስረከቧቸው መምህራን አንዱ የዩፍታሔ ንጉሴ ወንድም አያሌው ንጉሴ እንደ ነበሩ አስታውሰው ነግረውኛል::

ከዳንግላ ቀጥሎ በቀጥታ ወደ ደብረማርቆስ በተመሳሳይ ሙያ በመምህርነት ለማገልገል ተዘዋውረው በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ላአንድ ዓመት ሰርተዋል::

### 2.3.2 በአርበኝነት

በ1928 ዓ.ም ጣሊያን ከኢትዮጵያ ጋር በነበራት ጦርነት ለመሳተፍ ሀዲስ በራሳቸው ፈቃድ ዘመቱ:: ያን ጊዜ ከደብረ ማርቆስ መምህርነት በቀጥታ ነበር ዘመቻ የሄዱት::

> ጎጃም የመንግሥት ትምህርት ቤት አስተምሬያለሁ፣ መጀመሪያ ዳንግላ ከዚያ ደብረ ማርቆስ:: ደብረ ማርቆስ አስተማሪ ሳለሁ ጣሊያን ኢትዮጵያን ወረረች:: እኔም ማስተማሬን ትቼ ጠበንጃ ገዝቼ ዘመትኩ:: /ሀዲስ፣ ቃ.መ፣ ጥቅምት 10/1992/

ከሀዲስ ጋር አራት ዘማቾች፤ የሰራዊቱ አዛዥ፣ የሆኑት ራስ እምሩ ከደብረ ማርቆስ ከመነሳታቸው በፊት ወደ ዳንግላ አመሩ:: የስነ ፅሁፍ ሰው መሆናቸውን በ 'ያበሻና ወደኋላ' ቲያትር አስመስክረው ነበርና ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት ደብረማርቆስ ቀስቃሽ ጽሑፍ እንዲያዘጋጁ ታዘዙ:: ንግግርም አደረጉ:: ዳንግላ ከደረሱ

በኋላም ያንኑ ንግግር እንዲደግሙት ራስ እምሩ ጠይቀዋቸው ነበር። ይህንኑ አስመልክቶ በትዝታ መጽሐፋቸው በስፋትና በጥሩ ሁኔታ ገልጸውታል።

ጦርነቱ በተጀመረ በዓመቱ በአክሱምና በእንደስላሴ መሀል በሚገኘው በሰለክላካ ተራራ የጣሊያን ጦር ኢትዮጵያን ካሸነፈ በኋላ የወገን ጦር ሸሽቶ ከተከዜ ማዶ ሰፍሮ ነበር (በትዝታ ገጽ 72 እንደተገፈው) እንደገና ጦርነቱን ለመቀጠል ባሰቡ ጊዜ አቶ ሀዲስ በአለቃቸው ራስ እምሩ ትዕዛዝ ወደ ሱዳን ሄደው ነበር። ይህንኑ ሲገልፁልኝ እንዲህ ብለዋል።

> በጣሊያን ጦርነት ጊዜ ድል ስንሆን የጦሩ አዛዥ ራስ እምሩ ጦርነቱን በአርበኝነት እንቀጥላለንና ስወታደር መድኃኒት ፣ ልብስና ድንኳን ገዝተህ ያስንበትን ሳናሳውቅህ አዛ ድረስ ታመጣልናለህ በማለት ወደ ሱዳን ሳኩኝ። /ሀዲስ፣ ቃ.መ፣ ታህሳስ 17/1992/

የሱዳን ቆይታቸው ለጥቂት ወራት ነበር። ግዙ የተባሉትን እቃ ሁሉ ገዝተው ሰበሰቡ፤ በነጭ አባይ በመርከብ ዘንዘብ ከደረሱ በኋላ በነጋዴ አስጭነው ኢሉባቡር ጎሬ አስገቡ።

አቶ ሀዲስ በልጅነት የተለይዋቸውን አባታቸውን ከረዥም ጊዜ በኋላ ያገኟቸው በኢሉባቡር ጎሬ፤ በዚሁ ጦርነት ወቅት መሆኑን ነግረውኛል። በትዝታ መጽሐፋቸው ገፅ 150 ላይም ጠቅሰውታል። 'የኢትዮጵያ ለቅሶ' በሚል ርዕስ ሁለት ገጽ ግጥም በ1936 ዓ.ም ገደማ በጦርነቱ ወቅት መንገድ ለመንገድ ሲሄዱ የገፉት መሆኑንም በዚሁ መፅሐፋቸው ገፅ 162 ተገልጿል።

በምዕራብ ኢትዮጵያ ኢሊባቡር አካባቢ በዘመቱ ጊዜ ጎጀብ የሚባለው ወንዝ ዳር ሲደርሱ በጣሊያኖች ተማረኩ። ከምርኮ በኋላም ከ ይልማ ደሬሳ ጋር በግዞት ወደ ጣሊያን አገር ሊሄዱ መወሰኑን ጥር 1929 ዓ.ም ተሰማ። ከአዲስ አበባ ተነስተው አስመራ በአይሮፕላን ምፅዋ ድረስ በመኪና፤ በመጨረሻም ከምፅዋ በመርከብ ተጉዘው ናፖሊ (ጣሊያን አገር) ደረሱ (በትዝታ መጽሐፍ ገጽ 204፣ 20ና 209 እንደተገለጸው)። ራስ ዕምሩም በግዞት ጣሊያን አገር አብረዋቸው ሄደዋል። ይልማ ደሬሳ ከሦስት ዓመት ቆይታ በኋላ ወዳገራቸው ሲመለሱ አቶ ሀዲስ ግን ከሌሎቹ ጋር ቆይተው ነበር።

አቶ ይልማ አንድ ሦስት ዓመት ከቆየ በኋላ ደቅርታ ተደርጎለት ተመለሰ እኔ ራስ እምሩና እነ ደጃች ግርማቸው ግን ጣሊያኖች ሁለተኛው ዓለም ጦርነት ተከፍቶ በጠላቶቻቸው በእነካናዳ አሜሪካና እንግሊዝ ድል ሆነው አገራቸው እስኪወረር ድረስ እዛው ነበርን። እንግሊዞች ጣሊያንን ሲወሩ እኛን እዛ አገኙንና አስለቀቁን። /ሀዲስ ቃ.መ፣ ጥቅምት 10/1992/

በሰባት ዓመት ከስምንት ወር በጣሊያን አገር እስር ቤት ቆይታቸው የጣሊያን መንግሥት አስፈቅደው ላቲንም፣ ጣሊያንኛም ተምረዋል። እዛው እያሉ ጣሊያንኛ ቋንቋ በደንብ ይናገሩ ነበር። ከጣሊያን አገር ከመጡ በኋላ ግን አንብበው መረዳት ቢችሉም እንደቀድሞው አቀላጥፈው መናገር እንደማይሆንላቸው ገልፀውልኛል።

ከሚያደንቋቸው መጻሕፍት አንዱ የሆነው የከበደ ሚካኤል ትርጉም ሥራ <u>ከይቅርታ በላይ</u> '(Beyond pardon) የተሰኘው መጽሐፍ ነው። ይህን መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ያነበቡት ጣሊያን አገር እስር ቤት ሳሉ ጠባቂዎቻቸው ሰጥተዋቸው ነበር። ጠባቂዎቹ ከየት እንዳመጡት ግን የሚያወቁት ነገር የለም።

### 2.3.3 በሚኒስትርነት

ከጣሊያን አገር ግዞት መልስ በ1936 ዓ.ም አቶ ሀዲስ ኢትዮጵያ እንደገቡ በጽሕፈት ሚኒስቴር ስር በጋዜጣ ክፍል ተመድበው ለስድስት ወራት ያህል ሰርተዋል። በመቀጠ ልም በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ለአጭር ጊዜ አገልግለዋል።

<u>'ብላክ ላየንስ'</u> መጽሐፍ እንደሰፈረው ከ1943 - 1949 ዓ.ም በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በመጀመሪያ ዋና ዲሬክተር ከዚያም ምክትል ሚኒስቴር በመሆን አገልግለዋል። ጥቂት ዓመታት ውጭ ሀገር ቆይተው ከተመለሱ በኋላ ለአምስት ወራት የትምህርት ሚኒስቴር በመሆን ሰሩ። ከዚያም፣ በፕላንና ልማት ሚኒስትር ሚኒስቴር ነበሩ። በትምህርት ሚኒስትር ስለነበራቸው የኃላፊነት ቦታ አቶ ሀዲስ እንዲህ ይላሉ፦

የዛን ጊዜ ጃንሆይ ስለሙ የትምህርት ሚኒስትር ይባላሉ። ጃንሆይ የትምህርት ሚኒስትር እኔ ነኝ ስለሚሉ የዛን ጊዜ ሚኒስትር አይባልም። በሌላ ሁኔታ ግን የእሳቸው ምክትል የሆነው የትምህርት ሚኒስትር ማለት ነው። (ሀዲስ፣ ቃ.መ.፣ ጥቅምት10/1992)

ሀዲስ ትምህርት ሚኒስቴር በነበራቸው ጥቂት የስራ ወራት አንዳንድ ሁኔታዎች እንዲሻሻሉና እንዲታከሉ ጥረው ነበር። የአፍሪካ ትምህርት ሚኒስቴሮች ስብሰባ

ያሳለፈውን ጉባኤ ተመርኩዘው ያቀረቡት ሃሳብና ምላሹን በተመለከተ ከሚያስታውሱት አንዱ ነው::

የአፍሪካ የትምህርት ሚኒስቴሮች በስብሰባቸው መሃይምነትን በሃያ አምስት ዓመት ውስጥ ከአፍሪካ ምድር እናስወጣለን ብለው ነበር:: አቶ ሀዲስም ከሚኒስቴሮቹ አንዱ በመሆናቸው ይህንን ለማስፈፀም ተስማምተዋል:: በትምህርት ሚኒስትር የነበረው ባጀት ግን አነስተኛ ስለነበር በየዓመቱ እንዲያሳድጉላቸው ሚኒስትሮች ምክር ቤትን ጠየቁ:: ጥያቄያቸው ግን ተቀባይነት አላገኘም ነበር:: በወቅቱ በስዊዝ ካናል ጦርነት በመኖሩ አገሪቱ ለውጭ ሀገሮች የምትሸጠውን ቡና፣ ቆዳ፣ ሌጦ የመሳሰሉትን ወደ ውጭ ለመላክ ባለመቻሏ ገንዘብ እንደሌለ ተነገራቸው:: እንዲያውም «የገንዘብ እጥረት በመኖሩ ከትምህርት ሚኒስትር ባጀት እሩቡ ይቆረ::» በማለት የገንዘብ ሚኒስቴሩ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ሃሳብ አቀረቡ::

የገንዘብ ሚኒስትሩ ያቀረቡት ሃሳቡ ሀዲስን ያበሳጫቸዋል:: የአፍሪካ ሚኒስቴሮች ባሳለፉት ጉባኤ መሠረት መሃይምነትን በ25 ዓመት ውስጥ ከኢትዮጵያ ለማጥፋት ለትምህርት ሚኒስትር መጨመር እንጂ መቀነስ እንደማይገባ ቢናገሩም ሰሚ ያጣሉ::

> ከአገራችን ስምናጠፋው መሃይምነት ገንዘብ አስፈላጊ ነው:: በማለት ጠየቅኩ:: አሁን ካለው በጀት እሩብ ይቀነስ ከተባለ ግን እሩብ ትምህርት ቤት ልንዘጋ፣ እሩብ አስተማሪና እሩብ ተማሪዎች ልናባር ነው:: ይሄ ወደ ኋላ እንጂ ወደፊት አያራምደንምና እንዴት ይሆናል ስል ይህን ለጃንሆይ አቅርብ ተባልኩ:: ጃንሆይም የገንዘብ ሚኒስትሩ ገንዘብ የለም ካለ ምን እናድርግ አሉኝ:: /ሀዲስ፣ቃ.መ፣ ታህሳስ 17/1992/

ሀዲስ ጥያቄያቸው ውድቅ በመሆኑ ስራውን ለመቀጠል አልፈለጉም:: ስለሆነም ስልጣንን በገዛ ፈቃድ መልቀቅ ባልተለመደበት ወቅት ስልጣናቸውን ለመተው ተገደዱ:: በወቅቱ ስልጣንን በፈቃድ መልቀቅ /resignation/ ባለመኖሩ ወሬውን ከውጭ /ከፈረንጆች/ ይስሙታል እንጂ በአገራችን አላዩትም:: በዚህ ምክንያት ሀዲስ ይቀጣሉ ወይም ይታሰራሉ ተብሎ ይፈራ እንደ ነበር ራሳቸው ገልጸውልኛል:: ጃንሆይ ግን ምንም እርምጃ አልወሰዱም ነበር::

በሌላ ጊዜ በዚሁ በትምህርት ሚኒስትር ሳሉ የገጠማቸውን «ሀዲስ አጫውቶኛል» በማለት የነገሩኝ ጓደኛቸው ብላታ መህሪ ካሳ ናቸው::

በአንድ ወቅት የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ቲያትር አዘጋጅተው ግርማዊ ንጉስ ነገሥት እንዲመለከቱላቸው ቢጋብዟቸውም ጃንሆይ ግን ሳያዩት ይቀራሉ ስለቲያትሩ ካዩት ሰዎች ሲሰሙ መንግስታቸውን የሚወቅስ መሆኑን ይደርስበታል። ሀዲስን አስጠ ርተው ፊታቸው ሲቀርቡ «የጠራኸኝ ልታሰድበኝ ኑሯል?» በማለት በቁጣ ይጠይቋቸዋል። የሀዲስ መልስ «እኔ አልጠራሁዎትም» የሚል ነበር።

ጃንሆይ ደግመው በቁጣ የትምህርት ሚኒስትሩ ካልጠራቸው ማን ሊጠራቸው እንደሚችል ሲጠይቁ ሀዲስ ዩኒቨርሲቲ እንደሆነ ይመልሳሉ። ዩኒቨርስቲው የራሱ ቻርተር ስላለው፣ አዛገፑ ቦርድ እንጂ እሳቸው አለመሆናቸውን ያስረዷቸዋል።

ሁኔታው ያበሳጫቸው ጃንሆይ ወዲያው ሀዲስን የቦርዱ ፕሬዚዳንት ሆነው ተማሪዎቹን እንዲጠይቁ ያዟቸዋል። ሀዲስ የጃንሆይን ትዕዛዝ ተቀብለው ተማሪዎቹን ሲጠይቁ «እኛ ነፃነት ያለን መስሎን አዘጋጅተናል። ነፃነት ከሌለን ከዛሬ ጀምሮ አናዘጋጅም» በማለት ይመልሱላቸዋል። ይህንኑ ሳይሸፋፍኑ ለጃንሆይ ሲነግሯቸው፣ ጃንሆይ «ይሄ ነው መልሱ?» በማለት ሀዲስ ላይ ያፈጣሉ። ሀዲስም «ይኸውነው» ሲሉ በድፍረት መመለሳቸውን ብላታ መሀሪ በመገረም ገልጸውልኛል። ይህ ስልጣናቸውን በፈቃዳቸው ከመልቀቃቸው በፊት የሆነ ነበር።

ሀዲስ ስልጣናቸውን ከለቀቁ በኃላ ጃንሆይ የእንግሊዝ አምባሳደር አድርገው ወደ ለንደን ልከዋቸው ነበር። ያን ጊዜ የተከለከሉትን ባጀት ግን በምትካቸው የትምህርት ሚኒስቴር ሆነው ለተሾሙት ለአቶ ገብረ መስቀል ገብረ እግዚአብሔር ፈቅደውላቸዋል። ይህን አዲስ ተሹመው ከነበሩት የሰሙት ሀዲስ «እኔን ለማስለቀቅ የተደረገ መስሎ ተሰምቶኛል፣ እግዜር ይወቀው» በማለት አውግተውኛል።

### 2.3.4 በአምባሳደርነት

ሀዲስ አለማየሁ ለመጀመሪያ ጊዜ በስራ ምክንያት ከኢትዮጵያ ውጭ የኖሩት ኢየሩሳሌም ነበር። በሀገር ውስጥ በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በሚሰሩበት ወቅት በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ቆንስል ሆነው ለሁለት ዓመት /1937-1938 ዓ.ም/ አገልግለዋል።

በአሜሪካ አገር ዋሽንግተን ዲሲ ከራስ እምሩ ጋር በመሆን ለአራት ዓመታት ጸሀፊ ሆነው ሰርተዋል:: ያኔ ኤምባሲ ሳይሆን ለጋሰዪን እንደነበር ሀዲስ ተናግረዋል::

ከ1953-1958 ዓ.ም ከኒውዮርክ መልስ እንግሊዝ ሀገር ለንደን የእንግሊዝና የኔዘርላንድ አምባሳደር ነበሩ:: በአሜሪካ ኒውዮርክ እና በእንግሊዝ ለንደን የቆዩበት ዘመን መረጃ የተገኘው ከሞልቬር መጽሀፍ «ብላክላየንስ» ነው:: አቶ ሀዲስ ወደ ኢትዮጵያ ከመመለሳቸው በፊት የእንግሊዝ ንግስት ዳግማዊት ኤልሳቤጥ በ1958 ዓ.ም የኮላር ሽልማት የምስክር ወረቀት ሰጥታቸዋለች::

በተለያየ ምክንያት ሃያ ዓመት የፈጀውን ታላቁን መጽሀፋቸው ፍቅር እስከ መቃብርን ያጠናቀቁት በእንግሊዝ ሀገር ሳሉ ነበር:: ፍቅር እስከመቃብርን በመጀመሪያ በእንግሊዘኛ ጽፈውት እንደነበርና እንግሊዝ ሀገር ሊያሳትሙት ሰጥተዋቸው ማተሚያ ቤት እንዳቆዩባቸው ነግረውኛል:: በኃላም የእንግሊዘኛውን ትተው በአማርኛ ጽፈው በጓደኛቸው በብላታ መሀፊ እርዳታ እዚህ አገር ለመታተም በቃ:: በሕትመት ወቅት ብዙ ችግር ገጥሟቸው እንደነበር ለብላታ መሀሪ ከዳረግሁት ቃለ መጠይቅ ተረድቻለሁ::

ፍቅር እስከ መቃብር እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1995 ዶክተር ዴቪድ አፕሌየርድ በተባለው የውጭ ዜጋ:: በእንግሊዝኛ ተተርጉማል ( Molvaer Reidulf K., 1997, 152)

የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ሽልማት ድርጅት በ1962 ዓ.ም ሀዲስ የወርቅ ኒሻንና የምስክር ወረቀት ከ10ሺህ የኢትዮጵያ ብር ጋር ሰጥቷቸዋል:: ባሳዩት የደራሲነት ቅልጥፍና አዲስ የድርሰት መንገድ መክፈታቸውን በማስገንዘብ ሽልማቱ እንደተሰጣቸው 'የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ሽልማት ድርጅት' 10ኛ ዓመት መጽሔት ገፅ 97 ያስረዳል::

አቶ ሀዲስ የተባበሩት መንግሥታት አምባሳደር በነበሩ ጊዜ ለአገራቸው ውለታ ውለዋል:: የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን (ECA) ጽህፈት ቤቱ አዲስ አበባ እንዲሆን ታግለዋል:: አቶ ሀዲስ እንዳወጉኝ ጃንሆይ በወቅቱ በአገራችን የሚሻሻል ብዙ ነገር አለ በማለት ጽሕፈት ቤቱ እንዲቋቋም ያቀረቡትን ሃሳብ ውድቅ አድርገውት ነበር:: በኋላ ግን ሃሳባቸው ተቀባይነት አግኝቶ ተፈጻሚ ሆኗል:: ለአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ሃሳቡ እንዴት እንደቀረበ ሲናገሩም:-

> አራት አፍሪካ አገሮች ፅህፈት ቤቱ እኛ አገር ይሁን ብለው ጠይቀው ነበር:: ነገሩ ሲጎተት ቀይቶ እኛ አምስተኛ ነበርን:: ፅህፈት ቤቱ በሚቋቋምበት ቦታ ቤት የሚሰራው የተባበሩት መንግስታት ነበር:: በአውሮፓ በእስያና በአሜሪካም የሚደረገው ስፅህፈት ቤቱ ቦታ ብቻ መስጠት ነው:: እኛ ግን ከሌሎች አገሮች ቀድሚያ እንድናገኝ ቦታ መስጠት ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያ መንግስት ገንዘብ አውጥቶ በየተባበሩት መንግስታት ፕላን መሰረት ቤቱን እንስራለን የሚል ሃሳብ እናቀርብ በማለት ለጃንሆይ ነገርኳቸው እነሱም ሃሳቡን ተቀበሉት ቀድሚያም ተሰጠን:: /ህዲስ ቃ.መ ጥቅምት 10/1992/

ብለዋል::

ቀዳማዊ ኃይለስላሴ የህዲስን ሃሳብ ተቀብለው ጽህፈት ቤቱ ከተሰራ በኋላ «እንዴት ቤት ብቻ ተሰርቶ የሰጣል» በማለት የውስጡን እቃ ሁሉ አሟሉ::

በአሜሪካ ኒውዮርክ የተባበሩት መንግስታት ማህበር ስብሰባን/' General assembely/ ተካፍለው ከተመለሱ በኋላ ለአጼ ኃይለ ስላሴ አንድ ጽሑፍ ሰጥተዋቸው ነበር:: ወቅቱ የመንግስት ግልበጣ ሙከራ የተደረገበት 1953 ዓ.ም. ነው:: በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ይሰሩ የነበሩ የህዲስ ጓደኞች በሙከራው ተጠርጥረው ታስረው ነበር::

ህዲስ እስር ቤተ ድረስ በመሄድ ጓደኞቻቸውን ስለታሰሩበት ጉዳይ ጠየቋቸው:: እስረኞቹም አድማ ውስጥ እንዳልነበሩ ያለጥፋት መታሰራቸውን ገለጹላቸው:: ህዲስም እስረኞቹን ካዳመጡ በጂላ ለጃንሆይ ጥር 23 ቀን 1953 ዓ.ም አስራ ሦስት ገጽ 'ልዩ ማስታወሻ ' ጻፉላቸው:: ከፃፉላቸው ጥቂቱን አንብበውልኝ ነበር:: ሃሳባቸውን ለመግለጽ እንዲፈቀድላቸው በትሕትና ከጠየቁ በኃላ ካነበቡልኝ በአጭሩ እንዲህ ይላል፡-

> ማናቸውም ነገር መነሻ ምክንያት ሳይኖረው እንዲሁ ከደልዳላ መሬት አይፈልቅም ወይም ከጥሩ ሰማይ አይዘንብም:: ስምሳሌ አስመደሰት ወይም ቅርታ ከሌስ ሁከት አይነሳም::... ምናልባትም በቅርቡ በኢትዮጵያ ሁከት ያስነሱ ጥቂት ሰዎች በዚህ መንፈስ የተመሩ ናቸው ስማስት ይቻል ይሆናል:: የሆነ ሆኖ አስመደሰት ወይም ቅርታ ካስ ሁከት የሚነሳበተ ጊዜ፣ ሁከት የሚነሳበት መልክ፣ የሚያነሱት ሰዎች ወይም አሳማው የተስያየ ይሁኑ እንጂ መነሳቱ ስስማይቀር ከሁሉም የሚሻስው መነሻ የሚሆኑትን ምክንያቶች በጊዜ ደህና አድርገ መርምሮ ማስወገድ ነው... (ህዲስ፣ ቃ.መ ታህሳስ 17/1992)

በጽሑፋቸው መጨረሻም የገለጹበት ቋንቋ መራራ ሊሆን እንደሚችል ጠቅሰዋል:: ምንም እንኳን ሰው ሆኖ የተፈጠረ ሁሉ ከመራራ እውነት የተቀመመና የለዘበ ከንቱ ውዳሴ እንደሚጣፍጠው ማመናቸውንም ጽፈዋል:: ጽሑፋቸውን ሲያጠ

ቃልሉም የሰጡት አስተያየት ለግርማዊነታቸውና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘለቄታው ጠቃሚ እንደሚመስላቸው ገልጸዋል።

ልዩ ማስታወሻውን ያነበቡት ጃንሆይ ከፅሁፉ ውስጥ «ከንቱ ውዳሴ» የምትለውን ሀረግ መዘው «ሰደብከኝ» በማለት ሀዲስን ተቆጧቸው። ሀዲስም የጻፉት ስድብ ሳይሆን መራር እውነት እንደሆነ በትሕትና ገለጹ። ጽሁፉን አርመው እንዲያመጡ ጃንሆይ ቢያዟቸውም «ምንም የማርመው የለኝም» በማለት መለሱ። በዚህ ንጉሱ ትንሽ ተቀይመው እንደነበረ ሀዲስ ነግረውኛል።

ከእንግሊዝ ሀገር ከተመለሱ በኃላ አቶ ሀዲስ በፕላንና ልማት ሚኒስቴር ሆነው ሲያገለግሉ ወደ ህግ መወሰኛ የምክር ቤት አባል ሆነው ፓርላማ ተዘዋውረው ነበር። የቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ መንግስት እስኪወድቅ ድረስ እዛው ሰርተዋል። በ1966 አብዮቱ እንደፈነዳ ደርግ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሆኑ ጠይቋቸዋል።

> ደርግ ስልጣን ሲይዝ ለምን እንደሆነ አላውቅም እኔን ጠቅላይ ሚኒስትር ሁን ተባልኩ። እኔ ግን 'ምን ለመስራት ነው የተፈለገው' በማለት ስጠይቅ 'አንተ ዝም ብለህ ስራና በኋላ ይታያል' አሉ። የለም ለውጥ ለውጥ ይባላል ለውጡ ምን ልታመጡ ነው? ስላቸው ዝርዝሩን በኃላ እናመጣለን አሉኝ የለም ለመስራት የተፈለገው ነገር ፕላኑ ይነገረኝ።... አይ እሱ በኃላ የሚመጣ ነው አሁን ዝርዝሩ የለንም አሉ። እኔ ሳምጣና ቁጭ ብለን እንስማማበት ስላቸው አይሆንም አሉ። እንግዲያውስ እኔም አይሆንም አልኩ። (ሀዲስ፣ ቃ.መ.ጥቅምት 10/1992)

በወቅቱ የደርግ ባለሥልጣን ከነበሩት ጋር በሃሳብ ባለመስማማታቸው አሻፈረኝ እንዳሉ ይታሰራሉ ተብሎ ይፈራ ነበር። ሆኖም ግን ሳይታሰሩ በምትካቸው ልጅ ሚካኤልን ጠቅላይ ሚኒስትር አድርገው ሾሟቸው። ከዚህ ጊዜ በኋላ በቤታቸው ይጽፉና ያነቡ ነበር።

ለጠቅላይ ሚኒስትርነት ተጠይቀው ባለመስማማታቸው ከቀረ ከጥቂት ዓመታት በኋላ በደርግ ተቋቁሞ በነበረው ብሔራዊ ሸንጎ የጎጃም ክፍለ ሀገርን ህዝብ ወክለው እንዲሰሩ ተጠየቁ። ሀዲስም ጡረታ ላይ መሆናቸውን፣ ድካምና ሕመም እንደሚሰማቸው ገልጸው መስራት እንዳማይችሉ ተናግረው ነበር። «የጎጃም ሕዝብ የመረጠው ሌላ ሰው ሳይሆን እርስዎን ነው።» በማለት እንዲሰሩ አስገደዷቸው። በመጨረሻም አዲስ አበባ እንዳሉ ለሁለት ዓመት ያህል በሸንጎ አባልነት አገለገሉ።

በስራ ዓለም ከተሰማሩባቸው የመጨረሻው የጎጃም ሕዝብን ወክለው የብሔራዊ ሸንጎ አባል በመሆን ያገለገሉበት ነው። በመንግስት ስራ ላይ እያሉ ግን ጊዜውን ባያስታውሱትም ኢሉባቡር መሬት ያለሙ እንደነበር ነግረውኛል።

## 2.4 ትዳር

ሀዲስ ኢየሩሳሌም በቆንስልነት ተሹመው በሄዱ ጊዜ ወይዘሮ ክበበ ጸሀይ በላይም ከአያታቸው ጋር እዛው ይኑሩ ነበር። ተያይተው፣ ተዋወቁ፣ ተፋቀሩ ከእዛም ለጋብቻ በቁ፣ እንደ ሀዲስ አገላለጽ። ጋብቻቸውን የፈጸሙት በ1938ዓ.ም ገደማ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ደንብ በቁርባን ነበር።

ወይዘሮ ክበበ ጸሀይ ብዙ ጊዜ በህመም ይሰቃያሉ። አቶ ሀዲስ እንግሊዝ ሀገር በአምባሳደርነት ሲሄዱ ለሀገራቸው ከማገልገላቸው በተጨማሪ ያስደሰታቸው ነገር ነበር። ይኸውም በህመም ላይ የነበሩ ባለቤታቸውን ለማሳከም ጥሩ እድል ማግኘታቸው ነው።

> «እንግሊዝ ሀገር ሂድ በተባልኩ ጊዜ ደስ ብሎኝ የሄድኩ ለእሷ ሕክምና ይመቻል ብዬ ነበር። ምንም ያህል ጤና አላገኘችም። እንግሊዝ ሀገር ከመሄዳችን በፊት ቀድም እንዳልኩት አሜሪካ ተቀምጠን ሳለ የእኔም የእሷም ሐኪም ነበርን።... እንግሊዝ ሀገር ከሄድን በኃላ እሷ ታማ ሐኪሞቹ የሚሉትን ሁሉ እኔ ወደ ኒውዮርክ እልክበት ነበር። ... 'ይዘሃት ና' አለኝ እናም ለሕክምና ብቻ ይዤ ያት አሜሪካ ኒውዮርክ ሄድኩ እዛው እንዳለች አረፈች። (ሀዲስ፣ ቃ.መ.ኅዳር 1/1992)

ሀዲስ ከአስራ አምስት ዓመት የትዳር አጋራቸው ሞት በኃላ ሌላ ሚስት አላገቡም። ስለ ልጅ ባህርይና አስተዳደግ ጠንቅቀው እንደሚያውቁ «የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም» በተባለው መጽሐፋቸው ከመገለጹ በተጨማሪ የአጎታቸው ልጅ ወይዘሮ ስምረት አምሳሉ የመሰከሩት ነው። ቢሆንም ሀዲስ ግን ለልጅ አልታደሉም።

የሀዲስን ትዳር አስመልክተው ወይዘሮ ስምረት እንዲህ ብለውኛል፡-

> በጣም ጥሩ ትዳር ነበራቸው ያ ጥሩ ትዳር ስለጠፋም ይመስለኛል ከእዛ በኃላ ያላገቡት። ባለቤታቸው ቤት በማስተዳደር እንግዳ በመቀበል፣ ባለቤታቸውን በመንከባከብ ጥሩ ሴት ነበሩ። ሌላ እንዲያገቡ ጓደኞቻቸውም፣ ዘመዶቻቸውም ደክመውላቸው ነበር። እሳቸው ግን እምቢ አሉ በምን ልተካው ከሚል መሰለኝ።» (ስምረት፣ ቃ.ም.ጥር 26/1992)

ብላታ መሀሪ ካሳም፣ ሀዲስ ከባለቤታቸው ጋር የሞቀ ፍቅር እንደነበራቸው ያወሳሉ።

ሀዲስ በባለቤታቸው ወይዘሮ ክበበ ጸሀይ ቦታ ላይ ቤት ሰርተዋል። ቤቱን ሲሰሩ አንድ ወዳጃቸው፡«ከባለቤትህ ጋር ብትለያዩ እኮ ይኼንን ቤት አትሰጥህም» ቢላቸው «አንለያይም እንጂ ብንለያየም ይሄ ለባለቤቴ ያንስባታል» በማለት መመለሳቸውን ብላታ መሀሪ ነግረውኛል። ይህ የፍቅራቸው መግለጫ መሆኑንም ጠቁመዋል። አክለውም ሀዲስ ባለቤታቸው ከሞቱ በኋላ ሕፃናት ማሳደጊያ ሲሰጡ ባለቤታቸው ስም ማስየማቸው ሌላው የፍቅራቸው ማስረጃ ነው ይላሉ። በተመሳሳይ ክቡር ዶክተር ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ስላሴም ሀዲስ ከባለቤታቸው ጋር ስለነበራቸው ፍቅር ይህንኑ በምሳሌነት ጠቅሰውልኛል።

ሀዲስን ባለቤታቸው ከሞቱ በኃላ ለምን ሌላ ሚስት እንዳላገቡ ጠይቄያቸዋለሁ። መልሳቸው «ይኼንን የንስሀ አባት ስትሆኚ ጠይቂኝ» የሚል ነበር።

በብቸኝነት በጡረታ ቤት ውስጥ በተቀመጡበት ጊዜ ከፊል መጽሐፎቻቸውን አጠናቀዋል። ለቲያትር እንዲመች ያዘጋጀሁት ነው ያሉኝን መጽሐፍት <u>ወንጀለኛው</u> ዳኛን በ1974፣ በጣሊያን ጦርነት ወቅት የነበሩበትን ሁኔታ የሚያወሳው <u>ትዝታን</u> በ1985ና <u>የልምዣትን</u> በ1980ዓ.ም አሳትመዋል። በተጨማሪም ለሕትመት ያልበቁ ግጥሞች ጽፈዋል።

በ'ፈርጥ' መጽሔት ቅጽ 4 ቁጥር 2 ላይ እንደተገለጸውም «ዘላለማዊት ነፃና አንዲት ኢትዮጵያ» የሚል ርዕስ የያዘ ጽሁፍ አላቸው። «ወደፊት ጊዜ ያገኘሁ እንደሆን እሷን አሳትማለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ» ብለዋል።

ከቀድሞ እስካሁን በመጻፍ ያሰባሰቡትን ግጥም ለማሳተም እንደሚያስቡ ገልጸውልኛል። ሀዲስ መጻሕፍት የማሳተም እቅድ ብቻ ሳይሆን ሌላም ብዙ ሃሳብ አላቸው። ይህንንም ወይዘሮ ስምረት እንዲህ በማለት ይገልጹታል፡-

> ለአገራቸው ብዙ አድርገዋለሁ የሚሉት ህልም ነበራቸው። ያ ከንቱ ሆኖ በመቅረቱ እድሉ ስላልገጠማቸው በጣመ ያዝናሉ ብዙ ደስ የሚል ህልም ነበራቸው እሱን እንድነግርሽ ግን አትገፋፊኝ /ስምረት፣ ቃ.መ ጥር 26/1992/

ከእቅዳቸው ውስጥ ጥቂቱን ቢነግሩኝ ወይዘሮ ስምረትን ደጋግሜ ጠይቄያቸዋለሁ። ሊነግሩኝ ግን ፈቃደኛ አልነበሩም።

'ቤዛ ለወገን' የተባለው የበጎ ምግባር ማኅበር ሐምሌ 18 ቀን 1990 ዓ.ም 'ለሀገራችን ሥነ ፅሁፍ ላበረከቱት ቤዛዊ አስተዋፅኦ' በማለት ፎቷቸው በቆዳ ላይ የተሳለበት ስጦታ ሰጥቷቸዋል::

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ነሐሴ 27 ቀን 1991 ዓ.ም በመኖሪያ ቤታቸው ተገኝቶ ለኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ ላደረጉት አስተዋጽኦ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሰጥቷቸዋል::

በአሁኑ ወቅት የዘጠና ዓመቱ አዛውንት ክቡር ዶክተር ሀዲስ ዓለማየሁ ሕመም ተጭኗቸው ውሏቸው አልጋ ላይ ነው:: ብዙውን ጊዜ እንግዳ የሚቀበሉትም በመኝታ ቤታቸው ነው:: አልፎ አልፎ ጤንነት ሲሰማቸው የግላቸው ቤተመጻሕፍት ውስጥ እንደሚጽፉና እንደሚያነቡ የቤቱ አስተዳዳሪ፣ ረዳታቸው ወይዘሮ ባንቺ አምላክ ትናገራለች::

## 2.5 የደራሲው ዋና ዋና ባሕርያት

ከሕይወት ታሪካቸው እንደምንረዳው ሀቀኝነት ከሀዲስ ዋና ባህርያት አንዱ ነው:: በምንም ጉዳይ ላይ ቢሆን መወላወልና ሽፋፍኖ ማለፍን አይወዱም:: ለዚህም ነው በየተሰማሩበት የስራ መስክ የመጣውን ችግር ፊት ለፊት የተጋፈጡት::

በህይወት ታሪካቸው ላይ እንደተገለጸው የትምህርት ሚኒስትር በነበሩ ጊዜ መሃይምነትን ከኢትዮጵያ ለማጥፋት ካለው በጀት ላይ እንዲጨመርላቸው መንግስትን ጠይቀው ነበር:: ጥያቄያቸው ባለመመለሱ በፈቃዳቸው ስራውን ለቀቁ:: ስራ በመተዋቸው ሊደርስባቸው የሚችለውን ችግር ሳያስቡት ቀርተው አልነበረም:: «በትክክል በሀቅ መስራት አለበት» የሚል አቋም አላቸው::

በዚሁ በትምህርት ሚኒስትር ሳሉ ጃንሆይ አንዳንድ የወዳጆቻቸውን ልጆች ወደ ውጭ ሀገረ እንዲልኳቸው አዘዋቸው ነበር:: ሀዲስ ግን «ልጆቹ በመጀመሪያ በአገር ውስጥ ያለውን ግዴታ አልፈጸሙምና አይሆንም» በማለት እንደመለሱላቸው የቅርብ ወዳጃቸው ብላታ መሀሪ አውግተውኛል::

ሀዲስ ድፍረትና በራስ የመተማመን ባሕሪም ይታይባቸዋል:: መንግስት ያስረኛል፣ ያንገላታኛል፣ ችግር ይደርስብኛል ብለው መስራትና መናገር ያላባቸውን በመተው ወደ ኃላ ሲሉ አልታዩም:: በጊዜው ይፈሩ ለነበሩ ንጉሠ ነገሥት አልተሸቆጠቆጡም፤ ስህተት ሲሰሩ አይተው በዝምታ አላለፏቸውም::

በ1953 ዓ.ም በተደረገው የመንግስት ግልበጣ ሙከራ የተጠረጠሩትን ሰዎች ጃንሆይ እንዳሰሯቸው ሲሰሙ ሀዲስ ዝም አላሉም:: የሰሩት ስራ መልካም አለመሆኑን በሰላ ብዕራቸው ገልጸውላቸዋል:: በአስተዳደራቸው ላይ የነበረውን ችግርና ሌላውንም ሳይደብቁ በጽሁፍ አቅርበው ነበር:: በጽሁፋቸው የአስተዳደሩን ጉድለት ከዘረዘሩ በኃላ ማሻሻያ ነጥቦችን ጠቁመዋል:: መሻሻል የሚገባው ሳያሻሻል በቀር በዚህ ምክንያት ሰዎችን እየሰበሰቡ ማሰርና መቅጣት ተገቢ አለመሆኑን ገልጸዋል:: ይሄን ፅሁፍ ያስታወሱ ጓደኛቸው መሀሪ ካሳ እንዲህ ብለዋል:-

> በዚያን ጊዜ የነበረውን አስተዳደር አሻሽሉ ብሎ መጠየቅ በጣም ድፍረት ነው:: ይሄ ትክክለኛነቱን፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስተዳደር አሳቢነቱን የሚያስረዳ ነው:: (መሀሪ፣ ቃ.ም. ታህሳስ 2/1992)

የተጻፈላቸው ልዩ ማስታወሻ ያልተዋጠላቸው አፄ ኃይለ ስላሴ ሀዲስ ጽሑፉን አርመው እንዲያመጡ አዘዋቸው ነበር:: አቶ ሀዲስ ግን ማረም እንደማይችሉ በድፍረት ተናግረዋል::

ሀዲስ ከትምህርት ሚኒስትር ብቻ ሳይሆን ከፕላን ሚኒስትርም ስራቸውን በፈቃዳቸው ለቀዋል:: ይህም የዳፋርነታቸውና አስመስሎ ለመኖር ያለመቻላቸው ሌላ መግለጫ ነው:: ከፕላን ሚኒስቴር ስራቸውን ሲለቁ ምክንያታቸው መንግሥት ባጀት አለመጨመሩ እንደነበር ለብዙ ዓመታት ያልተለዩዋቸው ዶክተር ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ስላሴ ገልጸውልኛል::

በቤት ውስጥ አስራ አምስት ዓመት አብራቸው የኖረች ወይዘሮ ባንቺ አምላክ እና ቤት ጠባቂያቸው /ዘበኛ/ አቶ ንጉሴ፣ ሀዲስ በቃላቸው እንደሚጸኑ ይናገራሉ:: ቁጣ ካፋቸው የማይወጣና ደግነት የተላበሱ መሆናቸውንም ይመስክራሉ::

ሀዲስ ባለቤታቸው ክበበጸሀይ ከሞቱ በኃላ ሌላ ሚስት አለማግባታቸው ከፍቅራቸው ባሻገር እምነታቸውን ጠብቀው መኖራቸውን ያሳያል:: ዘመዶቻቸውና

ሀዲስ ድፍረትና በራስ የመተማመን ባሕሪም ይታይባቸዋል። መንግስት ያስረኛል፣ ያንገላታኛል፣ ችግር ይደርስብኛል ብለው መስራትና መናገር ያላባቸውን በመተው ወደ ኋላ ሲሉ አልታዩም። በጊዜው ይፈሩ ለነበሩ ንጉሠ ነገሥት አልተሸቆጠቆጡም፤ ስህተት ሲሰሩ አይተው በዝምታ አላለፏቸውም።

በ1953 ዓ.ም በተደረገው የመንግስት ግልበጣ ሙከራ የተጠረጠሩትን ሰዎች ጃንሆይ እንዳሰሯቸው ሲሰሙ ሀዲስ ዝም አላሉም። የሰሩት ስራ መልካም አለመሆኑን በሰላ ብዕራቸው ገልጸውላቸዋል። በአስተዳደራቸው ላይ የነበረውን ችግርና ሌላውንም ሳይደብቁ በጽሁፍ አቅርበው ነበር። በጽሁፋቸው የአስተዳደሩን ጉድለት ከዘረዘሩ በኋላ ማሻሻያ ነጥቦችን ጠቁመዋል። መሻሻል የሚገባው ሳያሻሻል በቀር በዚህ ምክንያት ሰዎችን እየሰበሰቡ ማሰርና መቅጣት ተገቢ አለመሆኑን ገልጸዋል። ይሄን ፅሁፍ ያስታወሱ ጓደኛቸው መሀሪ ካሳ እንዲህ ብለዋል፡-

> በዚያን ጊዜ የነበረውን አስተዳደር አሻሽሉ ብሎ መጠየቅ በጣም ድፍረት ነው። ይሄ ትክክለኛነቱን፣ ለኢትዮጵያ ሕዝብ አስተዳደር አሳቢነቱን የሚያስረዳ ነው። (መሀሪ፣ ቃ.ም. ታህሳስ 2/1992)

የተጻፈላቸው ልዩ ማስታወሻ ያልተዋጠላቸው አፄ ኃይለ ስላሴ ሀዲስ ጽሑፉን አርመው እንዲያመጡ አዘዋቸው ነበር። አቶ ሀዲስ ግን ማረም እንደማይችሉ በድፍረት ተናግረዋል።

ሀዲስ ከትምህርት ሚኒስትር ብቻ ሳይሆን ከፕላን ሚኒስትርም ስራቸውን በፈቃዳቸው ለቀዋል። ይህም የዳፋርነታቸውና አስመስሎ ለመኖር ያለመቻላቸው ሌላ መግለጫ ነው። ከፕላን ሚኒስቴር ስራቸውን ሲለቁ ምክንያታቸው መንግሥት ባጀት አለመጨመሩ እንደነበር ለብዙ ዓመታት ያልተለዩዋቸው ዶክተር ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ስላሴ ገልጸውልኛል።

በቤት ውስጥ አስራ አምስት ዓመት አብራቸው የኖረች ወይዘሮ ባንቺ አምላከ እና ቤት ጠባቂያቸው /ዘበኛ/ አቶ ንጉሴ፤ ሀዲስ በቃላቸው እንደሚጸኑ ይናገራሉ። ቁጣ ካፋቸው የማይወጣና ደግነት የተላበሱ መሆናቸውንም ይመሰክራሉ።

ሀዲስ ባለቤታቸው ክበበጸሀይ ከሞቱ በኋላ ሌላ ሚስት አለማግባታቸው ከፍቅራቸው ባሻገር እምነታቸውን ጠብቀው መኖራቸውን ያሳያል። ዘመዶቻቸውና

ጓደኞቻቸው ከብቸኝነት እንዲላቀቁ ሚስት እንዲያገቡ ቢሉምድቸውም አሻፈረኝ ማለታቸውን የአጎታቸው ልጅ ወይዘሮ ስምረት የተናገሩት ነው። እንደ ሀዲስ የሞቀ ቤት ለያዙና ለተደራጁ ሰው ያለሚሥት መኖር አስቸጋሪ መሆኑን ሁሉም ይረዳዋል።

ደርግ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሆኑ በጠየቃቸው ጊዜም እንደ መንግስት ሃሳብ ሳይሆን እንደራሳቸው ሃሳብ ነው የመለሱት። «ሊሰራ የተፈለገው ነገር ካልተነገረኝና ቁጭ ብለን ካልተስማማን አይሆንም» ብለው ነበር። ባላመኑበት ጉዳይ ውስጥ እጃቸውን ላለማስገባት ስልጣኑን እንደማይቀበሉ በግልጽና በድፍረት ተናግረዋል።

ለሰው ማዘን፣ የተቸገረን መርዳት፣ ሰው ራሱን ችሎ እንዲኖር ማገዝና ደግነትም ዓበይት ባህርያቸው ናቸው። ሀዲሰ መኖሪያ ቤታቸውን ከባለቤታቸው ሞት በኋላ ለሕጻናት ማሳደጊያ እንዲሆን ለመንግሥት ሰጥተዋል። ቀጨኔ መድኃኔአለም አካባቢ «ክበበጸሀይ የህጻናት ማሳደጊያ» በሚል መጠሪያ ተሰይሞ ይገኛል። እናትና አባት የሌላቸው ሕጻናት ያድጉበታል፣ ይረዱበታል።

ሀዲስ ካገራቸው /ከጎጃም ገጠር/ የዘመድና ወዳጆቻቸውን ልጆች እያመጡ ያስተምሩ ነበር ምንም እንኳን የወለዱት ልጅ ባይኖርም፤ አስተምረው ራሳቸውን እንዲችሉ የረዷቸውን የመንፈስ ልጆቻቸው ግን በርካታ ናቸው። ለምሳሌ አበሻ ቦጋለ፣ ማዕድን ከበደ፣ ቦጋለ ከበደ፣ አለምጸሀይ ደስታ፣ ጽጌረዳና አበባና በስማቸው የሚጠ ራውን ስዩም ሀዲስን አስተምረዋቸው በአሁኑ ወቅት ከፊሎቹ በውጭ ሀገር ሲኖሩ ከፊሎቹ ደግሞ በሀገር ውስጥ በመንግስት ስራና በጡረታ ላይ ይገኛሉ።

> ከአገራቸው ከገጠር የእህት፣ ወንድም፣ ወዳጆቻቸውን ልጆች ከገጠር ያመጣሉ። በመኖሪያ ቤታቸው ግቢ ውስጥ አምስት ክፍል ሰርተዋል። ሦስቱን ሰሴቶች ሁለቱን ሰወንዶች መድበው እዚህ እያስቀመጡ ያስተምሯቸዋል፣ ሰቁም ነገርም አድርሰዋቸዋል። (ዘውዴ፣ ቃ.መ.፣ ኅደር 22/1992 )

ለትምህርት ያላቸው አመለካከት ከፍተኛ መሆኑን በተለያየ መልኩ ማስተዋል ይቻላል። ለዚህም ምስክሮች በየመጽሐፎቻቸው መግለጻቸው አንደኛው ሲሆን ሌላው በሕይወት ታሪካቸው ውስጥ የምናገኛቸው ሰዎች ናቸው። ሀዲስ ከትዳራቸው የተፋቱ እህቶቻቸውንም አስተምረው ደሞዝ ለሚያገኙበት ስራ አብቅተዋል። በመማራቸውም ዛሬ ከመንግስት ጡረታ እንደሚያገኙ ከሀዲስ ንግግር ተረድቻለሁ።

ኢሊባቡር መሬት ለማልማት የሄዱ ጊዜ ከአካባቢው ሰዎች ጋር ይቀራረቡ ነበር:: ከመካከላቸውም ቡኒ የተባለን ወጣት ሊያስተምሩት አዲስ አበባ ይዘው መጥተው፣ በኋላ ግን ደስተኛ ባለመሆኑ ወደ አገሩ መመለሱን ስሙንም አስታውሰው አውግተውኛል::

የሀዲስ ጓደኛ የሆኑት ብላታ መሀሪ ስለ ሀዲስ ደግነት ሲያነሱ የሰሩትን መልካም ሥራም አስታውሰው ነበር::

> «በጣሊያን ጦርነት ወቅት ተከትስውተ ከሄዱት ወጣቶች የሞቱ ነበሩ:: ስሚቸቹ ቤተሰቦች/እናቶች/ ባስማቋረጥ ገንዘብ ይከፍላቸው ነበር::» አሜሪካን አገር በነበረበት ጊዜ እንኳን በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል እየላከላቸው እኔ እከፍላቸው ነበር::(መሀሪ፣ ቃ.ም፣ ታህሳስ 2/1992)

ይህ ብቻ ሳይሆን ደጃዝማች እንቁስላሴና ወንድሞቻቸው በደርግ ከተገደሉ በኋላ ለሞቾቹ እናት ያለማቋረጥ በየወሩ አንድ መቶ ብር ይሰጧቸው እንደነበርም ብላታ መሀሪ ምስክርነታቸውን ገልጸዋል:: ወይዘሮም ስምረትም ስለ ደግነታቸው እንዲህ ብለዋል:-

> «የመረረ ቁጣ አውጥተው አያውቁም:: ሰፊ አስተሳሰብ ያላቸው፣ ቅን፣ ደግ፣ ማንም ሰው ራሱን ረድቶ ሰው ሆኖ ማየትን የሚወዱ ናቸው:: ደግነታቸውን ደግ ብዬ ስቆርጠው አያረካኝም:: (ስምረት፣ ቃ.መ፣ ጥር 26/1992)

ወይዘሮ ስምረት ስለ ሀዲስ ደግነት ሲናገሩ አንደበታቸው ብቻ ሳይሆን ፊታቸውና እጃቸውም ይናገራል:: ከሁሉም በላይ አዛኝ መሆናቸውን ቅንነት እግዚአብሔር አብዝቶ እንደሰጣቸው ደጋግመው ሲነግሩኝ እንባቸው ይወርድ ነበር::

ታላቁ ደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁ ራስን ከፍ ማድረግ አይወዱም:: ይህንን መገናኛ ብዙሃንም በየጊዜው የመሰከሩላቸው ነው:: ስለ ፍቅር እስከ መቃብር ታላቅነት ተነስቶ አድናቆት ሲቸረቸው ለራሳቸው ከመቀበል ይልቅ በአንድ ወቅት በሬዲዮ ለተረከው ወጋየሁ ንጋቱ እንደሚገባ ይናገራሉ:: ጓደኞቻቸው ድርስቶቻቸውን በተመለከተ ምን አይነት አስተያየት እንደሰጧቸው ስጠይቃቸው እንዲህ ብለዋል:-

> የእኔ ስነ ፅሁፍ ፍቅር እስከ መቃብር የገነነው ወጋየሁ ንጋቱ የሚባል ሰው በራዲዮ ከተረከው በኂላ ነው ሰው በድጋሚ እንዲያነበር የተገፋፋውም ከመጀመሪያ ጀምሮ በመተረኩ ነው:: /ሀዲስ፣ ቃ.መ ጥቅምት 10/1992/

ክቡር ዶክተር ደጃዝማች ዘውዴ ገብረ ስላሴ በውጭ ሀገር አብረዋቸው በነበሩበት ወቅት ከአቶ ሀዲስ ባህሪ ካስተዋሉት አንዱ ስራ ወዳድነታቸውን እንደነበር ገልጸዋል:: ትኩረታቸው ስራ ላይ ስለነበር በውጭ ሀገር ቆይታቸው አገር ጎብኝተው እንደማያውቁና ከሰው ጋርም እንደማይገናኙ አውግተውኛል ስለ አጠቃላይ ባሕርያቸውም:-

> መሠረታዊ ሃሳብን (Principle) የሚከተሉ ናቸው:: ፊት አይተው አይዘሳብዱም:: በሚያምኑበት ግትር ናቸው (እስከ መጨረሻው):: ማናቸውንም ነገር በቀላሉ አይቀበሉም:: አንድን ነገር ጥርት አድርገው ሳያውቁ ይህንን አውቃለሁ ብለው አይቆሙም:: (ዘውዴ፣ ቃ.መ.፣ ኀዳር 22/1992)

የሀዲስ የሕይወት ታሪክ በራሱ ባሕርያቸውን አጉልቶ የሚያሳይ ነው:: ያሳለፉትን ሕይወት በማስታወስ ምን አይነት ሰው እንደሆኑ ስለባሕርያቸው ለማወቅ አያዳግትም:: ዛሬም በዘጠና ዓመታቸው የቀድሞ ባሕርያቸው አልተለያቸውም:: አርቆ አስተዋይነታቸው፣ ደግነታቸው እና በራሳቸው አቋም መጽናታቸው ይነበባል::

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. ደራሲ ሀዲስ ከረዥም ልቦለዶቻቸው አራት ዋና ገፀባሕርያት ጋር ያላቸው ጥቂት ተመሳስሎ

በየጊዜው የሚታተሙት ልቦለድ መጽሐፎች ፈጠራ ቢሆኑም መነሻ አላቸው:: ጸሐፊው ለመጻፍ ሲነሳ ይዟቸው የሚነሳው ጉዳዮች አሉ:: በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚያውቀውን ይገልጸዋል:: አስተሳሰቡ፣ አኗኗሩ ይንፀባረቅባቸዋል:: ይህ ሲባል ግን ሁሉም ልቦለዶች የየደራሲዎቹ የሕይወት ታሪክ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ልብ ማለት ያሻል::

በደራሲያን የሕይወት ታሪክና የስነጽሑፍ ስራዎቻቸው ዙሪያ ተሰርተው ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል የቀረቡትን የጥናት ጽሑፎች ስናነብ የምንገነዘበው ጉዳይ አለ:: ይኸውም የደራስያኑ የሕይወት ታሪክ ከልቦለድ መጽሐፎቻቸው ጋር ያለው ተዛምዶ ነው:: ተዛምዶው በጥቂቶች ላይ ጎልቶ ሲንጸባረቅ በአንዳንዶቹ ደግሞ በጥቂቱ ተገልፆ እናያለን::

ደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁ ባሳተሟቸው ሦስት ረዣዥም ልቦለዶቻቸው /<u>ፍቅር እስከ መቃብር</u>፣ <u>ወንጀለኛው ዳኛ</u> እና <u>የልምዕዣት</u> / ውስጥ የሕይወት ታሪካቸው የተወሰነ ገጽታ ሲንፀባረቅ ይታያል:: በድርሰቶቻቸው አስተሳሰባቸውንም፣ ማንነታቸውን በቀረጿቸው ገጸ - ባሕርያት አማካኝነት በመጠኑም ቢሆን አመልክተዋል ማለት ይቻላል:: በዚህ ክፍል ከላይ በተጠቀሱት ሦስቱ ልቦለዶቻቸው ውስጥ ደራሲው ከዋና ገጸባህርያት ጋር ያላቸውን ጥቂት ምስስሎሽ ለማሳየት ተሞክራል::

### 3.1 ሀዲስ በ<u>ፍቅር እስከ መቃብር</u>

#### 3.1.1 የ<u>ፍቅር እስከ መቃብር</u> ታሪክ ባጭሩ

ጎጃም ዳሞት አውራጃ ማንኩሳ በምትባል ስፍራ የሚኖሩ ውድነሽ በጣሙ የተባሉ ሴት ነበሩ:: በየተራ ያገቧቸው ሦስት ባሎቻቸው ከሞቱ በኋላ በባል ተስፋ ቆርጠው በብቸኝነት ሲኖሩ በመጨረሻ በንስሀ አባታቸው ምልጃ ቦጋለ መብራቱን ያገባሉ:: በተጋቡ በሁለተኛው ዓመት በዛብህን ይወልዳሉ:: በዛብህ በልጅነቱ ጤነኛ አልነበረምና

የልጃቸው በሽታ ያሰጋቸው እናት ጤነኛ ከሆነ እድሚውን ሙሉ በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲያገለግል ይሳላሉ፣ ከበሽታው ይድናል። ስድስት ዓመት ሲሞላውም የቤተክህነት ትምህርት ይጀምራል። ትምህርቱን በጀመረ በሁለት ዓመቱ ዳዊትና ጾመ ድጓን ያጠናቅቃል። በድቁና በሚያገኘው ደሞዝ ወላጆቹን ሲረዳ ቆይቶ ከስለት ልጅነት ለመሸሽ ሲል ወደ ሌላ አገር ኮበለለ። እናትና አባቱ ልጃቸው ካጠገባቸው ከራቀ በኋላ በሀዘንና በሽታ ተሰቃይተው ይሞታሉ።

በዛብህ ዋሸራ በምትባል አገር ቅኔ ተቀኝቶ፣ ዝማሬ መዋሲትና ጽሕፈት ለመማር ደግሞ ወደ ዙር አምባ ያቀናል። ከዚያም 'መጽሐፍ ለመቀጸል' ወደ ደብረ ወርቅ አውራጃ አመራ። ደብረወርቅ ሳለ እመት ጠጅቱ ከተባሉ ሴት ጋር ተዋውቆ በቤታቸው ሲኖር የእናትና አባቱን ሞት ከማንሱሳ የመጣ ሰው ያረዳዋል። በዛብህ ጥቂት ካዘነ በኋላ የወላጆቹ ሞት እሱን ከስለት ልጅነት እንደፈታው በማመን ይደሰታል። ከዚህ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ያስባል። ወደ አዲስ አበባ ከመሄዱ በፊት ግን ዲማ በሚባለው ስመጥር አገር በቅኔ መምህርነት ለመመረቅ ወስኖ ወደዛው አቀና። በዲማ ቆይታው ከእሱ የትምህርት ደረጃ ዝቅ የሚሉትን እያስተማረ ለራሱም ቅኔ ይማር ነበር።

ፊታውራሪ መሸሻ በዲማ በታላቅነታቸው የተከበሩ ሰው ናቸው። አንድ ቀን በቤታቸው ባዘጋጁት ድግስ በዛብህ ከሌሎች ካህናት ጋር ተገኝቶ ወረብ ሲወርብና ስማቸውን እየጠራ ሲያወድሳቸው ተደስተው ይሸልሙታል። ከዛች ቀን በኋላ የቤታቸው ባለሟል ይሆናል። አዲስ አበባ የመሄድ ሃሳቡን ለውጦም የፊታውራሪ መሸሻን ልጅ ሰብለወንጌልን ማስተማር ይጀምራል። በዛብህ ሰብለን ሲያስተምራት ከተማሪና አስተማሪነት አልፈው ይቀራረባሉ፣ መፋቀር ደረጃም ይደርሳሉ። ድብቅ ፍቅራቸውን መጀመሪያ ያወቀው የሰብለ ወንጌል አክስት ልጅ ካሳ ዳምጤ / ጉዱ ካሳ/ ነበር።

የበዛብህና የሰብለ ፍቅር ለሌሎች ሰዎችም እንደተገለጸ ጉዱ ካሳ ለበዛብህ ይነግረዋል። የሰብለ አባት ከሄዱበት ሳይመለሱ ተያይዘው ወደ አዲስ አበባ እንዲጠፉም ይመክረውና ለጉዞ ቅድመ ዝግጅት ያደርጋሉ። ፊታውራሪ መሸሻ 'ሰብለ ከበዛብህ አረገዘች' የሚለውን ወሬ በሄዱበት ዘመቻ ሰምተው እነ በዛብህ ወደ አዲስ አበባ ለመሄድ ካሰቡበት አንድ ቀን ቀደም ብለው ቤታቸው ይደርሳሉ። እቤት እንደደረሱም ሰብለን ስለ ሁኔታው ሲጠይቋት እውነቱን ስትነግራቸው ተደፈርኩ በማለት ያስሯታል።

በዛብህ የሰብለን መታሰር ሲሰማ እጅግ በጣም ያዝናል:: ፊታውራሪ ካገኙት እንዳይጎዱት አዲስ አበባ መሄድ እንደሚበጀው ፣ ሲመቸው ሰብለን እንደሚያመጣለት በማስረዳት ጉዱ ካሳ በዛብህን ይመክረዋል:: በዛብህም ምክሩን ተቀብሎ አዲስ አበባ ይሔዳል:: አዲስ አበባ ከደረሰ በኋላ ከአገሩ ልማድ ጋር እስኪግባባ ትንሽ ግር ይለዋል:: ከጎጃም አዲስ አበባ ሲመጣ በጉዞው ላይ የተዋወቃቸው ነጋድራስ ሁነኛው ሩፋኤል ቤተክርስቲያን በሚያውቋቸው ደብተራ አማካኝነት በዛብህ ከደብሩ አለቃ ጋር እንዲገናኝ ይረዱታል፤ በዛምህም የቅኔ መምህር ይሆናል:: ሰብለ ስትመጣ እንዳትቸገር በማለት ትልቅ ግቢ ያለው ቤት ተከራይቶ ይጠብቃታል::

የጎጃም ነጋዴዎች የሚሰፍሩበት መደብር ሲመላለስ አንድ ቀን ሁለት ነጋዴዎች በመንገድ ላይ ሲያወሩ ዲማን በመጥቀሳቸው ተከትሎ ማንነቱን ሳይገልፅ ስለፊታውራሪ መሸሻ ቤተሰብ ይጠይቃቸዋል:: ሰብለ ልታገባ ሰርግ በመደገስ ላይ መሆናቸውን ሲነግሩት ይደነግጣል:: ነጋዴዎቹ ወደ አገራቸው ከመሄዳቸው በፊት ለሰብለ የፃፈውን ደብዳቤ ለጉዱ ካሳ እንዲያደርሱለት ይሰጣቸዋል:: በደብዳቤውም ለእሷ ያለውን ፍቅርና እሷን በማጣቱ ቆርቦ በብቸኝነት ለመኖር ማሰቡን በግጥም ይገልጻል::

ሰብለ ደግሞ በሰርጓ ዋዜማ ምሽት ጠባቂዋ አባ ተክለሃይማኖት ራሳቸውን እስኪስቱ ሰክረው ነበርና ያወለቁትን ልብስ ለብሳ መነኩሴ በመምሰል ከቤት ትጠ ፋለች:: የሰርጓ እለት ጠዋት አጃቢዎቿ ሊቀሰቅሷት መኝታ ቤቷ ሲደርሱ ያጧታል:: በእሷ ምትክ አልጋዋ ላይ የተጋደሙት አባ ተክለሃይማኖት ናቸው:: የሰብለን መጥፋት የሰሙ ወላጆቿም ሀዘን ተጭኗቸው ፍለጋ ይሄዳሉ:: በመንገድ ላይም ፊታውራሪ መሸሻ ከፈረስ ወድቀው አለት ድንጋይ ይመታቸውና ወዲያው ያርፋሉ:: ወይዘሮ ጥሩ አይነትም ከቤተክርስቲያን ደረጃ ላይ ተፈጥፍጠው ይሞታሉ::

ሰብለ መነኩሴ እንደመሰለች ከቤቷ ወጥታ በእግሯ በመጓዝ ከብዙ ስቃይ በኋላ ከነጋዴዎች ጋር አዲስ አበባ ትገባለች:: አዲስ አበባ እንደደረሰች ወደ ሩፋኤል ቤተክርስቲያን በማምራት ስለበዛብህ ስትጠይቅ መጥፋቱ ይነገራታል:: ከቤተ ክርስቲያን ወጥታ መንገድ ትጀምራለች:: በመንገድም ወደ አንዲት ጎጆ በማምራት ሁለት ሦስት ቀን እንዲያሳርፏት ባለቤቲቱን ጠይቃ ወደ ወስጥ ትዘልቃለች:: በእዛም ታሞ ለተኛው በሽተኛ ውሃ ለማቀበል ስትቀርበው በዛብህ ሆኖ ታገኘዋለች፣ ተያይዘው ይላቀሳሉ:: አምስት ቀናትን አብረው ሲያሳልፉ በቃል ኪዳን ቆርበው ከተጋቡ በኋላ በዛብህ ይሞታል::

ጉዱ ካሳ ከጎጃም ተነስቶ በጉዞ ላይ ሳለ በመንገድ ወዳያት ቤተክርስቲያን በማምራት ግቢ ውስጥ ሲፀልይ የመነኩሲት ድምፅ ይሰማል፡፡ ሊጠይቃቸው ሲቀርብ መነኩሲቷ ሰብለ መሆኗን አላወቀም ነበር፡፡ ሰብለ ግን አውቃው ማንነቷን ገለጻለት ይላቀሳሉ፡፡ አስራ አምስት ቀናት አብረው ከቆዩ በኋላ ሰብለ ትሞታለች፣ እሷ በሞተች በሦስተኛው ዓመት ደግሞ ጉዱ ካሳ ይከተላታል፡፡

### 3.1.2 ሀዲስና በዛብህ

የወይዘሮ ደስታና የአቶ ዓለማየሁ ብቸኛ የጋራ ልጅ ሀዲስ ናቸው፡፡ የሀዲስ እናት ወይዘሮ ደስታ ከባለቤታቸው ከአቶ ዓለማየሁ ጋር ከተለያዩ በኋላ ሌሎች ልጆች ቢወልዱም፣ አቶ ዓለማየሁ ግን ከሀዲስ በቀር ሌላ ልጅ የላቸውም፡፡ የፍቅር እስከ መቃብር ዋና ገፀባህሪ በዛብህም ለእናትና አባቱ የመጀመሪያ ብቸኛ ልጅ ነው፡፡ የደራሲ ሀዲስና የገፀባህሪው በዛብህ የትውልድ አገራቸው ጎጃም ነው፡፡ የቤተ - ክህነት ትምህርት በመማር ረገድም ሁለቱን የሚያመሳስላቸው አለ፡፡ ይኸውም ፊደል ቆጥረው፣ ዳዊት ደግመው፣ ዜማ መማራቸውና የቅኔ ትምህርታቸውን ያጠናቀቁበት ቦታ ጎጃም ውስጥ በሚገኝ፣ ዲማ በሚባል ደብር መሆኑ ነው፡፡

የዲማ ትልቅነት በፍቅር እስከ መቃብር ገፅ 71 ላይ ተጠቅሷል፡፡ በዛብህ ዲማ ስመጥር በመሆኑ ቦታውን ሲያይ ያደንቃል፡፡ ሀዲስም ቃለ መጠይቅ ባደረግኩላቸው ወቅት የዲማን ትልቅነት ሲገልጹ «ዲማ ትልቅ ደብር ነው፡፡ የዛ መምህር መሆን ደግሞ ትልቅ ደረጃ ነው፡፡ ከብዙ አገር ወደ ዲማ እየሄዱ የሚማሩበት አገር ነው፡፡» /ኅዳር 1/1992 ቃ.መ./ ብለዋል፡፡

ሀዲስም ሆኑ በዛብህ በድቁና አገልግለዋል፡፡ የቤተክህነት ትምህርታቸውን በሁለት መምህራን ማጠናቀቃቸውም ያመሳስላቸዋል፡፡ የበዛብህ መምህሮች አለቃ ኑሬና አለቃ ክንፉ ሲሆኑ የሀዲስ  ደግሞ መምህር ገብረስላሴና መምህር በላይ ነበሩ፡፡ በዛብህ ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ በአጋጣሚ ከፊታውራሪ መሸሻ ለመሰወር ይሁን እንጂ ከሰብለ ጋር ከመገናኘቱ በፊት የቤተክህነት ትምህርቱን ለማሳደግ መሄድ እንዳለበት አስቦ ነበር፡፡ ሀዲስም መምህር በላይን ተከትለው ወደ አዲስ አበባ ያቀኑት በነበራቸው የቤተክህነት ትምህርት ላይ እውቀት ለመጨመር፣ ለማሳደግ ነበር፡፡ ሀዲስ ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ አበባ የገቡት በእግራቸው ተጉዘው ሲሆን በዛብህም አዲስ አበባን ለመርገጥ ከጎጃም ጀምሮ በእግሩ ተጉዟል፡፡

በዛብህ አዲስ አበባ ከመጣ በኋላ መንገድ ለመንገድ እየዞረ እንግዶች የሆኑበትን ሱቆች ይመለከታል/ ገጽ 434/ ሀዲስ ከጓደኞቻቸው ጋር በመሆን ያለምንም ስራ ሱቆችን ለማየት ይዞሩ እንደ ነበር ተናግረዋል::

በዛብህ ያፈቀራት ልጅ የሰብለ የዘር ግንድ አባቷ እንደሚሉት ከነገስታት ወገን ነው::/ገጽ 184/ የሀዲስ ባለቤት ክበበ ጸሀይም የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዘመድ መሆናቸውን ከሀዲስ ጓደኛ ከክብር ዶ/ር ደጃዝማች ዘውዴ ጋር ካደረግኩት ቃለ ምልልስ ተረድቻለሁ:: በዛብህ ለሞት በቀረበ ሰዓት ቢሆንም ከሰብለ ጋር ቀርበው ተጋብተዋል::/ ገጽ 548 / የሀዲስና የባለቤታቸው ጋብቻም በቁርባን ነበር፡ በዛብህ ሰብለን በማጣቱ ሌላ ሚስት አግብቼ አልኖርም እንደ[redacted]ው ሀዲስም ባለቤታቸውን በሞት ከተነጠቁ ጀምሮ እስካሁን ሌላ ሚስት ሳያገቡ በብቸኝነት ይኖራሉ:: እናም ሁለቱም በአንድ ሴት መጽናታቸው ያመሳስላቸዋል::

### 3.1.3 ሀዲስና ጉዱ ካሳ

በፍቅር እስከመቃብር መጽሀፍ ውስጥ የምናገኘው አንዱ ዋና ገጸባህሪ ካሳ ዳምጤ በቤተክርስቲያን እያገለገለ እንጂ እንደ ደራሲው በቤተክህነት ተምሯል:: በሚያነሳቸው ሃሳቦች ምጥቀት የዘመኑን ስርዓት፣ ማኅበረሰቡን በግልጽ በመቃወሙ በአካባቢው ሰው 'ጉድ' በመባል ተጠርቷል:: ምክንያቱም ሌሎች የሚፈሩትን እሱ በድፍረት ይናገራል፤ ስርዓቱን በግልጽ ይቃወማል::/ ገጽ 122/ ሀዲስም የነበሩበትን ስርዓት ይቃወሙ ነበር:: በወቅቱ ለነበሩት ንጉሥ አስተዳደራቸው ስህተት እንዳለበት በጽሁፍ ገልጸውላቸዋል::

ለፊታውራሪ መሸሻ ስድብ የሚመስላቸው የጉዱ ካሳ ቁም ነገር አዘል ንግግር / ገጽ 412 / ጃንሆይም የሀዲስ 'ልዩ ማስታወሻ ' ን (ኢትዮጵያን እንዴት ማስተዳደር እንዳለባቸውና ያለውን ሕጸጽ የገለፁበትን ጽሁፍ) እንደዘለፋ ቆጥረው 'ሰድቦኛል' በማለት ጠርተው ሀይለቃል ተናግረዋቸው ነበር::

ሀዲስም ሆኑ ጉዱ ካሳ የሰውን ጥቃት፣ የሰውን መገፋት አይወዱም:: ጉዱ ካሳ ፊታውራሪ መሸሻ ባላገሮቹን ሲያንገላቷቸው ሲያይ በዝምታ አላለፈም:: ትክክል እንዳልሆኑ ፊት ለፊት ነግሯቸዋል:: (ገጽ 221) ሀዲስ ከኒውዮርክ የተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ሲመለሱ በ1953 በነበረው መፈንቅለ መንግሥት የተጠረጠሩት

ጓደኞቻቸው ያለ ጥፋታቸው መታሰራቸውን ሲሰሙ ለጃንሆይ ስህተት መስራታቸውን በግልፅ አስረድተዋቸዋል::

ጉዱ ካሳ በነበረበት ዘመን ሰዎች ይንቋቸውና ያንቋሸሿቸው ከነበሩት ባሮች አንዷን አግብቷል:: አብረውት ይኖሩ የነበሩ ባሮችን አስተምሯል:: (ገጽ 341) ሀዲስ ደግሞ ኢሉባቡር መሬት በሚያለሙበት ወቅት 'ሻንቅሎች' የተባሉትን ተግባብተው ቡኒ የተባለን ወጣት ወደ አዲስ አበባ ይዘውት በመምጣት በኋላ እምቢ ብሎ ቢሄድም በቤታቸው አኑረው አስተምረውታል::

ፍቅር እስከ መቃብርን በጻፉበት ወቅት ስርዓቱን በግልጽ በመቃወም እንደልቡ የሚናገር የጉዱ ካሳ አይነት ባህርይ የነበረው ሰው በእውኑ ዓለም ያውቁ እንደሆነ ሀዲስን ለጠየቅኳቸው «እኔ የምጠላውን የማልፈልገውን ነገር እኔ ልለው የሚገባኝን ነገር አንድ ሰው ፈጥሬ እሱ እንዲናገረው አደርጋለሁ እንጂ እንደዚህ ያለሰው አልነበረም» በማለት መልሰውልኛል::

## 3.2 ሀዲስ በ ወንጀለኛው ዳኛ

### 3.2 .1 የወንጀለኛው ዳኛ ታሪክ ባጭሩ

ጥላሁን ፈይሳ በሕግ ትምህርት፣ ሶፊያ ሙላት በመምህርነት ኮርስ ኰሌጅ ተማሪ ሳሉ ተዋውቀው ጓደኛሞች ይሆናሉ:: ጥላሁን በአንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በክፍል ውስጥ አንደኛና ሁለተኛ የሚወጣ ጎበዝ ተማሪ ነበር:: በኮሌጅ ትምህርቱም ጉብዝናው የተደነቀለት ሆኖ ሳለ ባላሰበው መንገድ በመጨረሻ ዓመት ፈተና መውደቁን ሲሰማ በጣም ይደነግጣል:: ለመውደቁ ምክንያት ጓደኛው ወንድ ይራድ ነበር:: ወንድይራድ ሶፊያን የሚያውቃት ሀረር ሁለተኛ ደረጃ አብረው ሲማሩ ቢሆንም ጓደኛው እንድትሆንና እንዲጋቡ ቢጠይቃት ፈቃደኛ ባለመሆኗ ይበሽቃል:: እናም የምትወደውን ጥላሁንን በማጥፋት ሊበቀላት ቆርጦ ይነሳል:: ጥላሁን ትምህርቱን ጨርሶ ስራ ካልያዘ ሶፊያን አያገባትም በሚል አስተሳሰብ አንትዋን ለተባለው የኮሌጅ መምህር ገንዘብ በመስጠት ከፈተና እንዲወድቅና እንዲያቋርጥ በደል ይፈጽማል::

ጥላሁን ትምህርቱን በድጋሚ ተምሮ እንዲያሻሽል ትምህርት ቤቱ አለመፍቀዱን ሲያረጋግጥ ስራ ማፈላለግ ይጀምራል:: ትምህርት ሚኒስቴር ውስጥ ባገኘው ስራም

ኢሉባቡር፣ የኪ በምትባል የወረዳ ከተማ በመምህርነት ተቀጥሮ ለመሄድ ይቆርጣል:: ሶፊያም ተከትላው ልትሄድ መዘጋጀቷን ትገልጽለታለች:: ለጉዞው የሚያስፈልጋቸውን ቅድመ ዝግጅት አጠናቅቀው ወደ ኢሉባቡር ከማምራታቸው በፊት እማኝ በሌለበት ሁለቱ ብቻቸውን በቤት ውስጥ ጋብቻቸውን ይፈጽማሉ:: የኪ ከደረሱ በኋላ የሚሰሩትን ልማት ከወዲሁ አስበው ይዘጋጃሉ:: ከመሄዳቸው በፊት ግን ጥላሁን የተመደበበት ያስተማሪነት ቦታ ከእሱ በፊት ለሌላ ሰው መስጠቱን በትምህርት ሚኒስቴር ሠራተኛ የሆነው ማሞ ወልደተንሳይ ቤታቸው ድረስ በመሄድ ያረዳቸዋል::

የመምህርነት ስራውን ያጣው ጥላሁን ለጊዜው ቢደናገጥም ውብቱ በዛብህ የተባለ ጓደኛውን አስታውሶ ይጽናናል:: ውብቱ በዛብህ ከሁለተኛ ደረጃ ጀምሮ ጓደኛው ነበር:: በኢሉባቡር ጎሬ ለጥላሁን ርስት እንዲገዛለት ስለነገረው ይህንኑ ለሶፊያ ነግሯት በመሬቱ ሊተዳደሩ ወደዛው ያመራሉ:: ጥላሁንና ሶፊያ ከአዲስ አበባ ኢሉባቡር ሲጓዙ ወንድይራድ መንገድ ላይ ጠብቆ ሊያስገድላቸው ይሞክራል:: እነሱ ግን በሚሄዱበት የጭነት መኪና ሸራ ውስጥ ተደብቀው ነበር:: ሊገድላቸው የመጣውን ሰውም ጥላሁን ቀድሞ በመያዝ ያስረዋል:: ወንድይራድንም ይዞ ካስፈራራውና ካናዘዘው በኋላ እዛው ትቶት መንገዳቸውን ይቀጥላሉ::

ኢሉባቡር ጎሬ ደርሰው ውብቱ በዛብህ ቤት ጥቂት ከሰነበቱ በኋላ ውብቱ መሬታቸውን ሊያስረክባቸውና ከየኪ ሹማምንቶች ጋር ሊያስተዋውቃቸው ተያይዘው ወደ የኪ ያመራሉ:: በእዛም ግራዝማች ዳኛቸው ፍሪሳ ከተባሉ ከወረዳው ገገር ጋር ይተዋወቃሉ:: ውብቱ የገዛላቸው መሬት የሚያፈራውን ቡና እያስለቀሙ በመሸጥም ብዙ ገንዘብ ያገኛሉ:: ካላቸው አምስት ጋሻ መሬት አንዱን ጋሻ ብቻ ለራሳቸው አስቀርተው አራቱን መሬት ለሌላቸው ሰዎች ያከፋፍላሉ:: የየኪን ሕዝብ በማስተማርና ቀላል የሕክምና አገልግሎት በመስጠትም ረድተዋል::

ጥላሁን የየኪ ወረዳ ገገር የሆኑት ግራዝማች ዳኛቸው የቀኛዝማችነት ሹመት ከተቀበሉ በኋላ ስለ ስራቸው ሊያነጋግራቸው ቢመላለስ ፈቃደኛ አልሆኑም:: አንድ ቀን ግን ሊያነጋግሩት ስለሚፈልጉ ጽሕፈት ቤታቸው ድረስ እንዲመጣ ያስጠሩታል:: እለቱ ሌሎች ሰዎችንም ሰብስው ጉባኤ የሚያካሂዱበት ነበር:: በጉባኤው ጥፋት ሰርተዋል የተባሉ ሰዎች ጥፋታቸው እየተነገራቸው ይጻፋል:: ጥላሁንም ከባለቤቱ ሶፊያ ጋር ፈጸመ የተባለው ወንጀል ይነገረዋል:: አካባቢውን ማልማታቸው እንደጥፋት መቆጠሩ

ትክክል አለመሆኑን ቢያስረዳም ሰሚ አያገኝም:: በመጨረሻ መታገስ ሲያቅተው የቀኛዝማች ዳፕን ስህተት በመግለፅ ሀጢያታቸውን ይነግራቸዋል::

ቀኛዝማች ዳኛቸው ጥላሁንን ጽሕፈት ቤታቸው ውስጥ ባነጋገሩበት ማግስት 'ነፍጠኞቻቸውን' ልከው ያስጠሩታል:: ቤታቸው እንደደረሰም እንግዳ ቤት በሚሉት ሰፊ አዳራሽ ውስጥ ያስሩታል:: ሶፊያ የጥላሁንን መታሰር የሰማች እለት ይገድሉታል በማለት ስትጨነቅ፣ ከመታሰሩ በቀር ምንም አይነት ጉዳት እንዳልደረሰበት ትሰማና ትረጋጋለች:: ጥላሁን በታሰረበት ሌሊት ቀኛዝማች ጭፍሮቻቸውን አስከትለው ሶፊያ ያለችበት ቤት ድረስ በመሄድ የተዘጋውን በር አስከፍተው ወደ ውስጥ ይዘልቃሉ:: ቀኛዝማች አብረዋቸው የነበሩትን ሰዎች በኋላ እንዲመጡ ያዟቸዋል:: ሶፊያንም አጠገባቸው እንድትቀመጥም አዘዋት ከተቀመጠች ከትንሽ ቆይታ በኋላ ክኒን ልዋጥ በማለት ተነስታ ወደ መታጠቢያ ቤት ታመራለች:: ከዚያ አልጋ ላስተካክል በማለት ወደ መኝታ ቤት ትገባለች:: ይህን ሁሉ ስታደርግ ቀኛዝማች ይከተሏት ነበር:: በመጨረሻ አዘናግታ በሽጉጥ ታቆስላቸዋለች::

እፀገነት የተባለችውን ሴት ቀኛዝማጅ ዳኛቸው ጥላሁን ፈይሳ ከተባለ ባልዋ ነጥቀው ያገቧት ባለቤታቸው ናት:: ጥላሁንን የታሰረበት እንግዳ ቤት ድረስ በመሄድ ትጠይቀውና ታጽናናው ነበር:: ቀኛዝማች ከቤት ሲወጡ የታሰረበት ቤት ሄዳ እንደምትወደው ስትገልጽለት ባሏን ስለሚመስላት መሆኑን ጥላሁን በርጋታ ይነግራታል:: ከባሏ ጋር እንዲያገናኛት የታሰረበትን ሰንሰለት ፍችልኝ ይላታል:: እፀገነት ጥላሁንን እንደፈታችው ቀኛዝማች በጥይት የቆሰለ ሆዳቸውን ይዘው እየተንገዳገዱ ይገባሉ:: ጥላሁን የገዛ ሽጉጣቸውን በመንጠቅ ተኩሶ ይገድላቸውና በጓሮ በር ይወጣል:: እፀገነትም ቀድማ ወጥታ ነበር::

ጥላሁን ቀኛዝማችን ከገደለ በኋላ ወደ ሶፊያ ያመራል:: ከሶፊያ ጋር ስለተፈፀመው ነገር ሲያወሩ ባላምባራስ ጉደታ ይመጣሉ:: ባላምባራስም የሆነውን ነገር ሰምተው ነበርና እንዲሸሹ ይመክሯቸውና ወደሚሸሸጉበት ዋሻ ይወስዷቸዋል:: በዛም ጥቂት ቀናት ቆይተው ሚዛን ተፈሪ ወደሚገኙት የባላምባራስ አጎት ቤት ያመራሉ:: ሚዛን ተፈሪ ሲቀመጡ ስማቸውን ለውጠው ነበርና ማንም አላወቃቸውም ስለእነሱ የሚወራውን ወሬ እየሰሙ በስጋት ከሰነበቱ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ሲሄዱ ባላምባራስ ጉደታ መርቀው ይሸኟቸዋል::

ሶፊያና ጥላሁን አዲስ አበባ ሲኖሩም ስማቸውን ቀይረው ነበር፡፡ የቀኛዝማች ዳኛቸውን ገዳይ ለማግኘት ምርመራ በሚካሄድበት ፍርድ ቤት ውስጥ ጥላሁን ማንነቱን ደብቆ 'አንተነህ' በሚል ስም እየተጠራ ሰብሳቢ ዳኛ ሆኖ ይሰራል፡፡ ቀኛዝማች ዳኛቸውን በመግደል የተጠረጠሩት እፀገነትና የቀድሞ ባለቤቷ ጥላሁን ፈይሳ ለፍርድ በቆሙበት ችሎት ጥላሁን በመጨረሻ ራሱን ያጋልጣል፡፡ ሶፊያም ፍርድ ቤት ከተሰበሰበው ሰው መሀል በመውጣት እሷም በግድያው ተባባሪ መሆኗን ትናገራለች፡፡ ሶፊያና ጥላሁን በማረፊያ ቤት እንዲቆዩ ፍርድ ቤቱ ወስኖባቸው እዛው ይሰነብታሉ፡፡ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ ግድያውን የፈፀሙት «ከህገወጥ ለመዳንና ራሳቸውን ለመከላከል ነው» በሚል በነፃ ይለቃቸዋል፡፡

INSTITUTE OF ... STUDIES
FOREIGN LANGUAGES

### 3.2.2 ህዲስና ጥላሁን

ጥላሁን የወንጀለኛው ዳኛ ዋና ገጸባህሪ ነው፡፡ በዩኒቨርስቲ የሕግ ትምህርቱን ሲከታተል ወንድይራድ የተባለ ጓደኛው ከመምህሩ ጋር በሸረበበት ተንኮል ሳያጠናቅቀው ለማቋረጥ ይገደዳል፡፡ የወንጀለኛው ዳኛ ደራሲ ህዲስም ትምህርታቸውን ያቋረጡበት ምክንያትና የተማሩበት ትምህርት ቤት ከጥላሁን ይለይ እንጂ የሕግ ትምህርት በአሜሪካ ዩኒቨርሲቲ መከታተል ጀምረው በስራ ምክንያት ወደ ሌላ አገር በመሄዳቸው ሳይጨርሱ አቋርጠዋል፡፡

ጥላሁን ስለትምህርትና ተማሪ ያወራል፡፡/ ገፅ 37/ ህዲስም በዚሁ መጽሐፍ መግቢያና የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም በተባለው መጽሀፋቸው ስለ ትምህርት ያላቸውን አመለካከት ጽፈዋል፡፡ ህዲስ በመምህርነት ያገለገሉት ከትምህርት ቤት በረብሻ ምክንያት በመባረራቸው እንደ ነበር ገልፀውልኛል፡፡ ጥላሁንም በመምህርነት የተቀጠረው ትምህርቱን በማቋረጡ ስራ ማግኘት ግዴታው ስለሆነ ነበር፡፡ ለማስተማር በተመደበበት አገር በኢሉባቡር ጓደኛው ውብቱ ርስት ገዝቶለታል፡፡ /ገፅ 68/ ለህዲስም በኢሊባቡር ያለሙትን መሬት የገዙላቸው ወዳጃቸው አቶ አበበ ነበሩ፡፡

ህዲስ የሌሎች ሰዎችን መበደል እንደማይወዱ የሕይወት ታሪካቸው ያስረዳል፡፡ ይኸውም በምዕራፍ ሁለት የጠቀስኩት በ1953 መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ያላግባቡ ጓደኞቻቸው መታሰራቸውን ሲሰሙ ጃንሆይ ፊት በመቅረብ ነፃ ማውጣታቸው ምስክር ነው፡፡ ጥላሁን ደግሞ በወንጀለኛ ዳኛ ገጽ 91 እንደተጻፈው ከገጠር የመጡ ሰዎች

ገንዘባቸውን ሌባ ሲሰርቃቸው ሚስቱ ሶፊያ በማየቷ ስትነግረው ከሌሎቹ ጋር ተደባድቦ ገንዘቡን ተቀብሎ ለባለቤቱ መልሷል።

በወቅቱ ስለነበረው የፊውዳሊዝም ስርዓት ጥላሁንና ሀዲስ ተመሳሳይ ተቃውሞ ነበራቸው። ሀዲስ የንጉሥ ኃይለስላሴ አስተዳደር ስህተት እንዳለበት በጽሑፍ ገልጸውላቸዋል። ጥላሁን ደግሞ በመንግሥት ፍርድ እንደተበሳጨ በገጽ 218 ተጽፏል። ከብስጭት አልፎ በኢሉባቡር የየኪ ሕዝብ የሚፈራቸውን ቀኛዝማች ዳኛቸውን መልካም እንዳልሰሩ ፊት ለፊት ነግረቻቸዋል። (ገጽ 322/) ሀዲስ ለጃንሆይ ስህተት መስራታቸውን ሲገልፁላቸው ሰደብከኝ እንዳሏቸው ቀኛዝማች ዳኛቸውም ጥላሁንን እንዲሁ ብለውታል። (ገጽ 323) ጥላሁን ኢሉባቡር ሲኖር የአካባቢውን ተወላጆች (ሻንቅሎችና ጣማዎችን) ሳይንቅ ደስታና ሀዘናቸውን አብሮ ተካፍሏል። (ገጽ 268) ሀዲስ ኢሉባቡር መሬት በሚያለሙበት ወቅትም ከአገሬው ተወላጆች ጋር ይቀራረቡ እንደ ነበረ ገልፀውልኝ አብረዋቸው የተነሱትን ፎቶም አሳይተውኛል።

## 3.3 ሀዲስ በየልምጕርት

### 3.3.1. የየልምጕርት ታሪክ ባጭሩ

ደመቀች ጸሀይ በጎጃም ክፍለ ሀገር እንዶዳም ኪዳነምህረት በሚባለው አካባቢ ተወልዳ ታድጋለች፤ በዘጠኝ ዓመቷም ወላጆቿ ታምራት ተገኝ ለሚባል አምስት አግብቶ ለፈታ የሃምሳ ዓመት ሰው በ'ማደጎ ጋብቻ' ይድሯታል። ታምራት በአካባቢው የተፈራና የተከበረ እውቅ ሀብታም ቢሆንም የደመቀች አባት ባሻ ጸሀይ በዘር እንደማይተካከላቸው አስበውታል። ሀብቱን ፈልገው ግን ልጃቸውን አሳልፈው ይሰጡታል። ታምራትም እስከ አስራ ሦስት ዓመቷ ሊጠብቃት ለወላጆቿ የገባውን መሀላ በማፍረስ በአስር አመቷ ወሲብ ይፈጽምባታል፤ በአስራ ሁለት ዓመቷ ልጅ ትወልዳለች።

ደመቀች በሕፃን ገላዋ ባሏ በፈፀመባት ወሲብ ምክንያት ትዳሯን ትጠላለች። ወላጆቿ ቤት ለመውለድ በሄደች ጊዜ ወደ ባሏ መመለስ እንደማትፈልግ ለእናትና አባቷ ብትገልጽም አባቷ ሃሳቧን አይደግፉም፤ በግድ እንደሚመልሷት ስትረዳ አክስቷ ቤት መሄዷን ለእናትዋ ነግራ ከቤት ትወጣለች። ከዛች ቀን በኋላ ወደ ቤቷ አልተመለሰችም፣ አገሩን ጥላ ትሰደዳለች። በስደቷ ወቅት መቃብር ቤት የሚኖሩ መነኩሳትን በቤተክርስቲያን ውስጥ ስታይ ከትዳር ለመገላገል መመንኮስ ታስባለች።

ሃሳቧን ለመነኮሳቱ ስትነግራቸው ግን እንደማትችል ይነግሯታል:: ከእነሱ ጋር ጥቂት ቀን ከሰነበተች በኋላ አዲስ አበባ በግርድና ተቀጥራ እንድትኖር እዛው የሚያደርሳት ሰው በማግኘታቸው በአደራ ይልኳታል::

አዲስ አበባ ከደረሰች በኋላ ስራ ለመፈለግ ስትዞር ካረፈችበት ቤት ርቃ በመሄዷ አካባቢው ይጠፋባታል:: አንዲት አሮጊት አግኝታ የሰፈሩን ስም ስትነግራቸው ስላወቁት ሊያደርሷት በጋሪ ሲሄዱ ደመቀች በመንገድ ላይ ባሏን ታምራትን በማየቷ ትደነግጣለች፤ እሱ ግን አላያትም ነበርና ይተላለፋሉ:: አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ደመቀች የሰው ቤት ስራ (ግርድና) በማግኘቷ ተቀጥራ ትሰራለች:: በዚህም ከባሏ ለመደበቅ በመቻሏ ስትደሰት ከእመቤቷ ከወይዘሮ ጽጌ ጋር በልጇ ምክንያት በመጣላታቸው ከቤታቸው ያባርሯታል:: የቤቱ አለቃ የነበሩ አዛዥ ተካለኝ ደመቀችን ስታለቅስ አይተዋት በማዘን ቤታቸው ያስጠጓታል:: አዛዥ ተካልኝ ቤት ሳትኖር ልጇን ተፈሪ መኮንን አዳሪ ትምህርት ቤት ኃላፊውን ተለማምጣ ታስገባዋለች:: አንድ ቀን ለልጇ ልብስ ለመግዛት ከአዛዥ በሚያውቁት ልብስ ሰፊ አማካኝነት በሻህ ከተባለው ሰው ጋር ልብስ እንዲያጋዛቸው ይተዋወቃሉ::

በሻህ መተዳደሪያ የሌለው፣ አግብቶ የፈታ፣ በጣሊያን ጦርነት ወቅት በአርበኝነት የሰራ፣ በሰው ላይ ግፍ የዋሉትን ከአበሮቹ ጋር በመሆን የዘረፈና ያዘረፈ፣ በወቅቱ የነበረውን ስርዓት የሚነቅፍ ሰው ነበር:: እነደመቀችን ከተዋወቀ በኋላ አዛዥ ቤት በመመላለስ ቤተኛ ይሆናል:: ከደመቀች ጋርም ይቀራረባሉ:: ደመቀች ከእሱ በፊት ለወሲብ የከጀሏትን ወንዶች እንዳልሸሸችና በቅጣት እንዳልመለሰች በበሻህ ጀግንነትና መልካም አሳቢነት ተማርካ በፍቅር ትወድቃለች:: አዛዥ ተካልኝ ቤት ሲመጣ በተዋወቀችው በአዝማሪው ውቤ ፈላጊነት ሐኪም ቤት ውስጥ የዕዳት ስራ ታገኛለች:: በእዛም እየሰራች በሻህ የማታ ትምህርት እንድትጀምር ይመክራታል:: ምክሩን ተቀብላ በእሱው እርዳታ ትምህርት ቤት ትገባለች::

ደመቀች ልጇ አዳሪ ትምህርት ቤት ከገባ በኋላ የጠየቃትን ሁሉ ከመፈፀም ወደ ኋላ አላለችም:: ገንዘብ ባይኖራት እንኳን ተበድራ ግዥ ያላትን ነገር ትገዛለች:: ልጇ ተከስተ ግን አንድ ቀን በጓደኛው ቤት ግብዣ ላይ የጓደኛው አባትና ሌሎች ሰዎች ስለ እናቱ ሲጠይቁት ድህነቷ አሳፍሮት 'ሰራተኛችን ናት' በማለት እናትነቷን ይክዳል:: ለእሱ የነበራትን ጥልቅ ፍቅር ወዲያው ሲያስብ ደግሞ በጣም ይረበሻል፣ ፊቷን ላለማየት ይደበቃል:: በኋላም በውጭ አገር የትምህርት እድል አግኝቶ ሲሄድ

አይነግራትም:: ደመቀች የልጇን ርቆ መሄድ እንደሰማች በጣም ስታዝን በሻህ ከጎና በመሆን ያጽናናትና ራሷን እንዳትጎዳ ይመክራት ነበር፡ ይህ ከመሆኑ በፊት አስቀድማ ለልጇ የምታደርገውን በማየት ትክክል አለመሆኑን አስረድቷታል::

ደመቀችና በሻህ አንድ ቀን ገበያ ሲሄዱ ደመቀች አንድ ሱቅ ውስጥ የቀድሞ ባሏን ታምራትን በማየቷ ክፉኛ ትደነግጣለች፤ ለበሻህም ትነግረዋለች:: በሻህ ወደፊት በጋብቻቸው ላይ መሰናክል እንዳይፈጥር በመስጋት ደመቀችን አንድ ቦታ አስቀምጦ የጎጃም ኤልያስ ነዋሪ እንደሆነ በመዋሸት ከታምራት ጋር ይተዋወቃል:: መቼ ወደ አገሩ እንደሚመለስና ስለአሁኑ ሁኔታው ማረጋገጥ የሚፈልገውን ሁሉ ያረጋግጣል:: በሻህ ወደ ደመቀች እንደተመለሰ ብዙም ሳይቆይ ታምራት በመኪና ተገጭቶ ይሞታል ደመቀች የባሏ ሞት ለጊዜው ቢያሳዝናትም ወዲያው ግን ትጽናናለች፤ ትሸሸው የነበረና በሕልሟም የሚያስፈራራት በመሆኑ ይልቁን ወደፊት የነፃነት ኑሮ ለመኖር በመቻሏ ትደሰታለች::

አዝማሪው ውቤ፤ በሻህና ደመቀችን ለማቀራረብ ጥሯል:: በሻህም ውቤ በመከረው መሰረት ፊልም ቤትና አንዳንድ የመዝናኛ ቦታ ደመቀችን ይጋብዛታል:: ውቤ ከባለቤቱ ከውባየሁ ጋር በሻህና ደመቀች በመሆን አምቦ ለመዝናናት ሊሄዱ ይቀጣጠራሉ:: በቀጠሮው እለት ግን ውቤና ባለቤቱ ይቀራሉ፣ ደመቀችና በሻህ ጠብቀዋቸው ባለመምጣታቸው ቢያዝኑም ወዳሰቡት አምቦ ያቀናሉ:: አምቦ ከደረሱ በኋላ በአንድ ሆቴል ውስጥ ለየብቻ መኝታ ቤት ተከራይተው ይሰነብታሉ:: አምቦ ሳሉ ጥቂት ቢኳረፉም በኋላ ግን እርቅ ወርዶ፣ ዋናም አብረው ዋኝተው በፍቅር ወደ ቤታቸው ይመለሳሉ:: በመጨረሻም ሰርግ ደግሰው በቁርባን ይጋባሉ::

## 3.3.2 ሀዲስና በሻህ

<u>በየልምጉርት</u> መጽሐፍ መግቢያ ላይ ደራሲው ታሪኩ ስለተጻፈበት ዘመን እንዲህ የሚል ጽሁፍ አስፍረዋል፡-

> «ይህ የልም እዣት ከፋሽስቶች ወረራ ጥቂት አመታት ቀደም ብሎ ይጀምርና የኢትዮጵያ መንግሥት ወደ ስልጣኑ ከተመለሰ በኋላ እስከ አራት አምስት ዓመት ገደማ በነበረው ጊዜ ስለነበረው ሁኔታ ስማሳየት የሚሞክር ነው::» (ገጽ 6)

ከተጠቀሰው ዘመን ውስጥ በተለይ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት የነበረውን ሁኔታ ደራሲ ሀዲስ ተሳትፈውበታል:: በዚህ የልምገርት በተባለው መጽሀፋቸው ዘመኑ ከሚንጸባረቅባቸው አንዱ ዋናው ገጸባህሪ በሻህ ሲሆን ከወቅቱ ጋር በሚዛመድ ከደራሲው የሚያመሳስሏቸው ጥቂት ነገሮች አሉ::

ሀዲስ ከቤተክህነት ትምህርታቸው በኋላ በአዲስ አበባ ሚስዮን ትምህርት ቤት ዘመናዊ ትምህርት እንደተማሩት በሻህም በሚስዮን ትምህርት ቤት ተምሯል:: (ገጽ 180) ኢትዮጵያ ከጣሊያን ጋር በነበራት ጦርነት ወቅት የበሻህን የውስጥ አርበኝነት ጣሊያኖች ደርሰውበት ሊያጠፉት ሲያሳድዱት ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋር ተቀላቅሎ አርበኛ ሆኗል:: /ገጽ 210/ ሀዲስም ኢትዮጵያ መጀመሪያ ድል ከሆነች በኋላ ጦርነቱን በአርበኝነትን እንቀጥላለን በማለት ለወታደር መድኃኒት፣ ልብስና ሌሎች እቃዎችን በማቀበል በአርበኝነት አገልግለዋል:: ስለዚህ፣ በጣሊያን ጦርነት ወቅት ስለ ነበረው ሁኔታ በትዝታ መጽሐፋቸው ከገለፁት በተጨማሪ በየልምገርት መጽሐፍም በበሻህ አማካይነት አሳይተዋል::

በሻህ በመንግሥት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ ሲሰራ በውስጥ የሚከናወነው ያበሳጨዋል:: ሠራተኞቹ በአግባቡ አለመስራታቸውና ሹሞች ባለጉዳዮችን ሲያንገላቱ ሲመለከት የመንግሥት ስራን ይጠላል:: ስለዚህም ከአንድ መንግሥት መስሪያ ቤት ሌላው ቢሻል በማለት አጫጭር ጊዜ በመሰራት ስራውን በፈቃዱ እየለቀቀ ይዘዋወር ነበር:: / ገጽ 208/ ሀዲስም በመስሪያ ቤት ውስጥ እንዲስተካከል የሚፈልጉት ጉዳይ ሳይስተካከል ሲቀር አሰራሩን ካልተስማሙበት ስልጣናቸውን በገዛ ፈቃዳቸው በመልቀቅ ከመስሪያ ቤት መስሪያ ቤት ተዘዋውረዋል:: በሻህም ሆነ ሀዲስ በትምህርት ሚኒስቴር ሰርተዋል:: ሀዲስ ሚኒስትር ነበሩ፤ በሻህ ደግሞ በትምህርት እቅድና ፕሮግራም መምሪያ ውስጥ ሰርቷል::

በስልጣን ወዳጅ ዘመድን መርዳትን አስመልክቶ የሀዲስና የበሻህ አመለካከት አንድ አይነት ነው:: ሰው በስልጣኑ አገሩን በሀቅ ማገልገል አለበት የሚል አቋም አላቸው:: በሻህ «ከውቀትና ከችሎታ ይልቅ የዝምድና ሀረግ ስበው ወይም ልዩ ጥቅም ይዘው የሚቀርቡትን ለስራ ሲመርጡ የተመለከታቸውን ባለስልጣኖች መቅጣት .. !» / ገጽ 214 / በማለት ይዝታል:: ዛቻውን በተግባር ተረጎመው፣ ወሮበሎችን በማሰባሰብ እየተከታተለ ማጅራታቸውን በመምታትና በማዘረፍ ቀጣቸው::/ ገጽ 233/ የሀዲስ በስልጣን ዘመድን የመርዳት ተቃውሞ እንደበሻህ በቅጣት ባይሆንም ተቃውሞ ያሰሙ

ነበር፣ በነበራቸው ስልጣን 'ወዳጅን አልጠቀምበት' ሲሉ አሻፈረኝ ብለዋል:: የትምህርት ሚኒስትር በነበሩ ጊዜ ጃንሆይ የወዳጆቻቸውን ልጆች ለትምህርት ወደ ውጭ ሀገር እንዲልኩላቸው ቢጠይቋቸው ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገልጸው መልሰዋቸዋል::

ሀዲስ በሰዎች ላይ የሚደርሰውን በደል አይተውና ሰምተው ማለፍ አያስችላቸውም:: ለዚህም እንደዋነኛ ማስረጃ የሚጠቀሰው በ1953 በነበረው መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ያለጥፋታቸው የታሰሩት ጓደኞቻቸው ጥፋተኛ አለመሆናቸውን ለጃንሆይ ማሳወቃቸው ነው:: በሻህም ሰዎች ሲበደሉ ሲያይ በዝምታ አያልፍም አዝማሪ ጓደኛው ውቤን አለቃው ቢበድሉት በቅጣት ተበቀለለት:: /ገጽ 270 / ደመቀች ባልሰረቀችው እቃ 'ሌባ ነች' በማለት እመቤቷ ቢያሳስሯት በመዝረፍ ካሳት:: / ገጽ 313/ በሻህ አጥፊዎችን መቅጣት ክፉ ስራቸውን ደግመው እንዳይሰሩና ሌሎችም እነሱን በማየት ወደ ክፉ ስራ እንዳይገቡ መሆኑን ይገልጻል::/ ገጽ 215/

በሻህና ሀዲስን ሰው በመርዳት ደግነታቸውም ያመሳስላቸዋል:: ሀዲስ በየጊዜው ለተቸገሩ ይረዱ እንደ ነበር የጓደኛቸው የብላታ መሀሪ ምስክርነት በሕይወት ታሪካቸው ክፍል ተጠቅሷል:: የበሻህም ደግነት በጓደኛው ውቤ ተመስክሮለታል:: /ገጽ 298/ ሰዎችን ከመርዳት ጋር በተያያዘ ተምረው እንዲሻሻሉ በማገዝ ደራሲውና ገጸባህሪው አንድ አይነት አመለከካከት አላቸው:: በሻህ ደመቀች ትምህርት እንድትጀምር ሃሳብ ከመስጠት ጀምሮ ትምህርት ቤት እንድትገባ ረድቷታል:: / ገጽ 319 እና 325 / ሀዲስም እህቶቻቸውን፣ የእህቶቻቸውን ልጆችና ሌሎችንም ከገጠር በማምጣት አስተምረዋቸዋል::

በሻህ ከገፅ 366 - 383 በስፋት ስለትምህርት ያወሳል:: ይህንኑ <u>በወንጀለኛው ዳኛ</u> መጽሀፍ ገጽ 4 ደራሲ ሀዲስም ይናገሩታል:: ስለዚህም የበሻህ ንግግር የሀዲስ ንግግር ነው:: ለማለት ይቻላል:: ሁለቱም ልጅ ሳይኖራቸው ስለልጆች አስተዳደግ፣ የወላጆችና የልጆች ግንኙነትን ጠንቅቀው ያውቃሉ:: ሀዲስ <u>የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም</u> በተሰኘው መጽሐፋቸው ከገጽ 20 - 24 'የቤተሰብ ትምህርት' በሚል ርዕስ ስር በስፋት ከመዘርዘራቸው ባሻገር ወይዘሮ ስምረትም ይመሰክራሉ:- «አቶ ሀዲስ ልጅ የላቸውም ስለልጅ ግን በጣም ብዙ ያውቃሉ፣ ስለ እናትና ልጅ ያለውን ፍቅር ያውቃሉ:: እኔ ወልጄ አሳድጌያለሁ ከምለው በላይ እሳቸው ያውቃሉ::» /ጥር 26/1992 ቃ.ሙ/ በየልምፕት ገፅ 366 ደግሞ በሻህ ስለወላጆችና ልጆች ግንኙነት ይናገራል፣ ከገጽ 387 -

396 ደመቀች ከልጇ ተከስተ ጋር ምን አይነት ግንኙነት ሊኖራት እንደሚገባ ያስረዳታል::

ሀዲስ ዋና ያዘወትሩ እንደ ነበር የረዥም ጊዜ ጓደኛቸው ደጃዝማች ዘውዴ ተናግረዋል:: በሻህም አዘውትሮ ለመዋኘቱ ማስረጃ በገጽ 520 የተገለጸው የዋና ችሎታው ነው:: በጋብቻም ይመሳሰላሉ:: በሻህ ጋብቻውን የፈጸመው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሕግ በቅዱስ ቁርባን ነው:: / ገጽ 611/ የሀዲስ ጋብቻም እንደበሻህ ነበር::

በዚህ ምዕራፍ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ደራሲው ከፈጠሯቸው አራት ዋና ገጸባህርያት ጋር ያላቸውን ጥቂት ምስስሎሽ አይተናል:: ደራሲ ሀዲስ ከገጸ ባህርያቱ ጋር የጠበቀ ቁርኝት አላቸው ለማለት ባያስደፍርም ዝምድናቸውን በልቦለዶቻቸው ውስጥ ስንፈልግ ልናገኝ የምንችለው ግን በዚህ ክፍል ለመጥቀስ የተሞከሩትን ነው::

# ማጠቃለያ

በህይወት ታሪክ ላይ ጥናት ለማድረግ ለሚነሳ አጥኚ [illegible] የባለታሪኩ በህይወት መኖር ለጥናቱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አለው::

ይኸውም ከባለታሪኩ ቀዳማይ መረጃ ለማግኘት በመቻሉ ነው:: ምንም እንኳ ባለታሪኩን በቅርብ የሚያውቁትን ሰዎች በመጠየቅ የጽሑፍ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ ማጥናት ቢቻልም ከታሪኩ ባለቤት ውጭ መልስ የማይገኝላቸው ጥያቄዎች ሊያጋጥሙ ስለሚችሉ የባለ ታሪኩ በሕይወት መኖር አስፈላጊ ነው:: ደራሲ ሀዲስ በሕይወት ሳሉ የሕይወት ታሪካቸውን ለመጻፍ በመቻሌ ከዚህ ችግር አምልጫለሁ::

በዚህ ጥናት ምዕራፍ ሦስት ደራሲ ሀዲስ ዓለማየሁ በሦስቱ ረዥም ልቦለድ መጽሐፎቻቸው ከቀረጿቸው ዋና ገጸባህርያት ጋር ያላቸውን ጥቂት ተመሳስሎ ለማሳየት ተሞክሯል:: ለጥናቱ ከተመረጡት አራቱ ዋና ገጸባህርያት በሦስቱ የሚስተዋሉ ተመሳሳይ ባሕርያት አሉ:: ይኸውም ጉዱ ካሳ፣ ባሻህና ጥላሁን ለትምህርት ያላቸው አመለካከት፣ የዘመኑን ስርዐት መቃወማቸውና የሰውን በደል በዝምታ አለማለፋቸው ናቸው:: እነዚህ ባህርያት የደራሲው ናቸው::

ደራሲ ሀዲስ ከሦስቱ ረዥም ልቦለዶቻቸው ከፍቅር እስከ መቃብር ወንጀለኛው ዳኛ እና የልምገርት በተጨማሪ ኢ-ልቦለዶችንም አሳትመዋል:: ታሪክን በተመለከተ በጣሊያን ወረራ ወቅት በሀገራችን የነበረውን ሁኔታ ካዩት፣ ካጋጠማቸው ተነስተው ትዝታን ጽፈዋል:: የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሐፋቸው ደግሞ ትምህርት ከተማሪ ቤት ውጭም የት የት እንደሚገኝ በዝርዝር ገልጸዋል:: ኢትዮጵያ በምን መልኩ መተዳደር እንዳለባት ሲጠቁሙ ደግሞ ኢትዮጵያ ምን አይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል የተሰኘውን መጽሐፍ ደረሱ::

ተረት ተረት የመሠረት የሚል ርዕስ በያዘው መጽሐፋቸው በቃል የሚተላለፈውን የስነ ቃል ቅርስ ፈጠራ በማከል በጽሁፍ መዝግበዋል:: አውርሰውናል:: ሀዲስ ከላይ የተጠቀሱትን መጽሐፎችን አሳትመው አላረፉም:: ዛሬ እድሜና በሽታ ቢጫናቸውም ከማንበብና ከመጻፍ አልታቀቡም:: ሌላ መጽሐፍ ለማሳተም እቅድ አላቸው::

## ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

[1] Biography:- The narrative of a person's life; as we know it, a form proper to the modern centuries (post -17th.c) In classical and medieval times, such biographical wirting as existed tended to be summary and examplary lives of kings, heroes, and saints, with little concern for the personal subject. But the protestant and democratic spirit coferred greater value on the individual; and the subject of Bos wel's great biography (published in 1791), Dr Jahnson, maintained that the narrative of any person's life would be worth reading,... In the 20th c, biographical treatments are also to be found on audiotape, radio, film, and televison.

[2] --- all biography has this in common, that it is concerned with the truth of life and the truth of experience.

[3] Lytton Strachey once described biography as "the most delicate and human of all the branches of the art of writing."

[4] The biographer is called upon to take the base metals that are his disparate facts and turn them into the gold of the human personality, and no chemical process has yet been discoverd by which this change can be accomplished.

[5] In the writing of the novel, the artist is free to use all the resources of his imagination; in the writing of biography the material is predetermined: the imagination functions only as it plays over this material and shapes it.

# ዋቢ መጽሐፎች


ሀዲስ ዓለማየሁ :: 1948:: የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት::

--------------------::1958:: ፍቅር እስከ መቃብር፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሠላም ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ማተሚያ ቤት::

--------------------:: 1974:: ወንጀለኛው ዳኛ፣ አዲስ አበባ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት::

--------------------:: 1980:: የልምገርት፣ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት::

--------------------:: 1985:: ትዝታ፣ አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት

ሰለሞን ክፍሌ:: 1976:: «ሂዩመር በሀዲስ ዓለማየሁ ልቦለዶች ውስጥ»፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ::

በላይ ሰይድ::1987::«ደራሲ ገበየሁ አየለና የሥነ ጽሑፍ ስራዎቹ» አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ::

ብርሃነ መስቀል ደጀኔ:: 1982:: «የሰዓሊ ገብረ ክርስቶስ ደስታ የሕይወት ታሪክና አንዳንድ ግጥሞቹ»፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ::

ተሾመ ይመር::1972:: «የፍቅር እስከ መቃብሩ ጉዱ ካሳ»፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ::

ተድላ ወልደ ሥላሴ::1975:: «የበእምነት ገብረ አምላክ የሕይወት ታሪክና ልጅነት ተመልሶ አይመጣም፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ::

ታደለ ገድሌ:: መስከረም 8/1992::«አገራቸውን በሁለንተናዊ መልኩ ያገለገሉ ታላቅ ሰው»፣ አዲስ ዘመን ፣59ኛ ዓመት ቁጥር 7

--------------------:: መስከረም 15/1992:: « አርአያነታቸው የሚመረጥ የተከበሩ ዜጋ ሀዲስ አለማየሁ»፣ አዲስ ዘመን፣ 59ኛ ዓመት ቁጥር 19

--------------------:: መስከረም 22/1992:: «አርአያነታቸው የሚመረጥ የተከበሩ ዜጋ ሀዲስ ዓለማየሁ »:: አዲስ ዘመን :: 59 ዓመት ቁጥር 19

አለልኝ መንግሥቱ:: 1971:: «በፍቅር እስከመቃብር መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ የአነጋገር ዘዬዎች»፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል፣ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ::

አለስም:: የካቲት 1985:: «ለሀዲስ ዓለማየሁ ከቆሎ ተማሪነት እስከ አርበኝነት» ፍካሬ፣ 1ኛ ዓመት ፣ ቅፅ 1፣ ቁ 1

አለስም:: ጥቅምት 1992 ::« ሀዲስ እንደ አዲስ» ፈርጥ ፣ ቅፅ 4 ፣ ቁ2

አለስም:: 1957 - 1962 ዓ.ም:: «የአማርኛ ስነጽሑፍ ሽልማት»፣ የቀዳማዊ ኃይለስላሴ ሽልማት ድርጅት፣ 10ኛ ዓመት

አስፋው ሺበሺ::1964:: «በአቶ ሀዲስ ዓለማየሁ መጻሕፍት ውስጥ ያሉ ምሣሌያዊ አነጋገሮች»፣ በቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩኒቨርስቲለኢዱኬሽን ፋኩሊቲ፣ ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ::

አበበ ሐረገወይን::1970:: «ፊታውራሪ መሸሻ»፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ክፍልለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ::

አደፍርስ አድማሱ:: 1980:: «የኢትዮጵያ ልቦለድ ዐበይት ደራሲያን አጭር ዜና ሕይወት»፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ::

አዳነ ታደገ::1979::«ሻምበል ክፍሌ አቦቸርና የግጥም ስራዎቹ»፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ::

ዓለማየሁ ግርማ:: 1988::« አስፋው ዳምጤና የስነጽሑፍ አበርክቶዎቹ»፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍልለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ::

ዓለማየሁ ዐጋዬ:: 1976 ::«የግጭት ይዞት በፍቅር እስከመቃብር»፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ::

ዓምደማርያም ሀብተወልድ:: 1974:: «ሀዲስ ዓለማየሁ በወንጀለኛው ዳኛ ውስጥ የተጠቀሙባቸው ዘይቤአዊ አነጋገሮች»፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ስነጽሑፍ ክፍልለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ::

ደምስ አላምረው:: 1988:: «ደራሲ አውግቸው ተረፈና የስነጽሑፍ ስራዎቹ»፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሑፍ ክፍልለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ::

ጥጋቤ አስረስ:: 1962::«የነጋድራስ ገብረሕይወት ባይከዳኝ አጭር የሕይወት ታሪክ»፣ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ::

ግዛቸው ሙሉጌታ:: 1974 ::«ጥላሁን ፈይሳ የወንጀለኛው ዳኛ ዋና ገጸባህሪ»፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ለባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ::

Calder, Robert. 1989. Willie: The life of W. Semerset Maugham, Bungay; Suffolk: Richard Clay LTD

Edel , Leon. 1959. Literary Biography, New York: Doubleday .

Free man , william, 1954 , Biographies: Scientists and Inventors, London: Sir isac Pitruan & Sons , LTD.

"Literat ure", 1990, The Combridge Encyclopedia new, York: Cambridge Univeristy Press.

--------------------.1993. Vol II, A New Encyclopedai Britanica, Chicogo: Encyclopedia Britanica Inc.

Molvear, Dulf. K. 1997. Black Lions : The creative Lives of Modern Ethiopia's Literary Giants and pioneers, Asmara: The Red Sea Press, Inc

Shaw Harry. 1997. Dictionary of Literary Terms, USA: Mc Graw- Hill, Inc.

## አባሪ ፤ ሀ

**ለመጀመሪያ ጊዜ ለሀዲስ ዓለማየሁ ጥቅምት 10/1992 ዓ.ም በመኖሪያ ቤታቸው የተካሄደ ቃለ ምልልስ**

- የተወለዱበት ቦታ የት ነው? ዘመኑስ?
- ትምህርት ቤት የገቡት መቼ ነው?
- የቤተክህነት ትምህርት ተምረዋል? ከተማሩ እስከ ምን ድረስ?
- ዘመናዊ ትምህርት የጀመሩበትን ዘመን ቢነግሩኝ?
- አንደኛ ደረጃ ትምህርትዎን የተማሩት መቼና የት ነው?
- ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትዎንስ የተማሩት የት ነው? ዘመኑስ?
- ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር የተከታተሉት ትምህርት አለ?
- ከአማርኛ ውጭ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ቋንቋ ምን ምን ያውቃሉ?
- የትዳር ህይወትዎ ምን ይመስል ነበር? ስንት ዓመት በትዳር ቆይተዋል?
- የስነጽሑፍ ዝንባሌዎ መቼ እንደተከሰተ ያውቁታል?
- ስነጽሑፍ ሲጀምሩ የጓደኛና የዘመድ እገዛ አግኝተው ነበር?
- ጓደኞችዎ በእርስዎ ስነጽሑፍ ስራዎች ላይ ያደረጉት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽእኖ ነበር?
- በትምህርት ቤት እያሉ የስነጽሑፍ ውድድር ይካሄድ ነበር?
- በስራ ዓለም በነበሩ ጊዜ አገር ውስጥ የት የት መስሪያ ቤት አገልግለዋል?
- በውጭ አገርስ የት ሰርተዋል? በምን ሙያ?
- ከተሰማሩባቸው ስራዎች ለስነጽሑፍ መልካም ገጠመኝ አግኝቻለሁ ይላሉ?

## አባሪ ፡ ለ

<u>ለሁለተኛ ጊዜ ለሀዲስ ዓለማየሁ ሕዳር 1 ቀን 1992 ዓ.ም በመኖሪያ ቤታቸው የተደረገ ቃለ ምልልስ</u>

- ዳዊት ደግመው የጨረሱት በስንት ዓመትዎ ነው?
- ቦታው የት ነበር?
- ጾመድጓን ጨርሰው ክህነት የተቀበሉት መቼ ነበር ዘመኑ?
- ቅኔ ቤትስ የት ነው የገቡት?
- የቅኔ መምህርዎ ማን ነበሩ?
- እርስዎ የቅኔ መምህር ለመሆን ይመኙ ነበር?
- ከጎጃም ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ አበባ ሲመጡ ግር ያለዎት ነገር ነበር?
- ከጓደኞችም ጋር አዲስ አበባ ከመጣችሁ በኋላ የት ቆያችሁ?
- ዘመናዊ ትምህርት አልማርም ያሉት ለምንድን ነው?
- በመንግሥት መስሪያ ቤት ሲያገለግሉ ከአለቆችዎም ሆነ ከበታቾችዎ ጋር የነበርዎ ግንኙነት ምን ይመስል ነበር?
- በመሥሪያ ቤት ውስጥ የሚፈጸሙ አንዳንድ ድርጊቶች ያባሳጭዎ ነበር?
- የአስተማሪነት ሥራ ሲጀምሩ ወደውት /መርጠውት/ ነበር?
- ከአንዱ መሥሪያ ቤት ወደ ሌላው መሥሪያ ቤት የሚዘዋወሩት በምን ምክንያት ነበረ?
- ሥራዎን በፈቃድዎ የለቀቁበት ጊዜ አለ?
- ጎጃም እያሉ ያፈቀሯት ሴት ነበረች?
- ከባለቤትዎ ጋር እንዴት እንደተገናኙ ቢነግሩኝ?
- ኢሊባቡርን ያውቁታል? ካወቁት በምን ምክንያት ሄደው?
- በጎጃም አካባቢ እንደ ጉዱ ካሳ አይነት ሰው ነበር ይባላል። ይህ እውነት ነው?
- ጉዱ ካሳን በገጸባህሪነት ሲቀርጹት እንደሱ አይነት ስርዓቱን የሚቃወም ሰው በወቅቱ ይኖራል ብለው ነበር?
- ፍቅር እስከ መቃብርን ለመጻፍ ያነሳሳዎ ምክንያት ምን ነበር?
- የውጭ አገር ደራሲያን ስራዎች አንብበዋል? የማንን ያደንቃሉ?
- ከአገር ውስጥ ደራሲያንየማንን ያደንቃሉ?
- ያልታተሙ ጽፈው ያስቀመጧቸው አጫጭር ልቦለዶች አሉዎት?

- ግጥምስ ይጽፋሉ?
- በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው የስነጽሑፍ እንቅስቃሴ ምን አስተያየት አለዎት?
- ፍቅር እስከመቃብር ላይ ያለችው ገጸባህሪ ሰብለ በጣም የሚያስደንቅ ነገር ትሰራለች:: መንገድ ላይ ነብር ሲመጣባት በተዓምር ታመልጣለች:: ይህ በውጭው ሮማንቲክ አጻጻፍ የሚባለው ነው:: እርስዎስ! ይህን ተከትለው ነው የጻፉት? ተዓማኒነቱንስ አስበውበታል?
- አጻጻፉ የሰብለ ታሪክ የገድል አይነት አጻጻፍ ነው ይባላል:: ስለዚህስ ምን ይላሉ?
- የእረፍት ጊዜዎን በምን ማሳለፍ ይወዳሉ?
- ከድርሰቶችዎ ሁሉ የማኅበረሰቡን ገጽታ በማሳየት ረገድ ከፍ ያለ ዋጋ የሚሰጡት ለየትኛው ነው?
- አንባቢያን ፍቅር እስከ መቃብርን ያደንቃሉ እርስዎ የትኛውን ያደንቃሉ?
- ለንባብ የሚመርጧቸው መጽሐፍ ምን ላይ ያታኮሩ ናቸው?
- ባለቤትዎ በምን ምክንያት ነበር የሞቱት?
- ባለቤትዎ ከሞቱ በኋላ ሌላ ሚስት አላገቡም? ለምን?

አባሪ ፡ ሐ

## ለሦስተኛ ጊዜ ለሀዲስ ታህሣስ 7/1992ዓ.ም በመኖሪያ ቤታቸው የተካሄደ ቃለ ምልልስ

- ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ አበባ የመጡበት ዓመተ ምህረት መቼ ነበር?
- እናትና አባትዎ በምን ነበር የሚተዳደሩት?
- እናትና አባትዎ የተለያዩት በምን ምክንያት ነበር?
- እናትና አባትዎ ከተለያዩ በኋላ እርስዎ ከማን ጋር ነበር የሚኖሩት?
- ጎጃም እያሉ ቤተክርስትያን ያገለግሉ ነበር?
- ከአባትዎ ጋር ኢሊባቡር አብረው ኖረዋል?
- አባትዎ እስከመጨረሻው ኢሉባቡር ነበር የኖሩት?
- የእህቶችዎ ወይም የቅርብ ዘመዶችዎ ጋብቻ እንዴት ነበር? በስንት ዓመታቸው አገቡ?
- እርስዎ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት እስከ ስንተኛ ክፍል ተምረዋል?
- ጣሊያን አገር መቼ እና ለምን ጉዳይ ነበር የሄዱት?
- ትዳር በስንት ዓመትዎ መሰረቱ?
- ባለቤትዎ መቼ ነው የሞቱት?
- ትምህርት ሚኒስቴር እያሉ እንዲሻሻል ለሚፈልጉት ጉዳይ ሃሳብ ያቀርቡ ነበር?
- ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በሠሩ ጊዜስ የመሻሻል /የለውጥ/ ሃሳብ አንስተዋል?
- ፓርላማ ሲሠሩስ ምን ምን ጉዳዮችን አስፈጽመዋል?
- ጎጃም ሸንጎ ተመርጠው ይሠሩ ነበር ያኔስ ከፈጸሙት ወይ ካስፈጸሙት ጉዳይ የሚያስታውሱትን ቢነግሩኝ? ለምን ያህል ጊዜስ አገለገሉ?
- አምባሳደር የነበሩ ጊዜ እንግሊዝ ሀገርና ኒውዮርክ ለምን ያህል ጊዜ ቆይተዋል?
- በኢየሩሳሌምስ ስንት ዓመት አገልግለዋል?
- ከኢትዮጵያ ውጭ የሰሩበት ሌላ አገር አለ?
- ሱዳን ለምን ጉዳይ ነበር የሄዱት? ስንት ዓመት ቆዩ?
- ዲማ፣ እንዶዳምና ኤልያስ ጎጃም የት አካባቢ ነው የሚገኙት?
- መምህር ገብረስላሴ አያትዎም መምህርዎም ነበሩ:: በመምህርነታቸው የነበራቸው ባህርይ እንዴት ነበር? ይቆጣሉ፣ ይማታሉ፣ የሚያስታውሱት የተለየ ባህርይ ካለ ቢነግሩኝ?

- ዳንግላ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ የሥራ ድርሻዎ ምን ነበር?
- አሜሪካን አገር በተማሩት የህግ ትምህርት ምን ደረጃ ላይ ደርሰዋል?
- ከጃንሆይ ጋር የነበርዎ ግንኙነት እንዴት ነበር?
- በቅርቡ ያውቋቸው የነበሩ ቀኛዝማች፣ ደጃዝማች ባላምባራስ... አሉ? ካሉ በሹመት ላይ ሆነው ለሕዝቡ የነበራቸው አመለካከት እንዴት ነበር?
- ኢሉባቡር መሬት ሲያለሙ ነበር:: ለሕዝቡ ስልጣኔን ላስተምረው በማለት ጥረት አድርገዋል:: ከሕዝቡ ጋር የነበርዎ ቀረቤታስ ምን ይመስል ነበር?
- ኢሉባቡር መሬት ከማልማት ሌላ ምን ይሰሩ ነበር?
- በሕግ ሙያ ሰርተዋል?

## አባሪ ፤ ሀ

**ለመጀመሪያ ጊዜ ለሀዲስ ዓለማየሁ ጥቅምት 10/1992 ዓ.ም በመኖሪያ ቤታቸው የተካሄደ ቃለ ምልልስ**

- የተወለዱበት ቦታ የት ነው? ዘመኑስ?
- ትምህርት ቤት የገቡት መቼ ነው?
- የቤተክህነት ትምህርት ተምረዋል? ከተማሩ እስከ ምን ድረስ?
- ዘመናዊ ትምህርት የጀመሩበትን ዘመን ቢነግሩኝ?
- አንደኛ ደረጃ ትምህርትዎን የተማሩት መቼና የት ነው?
- ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትዎንስ የተማሩት የት ነው? ዘመኑስ?
- ከሁለተኛ ደረጃ በኋላ በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር የተከታተሉት ትምህርት አለ?
- ከአማርኛ ውጭ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ አገር ቋንቋ ምን ምን ያውቃሉ?
- የትዳር ህይወትዎ ምን ይመስል ነበር? ስንት ዓመት በትዳር ቆይተዋል?
- የስነጽሑፍ ዝንባሌዎ መቼ እንደተከሰተ ያውቁታል?
- ስነጽሑፍ ሲጀምሩ የጓደኛና የዘመድ እገዛ አግኝተው ነበር?
- ጓደኞችዎ በእርስዎ ስነጽሑፍ ስራዎች ላይ ያደረጉት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽእኖ ነበር?
- በትምህርት ቤት እያሉ የስነጽሑፍ ውድድር ይካሄድ ነበር?
- በስራ ዓለም በነበሩ ጊዜ አገር ውስጥ የት የት መስሪያ ቤት አገልግለዋል?
- በውጭ አገርስ የት ሰርተዋል? በምን ሙያ?
- ከተሰማሩባቸው ስራዎች ለስነጽሑፍ መልካም ገጠመኝ አግኝቻለሁ ይላሉ?

## አባሪ ፡ ለ

ለሁለተኛ ጊዜ ለሀዲስ ዓለማየሁ ሕዳር 1 ቀን 1992 ዓ.ም በመኖሪያ ቤታቸው የተደረገ ቃለ ምልልስ

- ዳዊት ደግመው የጨረሱት በስንት ዓመትዎ ነው?
- ቦታው የት ነበር?
- ጾመድጓን ጨርሰው ክህነት የተቀበሉት መቼ ነበር ዘመኑ?
- ቅኔ ቤትስ የት ነው የገቡት?
- የቅኔ መምህርዎ ማን ነበሩ?
- እርስዎ የቅኔ መምህር ለመሆን ይመኙ ነበር?
- ከጎጃም ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ አበባ ሲመጡ ግር ያለዎት ነገር ነበር?
- ከጓደኞችም ጋር አዲስ አበባ ከመጣችሁ በኋላ የት ቆያችሁ?
- ዘመናዊ ትምህርት አልማርም ያሉት ለምንድን ነው?
- በመንግሥት መስሪያ ቤት ሲያገለግሉ ከአለቆችዎም ሆነ ከበታቾችዎ ጋር የነበርዎ ግንኙነት ምን ይመስል ነበር?
- በመሥሪያ ቤት ውስጥ የሚፈጸሙ አንዳንድ ድርጊቶች ያባሳጭዎ ነበር?
- የአስተማሪነት ሥራ ሲጀምሩ ወደውት /መርጠውት/ ነበር?
- ከአንዱ መሥሪያ ቤት ወደ ሌላው መሥሪያ ቤት የሚዘዋወሩት በምን ምክንያት ነበረ?
- ሥራዎን በፈቃድዎ የለቀቁበት ጊዜ አለ?
- ጎጃም እያሉ ያፈቀሯት ሴት ነበረች?
- ከባለቤትዎ ጋር እንዴት እንደተገናኙ ቢነግሩኝ?
- ኢሊባቡርን ያውቁታል? ካወቁት በምን ምክንያት ሄደው?
- በጎጃም አካባቢ እንደ ጉዱ ካሳ አይነት ሰው ነበር ይባላል፡፡ ይህ እውነት ነው?
- ጉዱ ካሳን በገጸባህሪነት ሲቀርጹት እንደሱ አይነት ስርዓቱን የሚቃወም ሰው በወቅቱ ይኖራል ብለው ነበር?
- ፍቅር እስከ መቃብርን ለመጻፍ ያነሳሳዎ ምክንያት ምን ነበር?
- የውጭ አገር ደራሲያን ስራዎች አንብበዋል? የማንን ያደንቃሉ?
- ከአገር ውስጥ ደራሲያንየማንን ያደንቃሉ?
- ያልታተሙ ጽፈው ያስቀመጧቸው አጫጭር ልቦለዶች አሉዎት?

- ግጥምስ ይጽፋሉ?
- በኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው የስነጽሑፍ እንቅስቃሴ ምን አስተያየት አለዎት?
- ፍቅር እስከመቃብር ላይ ያለችው ገጸባህሪ ሰብለ በጣም የሚያስደንቅ ነገር ትሰራለች። መንገድ ላይ ነብር ሲመጣባት በተዓምር ታመልጣለች፡፡ ይህ በውጭው ተዓማኒነቱንስ አስበውበታል? ሮማንቲክ አጻጻፍ የሚባለው ነው፡፡ እርስዎስ! ይህን ተከትለው ነው የጻፉት?
- አጻጻፉ የሰብለ ታሪክ የገድል አይነት አጻጻፍ ነው ይባላል፡፡ ስለዚህስ ምን ይላሉ?
- የእረፍት ጊዜዎን በምን ማሳለፍ ይወዳሉ?
- ከድርሰቶችዎ ሁሉ የማኅበረሰቡን ገጽታ በማሳየት ረገድ ከፍ ያለ ዋጋ የሚሰጡት ለየትኛው ነው?
- አንባቢያን ፍቅር እስከ መቃብርን ያደንቃሉ እርስዎ የትኛውን ያደንቃሉ?
- ለንባብ የሚመርጧቸው መጽሐፍ ምን ላይ ያታኩሩ ናቸው?
- ባለቤትዎ በምን ምክንያት ነበር የሞቱት?
- ባለቤትዎ ከሞቱ በኋላ ሌላ ሚስት አላገቡም? ለምን?

## አባሪ ፡ ሐ

**ለሦስተኛ ጊዜ ለህዳስ ታህሣስ 7/1992ዓ.ም በመኖሪያ ቤታቸው የተካሄደ ቃለ ምልልስ**

- ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ አበባ የመጡበት ዓመተ ምህረት መቼ ነበር?
- እናትና አባትዎ በምን ነበር የሚተዳደሩት?
- እናትና አባትዎ የተለያዩት በምን ምክንያት ነበር?
- እናትና አባትዎ ከተለያዩ በኋላ እርስዎ ከማን ጋር ነበር የሚኖሩት?
- ጎጃም እያሉ ቤተክርስትያን ያገለግሉ ነበር?
- ከአባትዎ ጋር ኢሊባቡር አብረው ኖረዋል?
- አባትዎ እስከመጨረሻው ኢሉባቡር ነበር የኖሩት?
- የእህቶችዎ ወይም የቅርብ ዘመዶችዎ ጋብቻ እንዴት ነበር? በስንት ዓመታቸው አገቡ?
- እርስዎ ተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት እስከ ስንተኛ ክፍል ተምረዋል?
- ጣሊያን አገር መቼ እና ለምን ጉዳይ ነበር የሄዱት?
- ትዳር በስንት ዓመትዎ መሰረቱ?
- ባለቤትዎ መቼ ነው የሞቱት?
- ትምህርት ሚኒስቴር እያሉ እንዲሻሻል ለሚፈልጉት ጉዳይ ሃሳብ ያቀርቡ ነበር?
- ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር በሥሩ ጊዜስ የመሻሻል /የለውጥ/ ሃሳብ አንስተዋል?
- ፓርላማ ሲሠሩስ ምን ምን ጉዳዮችን አስፈጽመዋል?
- ጎጃም ሸንጎ ተመርጠው ይሠሩ ነበር ያኔስ ከፈጸሙት ወይ ካስፈጸሙት ጉዳይ የሚያስታውሱትን ቢነግሩኝ? ለምን ያህል ጊዜስ አገለገሉ?
- አምባሳደር የነበሩ ጊዜ እንግሊዝ ሀገርና ኒውዮርክ ለምን ያህል ጊዜ ቆይተዋል?
- በኢየሩሳሌምስ ስንት ዓመት አገልግለዋል?
- ከኢትዮጵያ ውጭ የሰሩበት ሌላ አገር አለ?
- ሱዳን ለምን ጉዳይ ነበር የሄዱት? ስንት ዓመት ቆዩ?
- ዲማ፣ እንዶዳምና ኤልያስ ጎጃም የት አካባቢ ነው የሚገኙት?
- መምህር ገብረስላሴ አያትዎም መምህርዎም ነበሩ:: በመምህርነታቸው የነበራቸው ባህርይ እንዴት ነበር? ይቆጣሉ፣ ይማታሉ፣ የሚያስታውሱት የተለየ ባህርይ ካለ ቢነግሩኝ?

- ዳንግላ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተማሩበት ትምህርት ቤት ውስጥ የሥራ ድርሻዎ ምን ነበር?
- አሜሪካን አገር በተማሩት የህግ ትምህርት ምን ደረጃ ላይ ደርሰዋል?
- ከጃንሆይ ጋር የነበርዎ ግንኙነት እንዴት ነበር?
- በቅርቡ ያውቋቸው የነበሩ ቀኛዝማች፣ ደጃዝማች ባላምባራስ... አሉ? ካሉ በሹመት ላይ ሆነው ለሕዝቡ የነበራቸው አመለካከት እንዴት ነበር?
- ኢሉባቡር መሬት ሲያለሙ ነበር:: ለሕዝቡ ስልጣኔን ላስተምረው በማለት ጥረት አድርገዋል:: ከሕዝቡ ጋር የነበርዎ ቀረቤታስ ምን ይመስል ነበር?
- ኢሉባቡር መሬት ከማልማት ሌላ ምን ይሰሩ ነበር?
- በሕግ ሙያ ሰርተዋል?

የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር
INSTITUTE OF ETHIOPIA STUDIES
የውጭ አገር ቋንቋዎች
FOREIGN LANGUAGES

## አባሪ ፡ መ

**ለሀዲስ ጓደኞች የቀረቡ ቃለ መጠይቆች**

1/ ለደጃዝማች ዘውዴ ገብረስላሴ፣ ኅዳር 22 /1992 ዓ.ም በሀዲስ ዓለማየሁ መኖሪያ ቤት

2/ ለብላታ መህሪ ካሳ፣ ታህሳስ 2 እና ታህሳስ 9/1992 ዓ.ምለመኖሪያ ቤታቸው::

- ከክቡር ዶ/ር ሀዲስ ዓለማየሁ ጋር ያለዎት ቅርበት ወይም እውቂያ በምን ደረጃ እንደ ነበር ቢገልጹልኝ?
- ከሀዲስ ጋር የምትተዋወቁት ከመቼ ጀምሮ ነው?
- ሀዲስ በባህርያቸው የሚወዱትና የሚጠሉት ነገር ምን ነበር?
- በቅርቡ ተገናኝታችሁ ነበር? መቼና የት?
- ስለጥንት ጸባያቸውና ስለ አሁኑ እያወዳደሩ ቢገልጹልኝ?
- ሀዲስን የሚያደንቁባቸው ባህርያት ወይም ድርጊት ካሉ ቢነግሩኝ?
- የሚነቅፉባቸው ባህርያት ወይም ድርጊትስ ምን ምን ናቸው?
- ከሥራ ጓደኞቻቸውና ከጎረቤቶቻቸው ጋር የነበራቸው ግንኙነት ምን ይመስል ነበር?
- የስነጽሑፍ ስራዎቻቸውን አንብበዋል? ካነበቡ የትኞቹን ያደንቃሉ? ለምን?
- ሀዲስ ለተቸገረ ሰው በመርዳት ያላቸውን አመለካከት ማስረጃ አስደግፈው ቢገልጹልኝ?
- በጭውውታችሁ ወቅት በአብዛኛው ማንሳት የሚፈልጉት ጉዳይ ምንን በተመለከተ ነበር?
- በሥራ አለም ስለገጠማቸው መጥፎም ሆነ መልካም ትዝታዎች አጫውተዎት ያውቃሉ? ካሉ ጥቂቱን ቢገልጹልኝ?
- የሀዲስ የትዳር ሕይወት እንዴት ነበር? ከባለቤታቸው ጋር የሚጋጩበት ጉዳይ ነበር?
- ስለ ደራሲው ሌሎች ተጨማሪ አስተያየቶች ካለዎት ቢገልጹልኝ?

## አባሪ ፡ ሠ

## ከሀዲስ ዘመድ ከወይዘሮ ስምረት ቦጋለ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ

ጥር 26/1992 በመኖሪያ፡ቤታቸው

- ከክቡር ዶ/ር ሀዲስ ዓለማየሁ ጋር ዝምድናችሁ በምንድነው?
- ከመቼ ጀምሮ ነው ይበልጥ የተቀራረባችሁት?
- ብዙ ጊዜ አብራችሁ ትቆያላችሁ?
- ስትገናኙ በአብዛኛው የምታወሩት በምን ጉዳይ ላይ ነው?
- ከእሳቸው ጋር ካሳለፉት የማይረሱት ገጠመኝ ካለ ቢነግሩኝ?
- ክቡር ዶ/ር ሀዲስ ቀድሞ ብዙ ጊዜያቸውን ምን በመስራት ነበር የሚሳልፉት? አሁንስ?
- የቀድሞ ባህርያቸው እንዴት ነበር?አሁንስ ከቀድሞ የተለወጠ ባህርይ አላቸው?
- እርስዎ በሚያውቁት ክቡር ዶ/ር ሀዲስ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚወዱትና የሚያደንቁት ነገር ምንድን ነው? የሚጠሉትስ?
- እርስዎስ ከባህርያቸው የሚወዱትና የሚጠሉት ምንድነው?
- ከዘመዶቻቸው ጋር ያላቸው ቀረቤታ እንዴት ነው?
- ስለመጽሐፎቻቸው ወይም ስለ ስነጽሑፍ ትነጋገራላችሁ?
- እርስዎ መጽሑፎቻቸውን አንብበዋል? ካነበቡ የትኛውን ያደንቃሉ? ለምን?
- በደራሲነታቸው በተለይም እንዲህ ታዋቂ በመሆናቸው ያለዎት አስተያየት ምንድነው?
- ክቡር ዶ/ር ሀዲስ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ውጭ ሀገር የሄዱት መቼ ነበር?
- ስለሰርጋቸው ቀን የሚያስታውሱት አለ?
- ስለባለቤታቸው ባህርያት ቢነግሩኝ?
- ባለቤታቸው ከሞቱ ወዲህ ያመጡት የባህርይ ለውጥ አለ?
- በአጠቃላይ ክብር ዶ/ር ሀዲስ ምን አይነት ሰው ናቸው ይላሉ?

Elizabeth R ኢገሬሬ

# Elizabeth the Second

by the Grace of God of the United Kingdom of Great Britain and Northern Ireland and of Her other Realms and Territories Queen Head of the Commonwealth Defender of the Faith and Sovereign of the Royal Victorian Order to His Excellency Ato Haddis Alemayehu Ethiopian Ambassador at Our Court at Saint James's

Greeting:

**Whereas** We have thought fit to nominate and appoint you to be an Honorary Knight Grand Cross of Our Royal Victorian Order.

**We do** by these Presents grant unto you the Dignity of an Honorary Knight Grand Cross of Our said Royal Order and We do hereby authorise you to have hold and enjoy the said Dignity as an Honorary Knight Grand Cross of Our said Royal Order together with all and singular the privileges thereunto belonging or appertaining.

**Given** at Our Court at Saint James's under Our Sign Manual and the Seal of Our said Royal Order this First day of February 1965 in the Thirteenth year of Our Reign.

By The Sovereign's Command

Elizabeth R

Grand Master.

Cobbold

Chancellor.

Grant of the Dignity of an Honorary Knight Grand Cross of the Royal Victorian Order to His Excellency Ato Haddis Alemayehou.

ከእንግሊዝ፡ንግሥት፡ ግርማዊት፡ ለአምባሳደር፡ ከሀዲስ፡ ዓለማየሁ፡ የተሰጠ፡ የክብር፡ ሽልማት
የምስክር፡ ወረቀት

ፈገሬሸ



ግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ በአማርኛ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ለክቡር ፡ አቶ ፡ ሐዲስ ፡ ዓለማየሁ ፡ ሽልማቱን ፡ ሲሰጡ ። አቅራቢ ፡ አቶ ፡ የወንድ ፡ ወሰን ፡ መንገሻ ።
H.I.M. awarding the Amharic literature Prize to H.E. Ato Haddis Alemayehou. Presented by Ato Yewond Wosen Mengasha.

የ፲፱፻፷፱ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የአማርኛ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ሽልማት ።

ክቡር ፡ አቶ ፡ ሐዲስ ፡ ዓለማየሁ ፡«የትምህርትና ፡ የትምህርት ፡ ቤት ፡ ትርጉም ፡» «ተረት ፡ ተረት ፡ የመሠረት ፡» የተባሉ ፡ በ፲፱፻፵፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የታተሙ ፡ መጻሕፍት ፡ ደራሲ ፡ ናቸው ።

ከዚህም ፡ በቀር ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓ ፡ ም ፡«ፍቅር ፡ እስከ ፡ መቃብር ፡» የተባለውን ፡ ታላቅ ፡ ልብ ፡ ወለድ ፡ መጽሐፋቸውን ፡ ላንባቢዎች ፡ ሲያቀርቡ ፡ ደራሲው ፡ የኢትዮጵያን ፡ ባህል ፡ ምን ፡ ያህል ፡ እንደሚያውቁትና ፡ በሕዝባችንም ፡ ላይ ፡ የሚታየውን ፡ አንዳንድ ፡ ባህላዊ ፡ መልክ ፡ ምንኛ ፡ እንደሚወዱት ፡ ማስገንዘብ ፡ ችለዋል ።

ያገራችንን ፡ ሕዝብ ፡ ፈሊጥና ፡ የንግግር ፡ ስልት ፡ ከየክፍሉ ፡ አንሥተው ፡ የጥንቱንና ፡ የዛሬውን ፡ እያቀናበሩ ፡ በልብ ፡ ወለድ ፡ መልክ ፡ በማቅረብ ፡ ለአማርኛ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የአቀራረብ ፡ ብልጽግናን ፡ አበርክተዋል ።

ደራሲው ፡ ልብ ፡ ወለዳቸውን ፡ ሲጽፉ ፡ ስለተከተሉት ፡ የፊደል ፡ አገባብ ፡ የሰዋስው ፡ ሊቃውንት ፡ አስተያየታቸውን ፡ ይሰጡበት ፡ ይሆናል ።

የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ሽልማት ፡ ድርጅት ፡ ክቡር ፡ አቶ ፡ ሐዲስ ፡ ዓለማየሁ ፡ ባሳዩት ፡ የደራሲነት ፡ ቅልጥፍና ፡ አዲስ ፡ የድርሰት ፡ መንገድ ፡ መክፈታቸውን ፡ ስለተገነዘበው ፡ በ፲፱፻፷፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የአማርኛ ፡ ሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ሽልማት ፡ የወርቅ ፡ ኒሻንና ፡ የምስክር ፡ ወረቀት ፡ ከ፲ሺህ ፡ የኢት ፡ ብር ፡ ጋር ፡ እንዲሰጣቸው ፡ ወስኗል ።

Amharic Literature Award, 2nd November 1969

## H. E. ATO HADDIS ALEMAYEHOU.

H.E. Ato Haddis Alemayehou will receive the 1969 Haile Selassie Award for Amharic Literature.

Ato Haddis is the author of "the Significance of Education and School" and "Fundamental Fables" both inspired from didactic art and published in 1955.

Imbued as he is with deep understanding of the Ethiopian way of life and a great sympathy for some cultural and social figures of our people, the author has created amongst his writings, an original work, "FIQER ESKE MEQABER" which occupies an eminent place in his literary achievements. (Published in 1965).

The author's ability to seize and use the expressive vocabulary and language patterns of various social spheres both from the past and from the present, bringing into play the values of that past and its current process of change is an outstanding contribution to the enrichment of the language and style of Amharic literature.

The author has adopted an orthography of his own, the merits of which will no doubt be evaluated by Ethiopian grammarians.

Fiqer Eske Meqaber is a fictional work of prose of considerable length, which has generated immediate and widespread interest.

In recognition of his creative ability, the Haile Selassie Award for Amharic Literature, gold medal and diploma with a sum of Eth. $ 10,000 will be given to H.E. Ato Haddis Alemayehou.